

"…በወቅቱ እኛ መስዋዕትነት እንዳንከፍል ከእኛ በፊት ሕወሓቶች ይሰው ነበር…"

ታጋይ በረከት ስምዖን

በገፅ 4




# ሰንደቅ

ሰንደቅ 10ኛ ዓመት ቁጥር 485 ረቡዕ ታህሳስ 15 2007 ዋጋ 7 ብር

# የኢትዮጵያ ዓመታዊ የነዳጅ ወጪ ከ51 ቢሊዮን ብር በላይ ደረሰ

*• ከኤክስፖርት ገቢው አንፃር ከ74 በመቶ በላይ የአገሪቱ ወጪ ለነዳጅ ግዢ ይውላል*

በፀጋው መላኩ

የኢትዮጵያ የነዳጅ ፍላጎት መጠን ከዓመት ወደ ዓመት በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ሲሆን በ2005 በጀት ዓመት የነበረው የነዳጅ አቅርቦት መጠን 43 ቢሊዮን 288 ሚሊዮን 83 ሺ ብር ጋር የተመጣጠነ የውጪ ምንዛሪን በማውጣት 2 ቢሊዮን 289 ሚሊዮን 612 ሺ የነዳጅ ምርት ግዢ የተከናወነ መሆኑን ከኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ያገኘነው መረጃ አመለከተ።

በ2006 በጀት ዓመት የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት 2 ቢሊዮን 622 ሚሊዮን 806 ሺ ሜትሪክ ቶን የነዳጅ ግዢን የፈፀመ ሲሆን ለዚህም 51 ቢሊዮን 733 ሚሊዮን103 ሺ ብር የሚተመን የውጪ ምንዛሬን ወጪ አድርጓል። በዚህም በነዳጅ አቅርቦቱ ደረጃ የ2006 በጀት ዓመት ከ2005 በጀት ዓመት አንፃር ሲታይ የ333 ሚሊዮን 195 ሺ እድገትን አሳይቷል።

በወጪ ደረጃም የ2006 በጀት አመት ከቀዳሚው ዓመት የ8 ቢሊዮን 445 ሚሊዮን 20 ሺ ብር ልዩነትን ያሳየ መሆኑን ከኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ያገኘነው መረጃ ያመለክታል። በ2007 በጀት አመት በሩብ ዓመት 12 ነጥብ 9 ሚሊዮን ብር የሚተመን የውጪ ምንዛሪን ወጪ በማድረግ 623 ሚሊዮን 918 ሜትሪክ ቶን የፈሳሽ ነዳጅ ግዢ የተከናወነ መሆኑን መረጃው ያመለክታል።

በ2006 በጀት ዓመት አገሪቱ ለነዳጅ ያወጣችው የውጪ ምንዛሪ መጠን አሁን ባለው የዶላር ምንዛሪ አንፃር ሲሰላ 2 ነጥብ 55 ቢሊዮን ዶላር ሲሆን ከንግድ ሚኒስቴር ባገኘነው መረጃ መሰረት ደግሞ በዚሁ በጀት ዓመት የአገሪቱ የወጪ ንግድ ገቢ መጠን 3 ነጥብ 25 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ነው።

ከኤክስፖርት ከተገኘው ገቢ አንፃር ሲሰላ ለነዳጅ ግዢ የሚወጣው የውጪ ምንዛሪ መጠን ከ74 በመቶ በላይ ነው። መንግስት የአምስቱን የትራንስፎርሜሽን እቅዱን ሲነድፍ የአገሪቱ የኤክስፖርት ገቢ መጠን በየዓመቱ እያደገ ሄዶ በትራንስፎርሜሽን እቅዱ መጨረሻ፤ ማለትም በ2007 በጀት ዓመት መዝጊያ ላይ 10 ነጥብ 2 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ለማድረስ አስቦ የነበረ ቢሆንም በ2006 የትራንስፎርሚሽን ዘመኑ ሊጠናቀቅ አንድ ዓመት እየቀረው በዚሁ በጀት ዓመት የተገኘው የኤክስፖርት ገቢ መጠን ግን 3 ነጥብ 2 ቢሊዮን ዶላር ብቻ ነበር። ይህም ከትራንስፎርሜሽን እቅዱ አንጻር ሲታይ ከ 32 በመቶ የሚበልጥ አፈፃፀም ሆኖ አልታየም።

በዚሁ ዙሪያ ያነጋገርናቸውና ስሜ አይጠቀስ ያሉ አንድ የኢኮኖሚ ባለሙያ የአገሪቱ የኤክስፖርት ገቢ ማደግ ባልቻለበት ሁኔታ የነዳጅ ፍላጎቷ በየጊዜው እየጨመረ መሄዱ ኢኮኖሚው ላይ የሚፈጥረው ጫና በቀላሉ የማይታይ መሆኑን ገልፀዋል። በኤክፖርት ከሚገኘው ገቢ አንፃር አገሪቱ ሰማኒያ በመቶ

በገፅ 7

# የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ ለሶስት ተከፈለ

*• የቢሮ ኃላፊውንና ምክትሉን አነሳ*



በፀጋው መላኩ

የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ የአደረጃጀት ለውጦችን በማድረግ ለሦስት መከፈሉ ታወቀ። በዚህ የአደረጃጀት ለውጡ ቀደም ሲል የቢሮ ኃላፊ የነበሩትን አቶ ቀፀላ ዘውዴን በማንሳት በአቶ ያብባል አዲስ የተካ ሲሆን በምክትል ቢሮ ኃላፊነት ለረዥም ዓመታት የሰሩትን ወይዘሮ ትብለፅ አስገዶምን ከኃላፊነታቸው የተነሱ መሆኑ ታውቋል። በወይዘሮ ትብለፅ ቢሮ በመገኘት በማን እንደተተኩ ለማወቅ ሙከራ ያደረግን ሲሆን እስከ አሁንም ድረስ በእሳቸው ቦታ ኃላፊ ያልተመደበ መሆኑን ተረድተናል።

የትራንስፖርት ቢሮው ከዚህ ቀደም በነበረው አደረጃጀት በሶስት ዋና ዋና የሥራ ሂደቶችና ደጋፊ የስራ ሂደቶች ይመራ የነበረ ሲሆን አሁን ግን ይህንን አደረጃጀት ለመቀየር ሰፊ ሥራ እየተሰራ መሆኑን የትራንስፖርት ቢሮው ምክትል ኃላፊ አቶ ውድነህ ደስታ ገልጸውልናል። እንደ አቶ ውድነህ ገለፃ ቀደም ሲል የነበሩት የሥራ ሂደቶች ቀርተው ሥራው በሁለት ባለስልጣን መስሪያ ቤቶችና በአንድ ኤጀንሲ እንዲደራጅ በመድረግ ላይ ነው። እንደ አቶ ውድነህ ገለፃ ቀደም ሲል በነበረው አደረጃጀት መሰረት የትራንስፖርት ኦፕሬሽን ዋና የሥራ ሂደት፣ የትራፊክ ማኔጅመነት ዋና የሥራ ሂደትና የትራንስፖርት ፕላኒግ

በገፅ 7



ሀገራችንን ለማሸበር ሲዶልቱ የሚውሉ

## የተቃዋሚ ፓርቲ ግለሰብ አመራሮች አሉ

ጠ/ሚኒስትር ኃ/ማርያም ደሳለኝ

በገፅ 3

## በባህርዳር ሰልፍ ለጥቃት የተጋለጡ ወገኖች ጉዳይ እንዲጣራ አራት ፓርቲዎች ጠየቁ

በገፅ 7

ሕግ…13
ኢኮኖሚ…8
መዝናኛ…10
የኔ ሃሳብ…18

ርዕሰ አንቀጽ

# ሰዎች ለተቃውሞ አደባባይ በመውጣታቸው ብቻ ሊጎዱ አይገባም



ሰሞኑን በባህርዳር ከተማ ከግዮን ሆቴል እስከ አዝዋ ሆቴል ሊሰራ በታቀደው የመንገድ ማስፋፊያ ግንባታ ጋር ተያይዞ የታቦት ማረፊያ የሆነው የመስቀል አደባባይ ሊፈርስ ነው በመባሉ በርካታ ሕዝብ ለተቃውሞ አደባባይ ወጥቷል። ይህ ድንገት አደባባይ የወጣው ሕዝብ ከጸጥታ ኃይሎች ጋር በመጋጨቱም ሰዎች ለሞትና ለመቁሰል አደጋ መጋለጣቸው የሚታወስ ነው።

በቅርቡም ከአዲስአበባ ማስተር ፕላን ክለሳ ጋር ተያይዞ በኦሮሚያ አንዳንድ ከተሞች የተቃውሞ ሰልፍ የወጡ ተማሪዎች ከጸጥታ ኃይሎች ጋር ተጋጭተው ለጉዳት መጋለጣቸውን የምናስታውሰው ነው።

የመንግሥት ኃላፊነት የሕዝብን ጸጥታና ሠላም መጠበቅ ነው። ሕዝብ በታቀደም ሆነ ባልታቀደ ሁኔታ የተቃውሞ ሰልፍ ሊያካሂድ ይችላል። ይህ በኢትዮጵያም ብቻም ሳይሆን በሰለጠኑትም እንደዩናትድ ስቴትስ አሜሪካ ባሉ ሀገራት ጭምር ዜጎች መንግስታቸውን አደባባይ ወጥተው የሚቃወሙባቸው በርካታ አጀንዳዎች አሏቸው። ልዩነቱ ግን እንደአሜሪካ ባሉ ሀገራት የጸጥታ ኃይሎች ለሰልፍ የወጡ ሰዎች ላይ ተኩስ ሊከፍቱ አይችሉም። ይህ ሆኖ ከተገኘም ቅጣቱ ከበድ ያለ በመሆኑ የጸጥታ ኃይሎች የዜጎችን መብት ላለመጣስ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋሉ። አንዳንዴ በተቃራኒው የጸጥታ ኃይሎች ለተቃውሞ በወጡ ወገኖች ከባድ ጥቃት እየደረሰባቸውም ቢሆን የጦር መሣሪያ መጠቀምን እንደ አማራጭ አድርገው አይወስዱም። እንደኢትዮጵያ ያሉ አንዳንድ የአፍሪካ ሀገራት ግን ሰልፍን በተኩስ ለመበተን የሚሞክሩበት አጋጣሚ ይበዛል። በዚህም ምክንያት ክቡር የሆነው የሰው ልጆች ሕይወት እንደዋዛ ሲቀጠፍ ይታያል። እናም ኢትዮጵያ በሰለጠነ መንገድ የጸጥታ ኃይሏን በተለይም ፖሊሶች ሰላማዊ ሰልፍን የመቆጣጠሪያ ዘመናዊ መንገዶችን በማስተማርና ተገቢውን ቁሳቁስንም በማሟላትና በማስታጠቅ ሰዎች ሳይጎዱ ተቃውሟቸውን ገልጸው ወደቤታቸው እንዲሄዱ ለማስቻል ብዙ መሰራት አለበት።

ክቡር ጠ/ሚ አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ሰሞኑን በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ሰላማዊ ተቃውሞን በሰለጠነ መንገድ ለመቆጣጠር ለፖሊሶች ሥልጠና መሰጠቱን እንዲሁም በቁሳቁስም እንዲታጠቁ መደረጉን በመግለጽ የመንግስታቸው አቋም በሰላማዊ መንገድ ሰልፍን መቆጣጠር መሆኑን አስታውቀዋል። በተጨማሪም ሰልፍ የወጡ ሰዎች እንዴት ሊሞቱ እንደቻሉ ተጣርቶም ተገቢው እርምጃ እንደሚወሰድም ይፋ አድርገዋል። ይህ ጥሩና የሚደገፍ አቋም ነው። ፖሊሶች በዘመናዊ ስልት ሰልፎችን ተቆጣጥረው፤ ሰዎች ሳይጎዱ በሠላም ወደቤታቸው ሲገቡ ማየት እንመኛለን። ሰዎች ሰልፍ በመውጣታቸው ምክንያት ተገደሉ፣ ቆሰሉ፣ ተደበደቡ የሚሉ የመገናኛ ብዙሃን ወሬዎች ተቀይረው በምትኩ ስለጸጥታ ኃይሉ ብቃትና ዲሲፒሊን የሚነገርባቸው እንዲሆኑ ምኞታችን ነው። በሕገመንግሥቱም ጭምር ጥበቃ ያገኙ የዜጎች ሰብዓዊ መብቶች በምንም መልኩ እንዳይጣሱ መንግስት ያለውን ቁርጠኛ አቋም በተግባርም ጭምር ሊያረጋግጥ ይገባል።■

## ቁጥሮች

**230 ሚሊዮን**

እስከአሁን ለአርሶ አደሮች የደረሱ አዲስ የግብርና ግብአቶች ዋጋ

**156 ሺህ**

አዲሱን የግብርና ግብአት የተጠቀሙ አርሶ አደሮች ብዛት

ምንጭ - የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ■

## መልዕክቶች

### የግምት ስራ ጦሱ ለህዝቡ ነው

ባለፈው ሳምንት በባህርዳር ከተማ የሚገኘው የመስቀል አደባባይ ለልማት ሊፈርስ ነው የሚለውን መረጃ የሰማው የከተማዋ ህዝብ ባደረገው ተቃውሞ በርካታ ዜጐች ጉዳት እንደደረሰባቸው የተለያዩ የማኅበራዊ መገናኛ ብዙሃን በምስል እያስደገፉ ጭምር እያወጡ ይገኛሉ። እስከ አሁን ድረስ በተለይ በመንግስት መገናኛ ብዙሃን በኩል ጉዳቱን አስመልክቶ የተባለ ነገር የለም። ሲጀመርም ተቃውሞው ሊነሳ የቻለው የአካባቢውን ኅብረተሰብ በቅርበት ካለማነጋገር እና ገዢው ፓርቲ ለመሬት ካለው ከፍተኛ ፍቅር የተነሳ እንደሆነ ያሳያል። በአንድ በኩል ሃይማኖትና መንግስት የተለያዩ ናቸው፤ በሌላ በኩል ደግሞ የሙስሊሙንም ሆነ የክርስቲያኑን በዓል አብሬ አክብሬ በቀጥታ ስርጭት አስተላልፋለሁ። የሚለው ገዢው ፓርቲ ዞር ብሎ ደግሞ እንዲህ ህዝቡን ለአደጋ ሲያጋልጠው ይታያል። ሰዎች ከቆሰሉ እና ከተጐዱ በኋላ ልማቱን ልናጥፈው እንችላለን እያሉ የግምት ስራ የሚሰሩበት ዓላማቸው ግልፅ አይደለም።

ከጐጃም በረንዳ - በስልክ የተሰጠ■

### እስኪ ወደ መንስኤው እንመልከት

ወትሮም በእኛ ሀገር አንድ ነገር ሲነገር በርካታ ተመሳሳይ ነገሮች ቀስ በቀስ መውጣት ይጀምራሉ። የሃና ላላንጉን ተገዶ መደፈር ሰምተን ሐዘናችን እና ቁጭታችን ሳይለቀን ከሰሞኑ ደግሞ ከየክልሎቹ ሰዎች ተገደው መደፈራቸውን እንዲያም ሲል በዚህ በመደፈራቸው ምክንያት ህይወታቸው ማለፉን በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን እየሰማን ነው። በአርባ ምንጭ እና በአማራ ክልል የተከሰቱትን አሰቃቂ ድርጊቶች ለአብነት ያህል ማንሳት ይቻላል። እነዚህ ድርጊቶች ስለተደረሰባቸው ይፋ ሆኑ እንጂ ሌሎች በርካቶች ደግሞ በየአካባቢው የእነዚህ አይነት ጨካኝ ወንዶች ሰለባ እየሆኑ ይገኛሉ። በአሁኑ ወቅት እዚህ አካባቢ እንዲህ ተደረገች ከሚለው ይልቅ ለዚህ አይነቱ እኩይ ተግባር መንስኤ በሆኑት ጉዳዮች ላይ በስፋት መስራት የሚያስፈልግ ይመስለኛል። ይህ ደግሞ የሁሉም ኅብረተሰብ ክፍል ኃላፊነት ሊሆን ይገባል።

ወ/ሮ እቴነሽ - ከአዲሱ ገበያ■

"ሰንደቅ" ጋዜጣ በሰንደቅ የሕትመትና የማስታወቂያ አገልግሎት ኃ/የተ/የግ/ማኅበር በንግድ ሚኒስቴር በንግድ ሥራ ፈቃድ ቁጥር 14/673/7498/2004፣
በብሮድካስት ባለሥልጣን የምዝገባ ቁጥር 38/2001 የተመዘገበ ሳምንታዊ ጋዜጣ ነው

ዋና አዘጋጅ
ፍሬው አበበ
ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር 12/201
0911 61 79 35
abebeferew@gmail.com

ም/ዋና አዘጋጅ
ፋኑኤል ክንፉ
0911 865119
Kinfu2006@yahoo.com

አዘጋጅ
ፀጋው መላኩ

ከፍተኛ ሪፖርተሮች
አሸናፊ ደምሴ
መስከረም አያሌው

ግራፊክ ኤዲተር
ነብዩ መሥፍን
0911 18 09 33
nebiyou1st@yahoo.com

ኮምፒዩተር ጽሁፍ
አለምነሽ ታከለ
ሰብለወንጌል ንጉሴ
ምናለሽዋ ተ/አረጋይ

ህትመት ክትትልና ስርጭት
በዛብህ ተክሉ
0911 41 68 00

ማስታወቂያ ሽያጭ
ባይለየኝ ወርቁ
bayleyworku@gmail.com
0921 56 95 03
0912 95 67 95

አታሚ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት
አድራሻ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 07 የቤት ቁጥር 984

የአሳታሚው አድራሻ:- ቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 05/03 የቤት ቁጥር 027 ከአትላስ ሆቴል በስተጀርባ 011-6-62 81 90/ 011-6-18 40 34/ 0911 95 58 16 ፖ.ሣ.ቁ. 80964
www.sendeknewspaper.com




# ሀገራችንን ለማሸበር ሲዶልቱ የሚውሉ
# የተቃዋሚ ፓርቲ ግለሰብ አመራሮች አሉ

## ጠ/ሚኒስትር ኃ/ማርያም ደሳለኝ

**ጠ/ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከትላንት በስቲያ በጽ/ቤታቸው ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተዋል። በተመረጡ ጉዳዮች ዙሪያ የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።**

(በፍሬው አበበ)

- የፖለቲካ ፓርቲዎች ሠላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብት ተከልክለናል እንዲሁም መሪዎቻችንና አባሎቻችን ይታሠራሉ ማለታቸውን በተመለከተ፣

የኢትዮጵያ መንግሥት በዚህ የታዳጊ ዴሞክራሲ ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሕጋዊና ሠላማዊ መንገድ እየተወዳደሩ የዲሞክራሲ ባህል እንዲጎለብት፣ እንዲያድግ ኃላፊነት አለብን የሚል እምነት አለን። ገዢው ፓርቲ፣ ተቃዋሚ ፓርቲም በአጠቃላይ ይህንን ታዳጊ ዲሞክራሲያችንን ለማጎልበት የየበኩላችንና ሚና መጫወት አለብን። ይሄ የመድብለ ዲሞክራሲ ሥርዓት በሀገራችን መጎልበት ጉዳይ ሕገ-መንግሥታችንም በአግባቡ ያስቀመጠው ጉዳይ ነው። ስለዚህ ይሄ ነገር መጎልበት ማለት የተለያየ አስተሳሰቦች ወኪሎች ነን የሚሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተደራጅተው እነዚህ የወከሉዋቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች አስተሳሰብ በነፃነት ማራመድ መቻል አለባቸው። ማንኛውም ሀገር ላይ ዲሞክራሲ እንዲያብብ ካስፈለገ የዲሞክራሲ መጫወቻ ሜዳዎች በሕግና በሥርዓት የሚመሩ መሆን አለባቸው። ብዙውን ጊዜ ብዙ ሰዎች ይህን ከእግር ኳስ መጫወቻ ሜዳ ጋር ያነፃፅሩታል። ዳኛው የሌለበት፣ ተቆጣጣሪ ባሌበት በሌለበት ሁሉም ሰው ወደ ሜዳ ገብቶ ይጫወት ቢባል እግር ኳስ፣ እግር ኳስ ሊሆን አይችልም። ጨዋታውም በሥርዓት ሊከናወን አይችልም።

የእግር ኳስ ህግና ሥርዓት የተበጀው ሕግና ሥርዓት በማስፈለጉ ነው። ዴሞክራሲን ፓርቲዎች የሚሰሩበት መስፈርት እንደዚሁ በሕገ-መንግሥቱ፣ በሕገ-መንግሥቱ በመነጩ ሕጎች ሥነሥርዓቶች ያለው ሆኖ ተቀርጿል። በእኛ ሀገር እንዲሁም በ2002 ምርጫ ወቅት ሕጋዊ ሥርዓቱ እና የምንጫወትበትን ሜዳ የበለጠ ለማሻሻል ይረዳናል የተባለ የምርጫ ሥነምግባር ደንብ አውጥተናል። እስከዚህ ድረስ በመሄድ የሀገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎች በሕጉ መሠረት የሚንቀሳቀሱበትን ፍላጎታቸውን አስተሳሰባቸውን፣ ሒደታቸውን ለሚወክላቸውና ለአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ሊገልጹ የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለብን ተብሎ እየተሰራ ነው ያለው። በዚህ ሂደት ውስጥ ከመጫወቻው ሜዳ ውጪ እንሠራለን የሚሉ ፓርቲዎች በሚኖሩበት ጊዜ ያው ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት እነዚህ አባላት ወጣ ብለውሃል ተብሎ ቢወጣ የማስጠንቀቂያ ካርድ እንዲሁም ቀይ ካርድ የሚሰጥበት ሁኔታ ሊኖር ይገባል ነው። ስለዚህ አሁን ቢጫ የሚሰጣቸውም አሉ፣ ቀይ የሚሰጣቸው አሉ። ደግሞ በጨዋታ ሜዳ እየተጫወቱ ያሉም አሉ።

በገፅ 16

# “...በወቅቱ እኛ መስዋዕትነት እንዳንከፍል ከእኛ በፊት ሕወሓቶች ይሰው ነበር...”

## ታጋይ በረከት ስምዖን

ህወሓት የትጥቅ ትግል የጀመረበትን 40ኛ አመቱን ለማክበር ሰፊ የቅድመ ዝግጅት ክንውኖች በመደረግ ላይ ናቸው። ተጠቃሽ ከሆኑ የዚህ ቅድመ ዝግጅት መርሃግብሮች መካከል የሚጠቀሰው ከታህሳስ 13 -16 ቀን 2007 ዓ.ም በታዋቂ አርቲስቶች እና በጋዜጠኞች የሚደረገው የትጥቅ ትግሉን ታሪካዊ ዳራ የመጎብኘት ክንውን አንዱ ነው። በዚህ ጽሁፍም የትጥቅ ትግሉ ከተጀመረበት በማይ ሓንሰን ወረዳ ደደቢት ተብሎ በሚጠራው ስፍራ ላይ በመገኘት ህወሓት በኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ውስጥ ምን ድርሻ ነበረው? ምንስ ይዞ መጣ? የኢህዴን እና ህወሓት መገኛኘት ፋይዳስ ምን ነበር በሚሉ አንኳር ነጥቦች ዙሪያ ታጋይ በረከት ስምኦን ያቀረቡትን ልብ የሚነካ የትግል ምስክርነት ለአንባቢያን በሚመች መልኩ ወደ ጽሁፍ ቀይረን እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

በፋኑኤል ክንፉ (ደደቢት - ማይሓይሰን)



(ከግራ ወደ ቀኝ) አቶ በረከት ስምኦን፣ አቶ አባይ ፀሃዬ፣ አቶ ስዩም መስፍን እና አቶ ስብሃት ነጋ - (ደደቢት ታህሳስ 2007)

ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ የለውጥ ፍላጎቶች ዘመናትን ያስቆጠሩ ናቸው። የብዙ ትውልዶች የትግል ውጤትም ናቸው - ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚደረግ የቅብብሎሽ ትግል ሆኖ ኢትዮጵያን ለማሻሻልና ለመለወጥ ኢትዮጵያዊያን ዋጋ የከፈሉበት ሂደትም ነው።

በዚህ ሂደት ውስጥ የካቲት አስራ አንድ የተመሰረተው ህወሓት በዚህ ሂደት ውስት የሚጠቀስ አንዱ ድርጅት ነው። በዚያን ጊዜ ከተመሰረቱት ድርጅቶች ህልውናውን ጠብቆ ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በመሆን በኢትዮጵያ ትልቅ ለውጥ ለማምጣት ተሳክቶለት ▶



በአሸናፊነት የወጣ ድርጅት ነው::

ህወሓት የሰራቸው ስራዎች ምንድን ናቸው ብዬ ሳይ፣ የመጀመሪያው በ1967 ዓ.ም ሲደራጁ ከዚያ በፊት የነበረው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ አካባቢ የነበረው ሁኔታ ማስታወስ ጠቃሚ ይመስለኛል:: ለውጥ ውስጣችን እንዲቀሰቀስ፣ እኛ ጋር የነበረው የለውጥ ስሜት በሌሎች ኢትዮጵያዊያን ውስጥም እንዲኖር፣ ብዙ ትውልድ መስዋዕትም እንዲከፍል ያደረገው የዴሞክራሲ የልማት እና የመለወጥ ብሎም የህዝቦችን ፍላጎት የሚያረካ ብቃት ያለው ሥርዓት ስላልነበረ ነው:: እንደዚህ አይነት ስርዓት በሌለበት፣ በተለይ ብዝሃነትን በአግባቡ ማስተናገድ የማይችል፣ የሃይማኖት፣ የብሔር መብት በአግባቡ ማክበር የማይችል የዜጎችን ዴሞክራሲያዊና የልማት ጥያቄዎችን በአግባቡ መመለስ የማይችል ስርዓት ባለበት እና በወቅቱ የነበረው ስርዓት የቆመው ከምንም ነገር በላይ በአፈና ስርዓት ተደግፎ በሆነበት፣ በጣም ግዙፍ ወታደራዊ ተቋም፣ በጣም ግዙፉ የስለላ ተቋም፣ በመላ ሀገሪቱ በተንሰራፋበት ሁኔታ እንዴት ነው ይህ የአፈና ስርዓት አስወግዶ በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲ ማምጣት የሚቻለው? ግዙፉን የአፈና ተቋምስ በታሰበው መልኩ ማስወገድ ይቻላል ወይ?

እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ ስርዓት ውስጥ የመጨረሻ ትልቁን አፋኝ የደርግ አገዛዝ 500ሺ ጦር ሰራዊት የነበረው፣ በጥቁር አፍሪካ በትጥቁም በወታደራዊ ብዛቱም የሚስተካከለው አልነበረም:: ይህን ሃይል አስወግደህ ብቻ ነው፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲ ሊመጣ የሚችል የነበረው:: ይህ ሃይል ባለበት ቀይ ሽብር ነበር የነበረው:: ይህ ሃይል ባለበት አፈና ነበር የነበረው:: ስለዚህ ይህን ግዙፍ ሃይል እንዴት ነው የምናስወግድነው? የሚለው ጉዳይ በጣም ብዙ መሰረታዊ ጥያቄዎችን መመለስ ይጠይቅ ነበር:: ከሁሉ በፊት የጠራ ዓላማ መያዝንም ይጠይቃል:: የት ነው የምደርሰው? መዳረሻየስ የት ነው? ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲ ማስፈን፣ ለልማት የተመቸ ከባቢያዊ ሁኔታዎች መፍጠር፣ ዴሞክራሲያዊ አዲስ የሆነ አንድነት መፍጠር እነዚህን የመሳሰሉት ግልፅ ዓላማዎችን መያዝም ይጠይቅ ነበር:: ሁለተኛ፣ ብቃት ያላቸው የትግል ስልቶች፤ ትክክለኛ አቅጣጫዎች መተለምና እነሱንም ተግባራዊ ማድረግ ይጠይቅም ነበር:: ስለዚህም ህወሓት ይሄን (ከላይ የሰፈሩትን) ይዞ ነበር የተነሳው:: ህወሓትን ከሌሎች ድርጅቶች የሚለይበት ወሳኙ ነገርም ይህ ነው:: ጥርት ያሉ ነገሮችን፣ ሊያታግሉ የሚችሉ፣ ለውጥ ማምጣት የሚችሉ፣ ሃሳቦችን ይዞ መምጣት::

ላለፉት ሰላሳ አራት ዓመታት ከህወሓት ጋር አብረን ታግለናል:: ድርጅቱን በቅርቡ እናውቀዋለን፣ ህወሓት ለሃሳብ ልዕልና ትልቅ ቦታ ያለው ድርጅት ነው:: ጥርት ነገር ያለ መያዝ:: ነገ ከነገወዲያ በምናያቸው ቦታዎች ሃሳብን እንዴት እንደማጥራት የሚችል ድርጅት ነው:: ለትግሉ መነሻና መድረሻውን ጥርት አድርጎ በደንብ ማስቀመጥ በመቻል ላይ ትልቅ አቅም አለው:: ስለዚህም ግልፅ የትግል ዓላማ ይዞ የተንቀሳቀሰ ድርጅት ነበር:: ይህንን ዓላማ ይዞ በመጀመሪያዎቹ የደርግ ዓመታት የመሃል ሀገር እንቅስቃሴ በተዳከመበት ጊዜ ሸክሙ እዚህ ሰሜን ኢትዮጵያ ላይ ነበር:: በጣም ከባድ ሸክም ነበር የተቋቋምነው:: የትግራይን ሕዝብ ይዞ ከትግራይ ሕዝብ ጋር እጅና ጓንት ሆኖ በጣም ብዙ ዘመቻዎችን አልፏል:: እኛ በለሳ እስከምንመጣ፣ በስድስተኛ ዘመቻ ላይ ነበር ትግራይ የደረስነው:: እነዚህ ማዕበሎች ነበሩ:: የደርግ ሰራዊት ይመጣል፣ ድርጅቱን ለማጥፋት ይሞክራል:: ድርጅቱ ጥቃቱን ይቋቋማል፣ ወደአዲስ ምዕራፎችም ይሻገራል:: በዚህ መንገድ የደርግ ማዕበሎችን እየተቋቋመ የዘለቀ ድርጅት ነው ፤ህወሃት::

**እኛ ብአዴኖችም ሁሌም ቢሆን ራሳችንን ከህወሓት ነጥለን ያየንበት ጊዜ የለም:: ሁላችንም “ወየንቲ ኢና” (ወያኔዎች ነን) ነው የምንለው**

በዚህ ሁሉ ሂደት ጠንካራ ሠራዊት ገንብቷል:: እኛ ደጀን ነው የምንለው፣ ከሕዝቡ ጋር የፀና እና ጥብቅ ግንኙነት ነበረው:: ለሕዝብ ታዛዥ ሕዝብን የሚያከብር ድርጅት ነበር:: በዚህ መንገድ እየታገለ ቆየ:: እኛ በ1972 ዓ.ም. ከኢሕአፓ ተለይተን ህወሓት ወንድም ድርጅት ይፈልግ በነበረበት ጊዜ፣ ከበለሳ የመሐል ሃገሩ አልመች ሲለን ወደ ትግራይ እንሂድ ብለን መጣን:: ከህወሓት ጋርም ተገናኘን፣ ከተገናኘን በኋላ በብዙ ነገሮችም አብረን ሠርተኛል፤ታግለናል:: በወቅቱ እኛ ቁጥራችን ትንሽ ነበር:: እነሱ ደግሞ በአንፃሩ ግዙፍ መሆን ጀምረዋል:: እኛ መስዋዕትነት እንዳንከፍል ከእኛ በፊት እነሱ ለመሰዋት ብዙ ብዙ ነገሮች እያደረጉ እያገዙን፣ የእኛ ሃይል እንዳይመታ እንዳይመናመን ከፍተኛ እገዛ አድርገውልናል:: በኋላ የእኛ የሰው ሃይል እየተጠናከረ ሲመጣ በጋራ እየተፋለምን ኢሕአዴግን መስርተን ግዙፉን የደርግ ሰራዊት ለመደምሰስ ችለናል::

ስለዚህም የህወሓት አንዱ ትልቁ ሚና ተብሎ መጠቀስ ያለበት ምንድነው ከተባለ በኢትዮጵያ የአፈና ስርዓትን ማስወገድ ነው:: ያንን የአፈና ስርዓት ማስወገድ ባይቻል ኖሮ፣ ከዚህ ግዙፉ የአፈና ተቋም ጋር ኢትዮጵያ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት አትበቃም ነበር:: ይህ በታሪክ የተለየ ተደርጎ መታየት ያለበት ነው:: ሊከበርም፣ ሊገለጽም፣ ሊፃፍበትም የሚገባ ነው:: የጦርነቱ ሂደት፣ የተከፈለው መስዋዕትነት፣ ትግሉ መሃል ሃገር ሲዳከም እዚህ ጫፍ ላይ እንደምንም ሕዝባዊ ትግሉን ጠብቀህ የመቀጠል ነገር ትልቅ ትልቅ መስዋዕትነትን፣ አስተዋይነትን፣ በዚህ ደረጃ ሕዝባዊ ልቦናን የሚጠይቅ ነበር:: ለዚህም ነው የህወሓት ትልቅ ሚና፣ የነበረውን የአፈና ስርዓት በኢትዮጵያ ውስጥ ላይመለስ አድርጎ መታገሉ ተጠቃሽ የሚሆነው::

ይህም ብቻ አይደለም:: ደርግ በወደቀ ማግስት ምንድን ነው የተደረገው ብለን ከመጀመሪያው እንይ:: የካቲት 11 ድርጅቱ እዚህ ቦታ ትጥቅ ትግል ሲጀምር ይዞት የነበረውን ዓላማ በፍጥነት ወደ ተግባርመተርጎም የደመረበት ወቅት ነው:: የአፈናው ስርዓት ተቋም ከተገረሰሰ በኋላ አዲስ መሰረተ ሰፊ ዴሞክረሲ ነው በኢትዮጵያ ውስጥ የተዘረጋው:: ስለዚህም ይህ መስዋዕትነት ባይኖር ኖሮ ያንን ማድረግ ይቻል ነበር ወይ? በብሔር ጥያቄ ዙሪያ በወቅቱ ብዙ አማራጮች ነበሩ:: በኦሮሚያ ውስጥ ከዳር እስከ ዳር የነበረው ኦነግ ነው:: በደቡብ ኢትዮጵያም ብዙ ተመሳሳይ ድርጅቶች ነበሩ:: በሶማሌም በአፋርም ተመሳሳይ ድርጅቶች ነበሩ:: በመሐል ሀገር ኢሕፓ ሞካክሮ የተወው ትግል አለ:: ተስፋ መቁረጥ በተዛባ አካሄድ የመሄድ እድሎች ሰፍተው የነበረበት ሁኔታ ነበር የነበረው:: ይህን ተቋቁሞ በትክክለኛ መስመር ተመርቶ ጥሩ አጋሮች ካገኘ በኋላ የአጋርነት እንቅስቃሴውን አጠናክሮ ላለፉት አርባ አመታት የታገለ ድርጅት ነው::

በሌላ መድረክ ከዴሞክራሲው ባሻገር በልማት ሥራዎች ላይ ያለውን አስተዋፅዖ እንመሰክራለን:: ሆኖም ግን የህወሓት አስተዋፅዖና ሚና በኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ውስጥ ትውልድ በቅብብሎሽ ትግሉን ዳር ያደርሳል ብሎ የተነሳበት ሁኔታ በልዩ ሁኔታ መታየት ያለበት ይመስለኛል:: ይህን ትግል ከመነሻው የመሩት እዚህ ያሉት ጓዶች ናቸው:: ከእነሱ ጋር በመሆን አብረው ሲመሩት የነበሩት ምንአልባትም በአስተሳሰብ ልቀት ሁላችንም የምናከብራቸው አቶ መለስ ለዚሁ ትግል ያበረከቱት ትልቅ አስተዋጽኦም አለ::

ህወሓት የአስተሳሰብ ጥራት የነበረው፣ አስተሳሰቡንም በተጨባጭ ተግባር ላይ ማዋል የሚችል ድርጅት ነው:: ይህም በመሆኑ ነው ብዙ ንቅናቄዎች ተጀምረው በከሸፉበት ሁኔታ ሃሳብን ተግባራዊ በማድረግና በተለይ ህዝብን ይዞ በብቃት በመታገል ረገድ ይኸው ድርጅት ውጤታማ የሆነውና እዚህ ደረጃም የደረሰው::

እኛ ብአዴኖችም ሁሌም ቢሆን ራሳችንን ከህወሓት ነጥለን ያየንበት ጊዜ የለም:: ሁላችንም “ወየንቲ ኢና” (ወያኔዎች ነን) ነው የምንለው:: ስለዚህ ይህንን ምስክርነት የምሰጠው እንደ ብአዴን ሆኜ አይደለም፤ እንደ አንድ ወያናይ ሆኜ ነው:: እንኳን ለዚህ በቃችሁ፤ እንኳን ለዚህ በቃን እላለሁ::



www.sendeknewspaper.com

# ለውጪ ሀገር የሕክምና ጉዞ የሚያማክር ተቋም ሥራ ጀመረ

በአሸናፊ ደምሴ

ኢትዮጵያውያን ዓለም በደረሰበት የሕክምና ደረጃ ተጠቃሚ እንደሆኑ የማድረግ አላማን አንግቦ የተነሳው ጌትዌል የጤና ማማከር አገልግሎት ተቋም ስራውን መጀመሩን አስታወቀ:: የጌትዌል የጤና ማማከር አገልግሎቶች መስራችና ዋና ዳይሬክተር ዶክተር በጋሻው ባይለየኝ ለጋዜጠኞች በሰጡት ማብራሪያ ተቋሙ በሀገራችን ለሚገኙ ህሙማን የተሻለ ህክምናን በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲያገኙ ለማስቻል የሚሠራ መሆኑን ጠቅሰዋል:: በዚህም የምክር፣ የውጪ ሀገር ህክምና ማመቻቸት፣ የጉዞ ወቅት አጋዥ የህክምና ባለሙያዎችን ማቅረብና የአምቡላንስ አገልግሎት መስጠትን ጨምሮ ታካሚዎች የተሟላ ህክምና እንዲያገኙ ይሠራል ብለዋል::

ጌትዌል የጤና ማማከር አገልግሎት ሰጪ ተቋም በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚጠቀሱ ዕውቅና ካላቸው በታይላንድ፣ በህንድ፣ በሲንጋፖርና በተባበሩት አረብ ኤሜሬቶች ውስጥ ከሚገኙ ስምንት ሆስፒታሎች ጋር በጥምረት እንደሚሰራ አስታውቀዋል:: በእነዚህ ሆስፒታሎችም ውስጥ ዜጎች በሀገራችን ውስጥ የማይገኙ ወይም አቅርቦታቸው ዝቅተኛ በሆኑ የህክምና ዘርፎች እንዲታከሙ የማማከርና የማገናኘት ስራዎችን ይሰራል ተብሏል::

በዚህም በሀገራችን አቅርቦታቸው ዝቅተኛ ከሆኑ የህክምና ዘርፎች መካከል ተቋሙ የሚያተኩርባቸው እንደካንሰር፣ የልብና የሳንባ ህክምናና ቀዶ ጥገና፣ የነርቭ ህክምናና ቀዶ ጥገና፣ የአጥንት መገጣጠሚያ ህክምና፣ የመሀንነት ችግር፣ እንደኩላሊት፣ ጉበትና መቅኔ ያሉትን የውስጥ አካል ማስቀየርን ጨምሮ ለህሙማን አገልግሎቱን የት ከማንና እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ያማክራል ብለዋል::

ከጌትዌል ተቋም ጋር ለመስራት ከአራቱ አገራት የተመረጡት ስምንት ሆስፒታሎች ያላቸው የሰው ሃይልና ብቃት፣ የሚጠቀሙት የህክምና ቴክኖሎጂ ደረጃ፣ ከውጪ ሀገር ለሚመጡ ታካሚዎች ያላቸው ልዩ አገልግሎትና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላቸው ተቀባይነት ከግምት ውስጥ ገብቶ የተመረጡ ናቸው የተባለ ሲሆን፤ ከዚህም ባሻገር ሆስፒታሎቹ በዝቅተኛ ዋጋ የተሻለ ህክምናን መስጠት መቻላቸው ተመራጭ እንዳደረጋቸው የተቋሙ መስራችና ዳይሬክተር የሆኑት ዶክተር በጋሻው ባይለየኝ አስረድተዋል::

በተቋሙ በኩል ወደተጠቀሱት ሀገሮች እና ሆስፒታሎች ሄዶ መታከም የሚፈልግ ደንበኛ ሲመጣ የህሙማኑን ሁኔታ ማጣራትና የውጪ ሀገር ህክምና አስፈላጊነትን፤ ቀደም ብሎ የተከታተላቸውን የህክምና ማስረጃዎች በመመርመር፤ በሽተኛው ከሚታከምበት ሆስፒታል ዶክተሮች ጋር መረጃን መለዋወጥ፤ የጉዞውን ሁኔታ ማሰናዳት ጨምሮ ታካሚው ከውጪ ሀገር ህክምናውን ጨርሶ ሲመለስ የህክምና ክትትል እንዲያገኝ ማመቻቸትን ያካተተ መሆኑ ተነግሯል:: እንደዶክተር በጋሻው ባይለየኝ ገለፃ ከሆነ በቀጣይ በውጪ ሀገር በሚሰጡ ክሊኒካል ፌሎ ሺፕ ፕሮግራሞች ላይ የህክምና ባለሙያዎችን በመላክ ልምድ ይዘው እንዲመጡ ከማስቻል ባሻገር፤ የውጪ ዶክተሮች በሀገራችን ተገኝተው ህክምናዎችን የሚሰጡበትን ሁኔታ እንደሚያመቻቹ ጠቁመዋል::■

# መድረክ አባሎቼ እየታሰሩብኝ ነው አለ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በደቡብ ክልላዊ መንግስት በወላይታ ዞን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ አባላት በማዳበሪያ ዕዳ ሰበብ በብዛት እየታሰሩብኝ ነው አለ::

**ከዘንድሮው የምርጫ እንቅስቃሴ አባላቱን ለመግታትና ከትግላቸው ለማራቅ አቅዶ መሆኑን ኃላፊው ግምታቸውን አስቀምጠዋል**

መድረክ እንዳስታወቀው ታህሳስ 14 ቀን 2007 ብቻ በቦሎሶ ሶሬ ወረዳ፡- 1ኛ፤- አቶ ሚሊክያስ ሞታ 2ኛ፡- አቶ በርታ ባሳ 3ኛ፡- አቶ ሞገስ ሞታ 4ኛ፡- አቶ ኤልያስ ገንታ የሚባሉ የመድረክ አባል የሆነው የኢትዮጵያ ማሕበረ-ዴሞክራሲ- ደቡብ ሕብረት አንድነት ፓርቲ /ኢማዴደሕአፓ/ አባላት ተይዘው በወረዳው ፖሊስ ጣቢያ ታስረዋል:: የቤት እንሰሶቻቸውም ጭምር በባለሥልጣናቱ ተይዘው እንደሚገኙም ከስፍራው ከደረሰን መረጃ ለማወቅ ተችሎአል:: ቀደም ስልም አቶ ደምሴ ዳና የቦሎሶ በምቤ ወረዳ የኢምዴደሕአፓ ተጠሪና አቶ ዮሐንስ አበበ የቦሎሶ ሶሬ የፓርቲው ተጠሪ በተመሳሳይ ምክንያት ተሰረው ከቆዩ በኃላ ከጥቂት ቀናት በፊት መፈታታቸው መታወቁን አቶ ጥላሁን እንዳሻው የመድረክ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አስታውቀዋል::

ኢህአዴግ በማዳበሪያ ዕዳ ቢያሳብብም የብድር ጉዳይ ወንጀል ሳይሆን የፍትሐብሔር ጉዳይ መሆኑ እየታወቀ እስከአሁን ዝም ብሎ ቆይቶ አሁን ጉዳዩን ለፍርድ ቤት እንኳን ሳያቀርብ በካድሬዎችና አስተዳዳሪዎቹ አማካይነት የመድረክ አባላትን ለይቶ በሰፊው እያሰረ የሚገኝበት እውነተኛ ምክንያት ከዘንድሮው የምርጫ እንቅስቃሴ አባላቱን ለመግታትና ከትግላቸው ለማራቅ አቅዶ መሆኑን ኃላፊው ግምታቸውን አስቀምጠዋል::

በዚህ ጉዳይ ላይ የደቡብ ክልል የሚመለከታቸውን ኃላፊዎች ለማነጋገር ያደረግነው ጥረት ለጊዜው አልተሳካም::■

# ከደም እጦት ጋር በተያያዘ 40 በመቶ እናቶች በየዓመቱ ይሞታሉ

በአሸናፊ ደምሴ

በአገራችን ከ25 እስከ 40 በመቶ የሚሆኑ እናቶች ከደም መፍሰስ ጋር በተያያዘ በየዓመቱ ህይወታቸው እንደሚያልፍና ለዚህም ችግር መፍትሄ ይሆን ዘንድ የብሔራዊ ደም ባንክ አገልግሎት ከደም ለጋሾች ጋር በመተባበር እየሠራ መሆኑ ተገለፀ:: ይህ የተገለፀው የብሔራዊ ደም ባንክ አገልግሎት “የሚዲያ ተቋማት አስተዋፅኦ በበጐ ፈቃድ የደም ልገሳ መበራከት ዙሪያ” በሚል ለመገናኛ ብዙሃንና ለኮሙኒኬሽን ባለሙያዎች በአዳማ ከተማ ባዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ ነው::

በፕሮግራሙ ላይ ተገኝተው የውይይት ሃሳቦችን ያቀረቡት በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የብሔራዊ ደም ባንክ አገልግሎት ዳይሬክተር ዶክተር ዳንኤል ገ/ሚካኤል እንደተናገሩት፤ የዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት ባወጣው መረጃ መሠረት በአንድ ሀገር ውስጥ ከአጠቃላዩ የህዝብ ቁጥር አንፃር አንድ በመቶ የሚሆነው ደም መለገስ አለበት ቢልም፤ ሀገራችን አላት ከሚባለው 90 ሚሊዮን ህዝብ አንፃር በዓመት 900 ሺህ ዩኒት ደም መሰብሰብ ነበረበት ያሉ ሲሆን፤ አሁን ባለበት ሁኔታ ግን በደም ባንኮች ያለው ስብስብ 88 ሺህ ዩኒት ወይም 10 በመቶ ብቻ መሆኑን አስረድተዋል:: ይህም በመሆኑ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች እናቶች ከደም መፍሰስ ጋር በተያያዘ መሞታቸው ተጠባቂ ነው፤ ይህንም ለመቀነስ በእጅጉ መስራት እንደሚገባ አሳስበዋል::

**በብሔራዊ ደረጃ 25 የሚደርሱ የደም ባንኮች መኖራቸውን የተናገሩት ዶ/ር ዳንኤል ገ/ሚካኤል፣ እነዚህ የደም ባንኮች እስከ 400 ሺህ ዩኒት ደም በዓመት የመሰብሰብ አቅም አላቸው ብለዋል**

በብሔራዊ ደረጃ 25 የሚደርሱ የደም ባንኮች መኖራቸውን የተናገሩት ዶ/ር ዳንኤል ገ/ሚካኤል፣ እነዚህ የደም ባንኮች እስከ 400 ሺህ ዩኒት ደም በዓመት የመሰብሰብ አቅም አላቸው ብለዋል:: አሁን ባለው ሁኔታ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከ200 ሺህ እስከ 250 ሺህ ዩኒት የደም ፍላጐት መኖሩን ገልፀው፤ ባለፈው ዓመት 88 ሺህ ዩኒት ደም መሰብሰቡንና በያዝነውም ዓመት እስከ 160 ሺህ ዩኒት ደም ለመሰብሰብ መታቀዱን አስረድተዋል::

በውይይት መድረኩ ላይ የሚዲያና የኮሙኒኬሽን ባለሙያዎች ግንዛቤን ከማስረጽ አኳያ ብዙ መስራት እንደሚጠበቅባቸው የተጠቆመ ሲሆን፤ በአገር አቀፍ ደረጃ ህዝባችን ደም የመለገስ ባህሉ ደካማ መሆኑን የጠቀሱት ዶክተር ዳንኤል፤ ከ2ሺህ 500 እስከ 3ሺህ የሚደርሱ ቋሚ ደም ለጋሾች ቢኖሩም በቂ አይደሉም ብለዋል:: ይህንንም ቁጥር ለማሻሻልና የደም ለጋሾችን ለመጨመር እንደ እንቅፋት ከተጠቀሱት ምክንያቶች መካከል አንዳንዶች ደም ከለገሱ የሚጐዱ ስለሚመስላቸው፣ መርፌን ፍራቻ፣ የግንዛቤና የተሳሳተ አመለካከት መኖሩ ለደም ለጋሾች እጥረት እንደዋነኛ መንስኤዎች ናቸው ተብለው ተጠቅሰዋል::■




# በአምስት ዓመቱ ሕፃን ላይ የግብረ-ሰዶም ጥቃት የፈፀመው በ20 ዓመት እሥራት ተቀጣ

በአሸናፊ ደምሴ

አስራ ሦስት ዓመት ባልሞላው ሕፃን ላይ የግብረ ሰዶም ጥቃት ፈፅሟል ሲል የፌዴራሉ ዐቃቤ ሕግ ክስ የመሠረተበት የ23 ዓመቱ ወጣት ሳሙኤል መርዕድ ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ በ20 ዓመት እሥራት እንዲቀጣ የፌዴራሉ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት 7ኛ ወንጀል ችሎት ከትናንት በስቲያ ታህሳስ 13 ቀን 2007 ዓ.ም የቅጣት ውሳኔ አስተላለፈበት::

ዐቃቤ ሕግ ለፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት 7ኛ ወንጀል ችሎት በየካቲት 06 ቀን 2006 ዓ.ም ባቀረበው ክስ ላይ እንደዘረዘረው፤ የ23 ዓመቱ ወጣት ከእርሱ ጋር አንድ አይነት ፆታ ባለውና ዕድሜው ከ13 ዓመት በታች በሆነው ታዳጊ ልጅ ላይ የግብረ-ሰዶም ጥቃት ለማድረስ አስቦ ተንቀሳቅሷል ይላል:: በዚህም መሠረት በጥቅምት 24 ቀን 2006 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 8:00 ሲሆን በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/02/03 ክልል ልዩ ቦታው ጌሾ ተራ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ እድሜው አምስት ዓመት በሆነው የግል ተበዳዩን ህጻን ኳስ ከሚጫወትበት ሜዳ ላይ ጠርቶ፤ ጭር ወዳለና ሰው ወደማይዘዋወርበት ቦታ በመውሰድ ሱሪውን አውልቆ የግብረ-ሰዶም ጥቃት ፈፅሞበታል ሲል ያትታል::

በዚህም ሳያበቃ ተከሳሽ የ5 ዓመቱን የግል ተበዳይ ህዳር 1 ቀን 2006 ዓ.ም ከቀኑ 6:00 ሰዓት ሲሆን ከላይ በተጠቀሰው ቦታ ተመሳሳዩን የግብረ-ሰዶም ጥቃት በህፃኑ ላይ ሊፈፅምበት ሲሰናዳ ሰው ደርሶ ያስጣለው በመሆኑ በፈፀመው ለአካለ መጠን ባልደረሱ ልጆች ላይ የሚፈፀም የግብረ-ሰዶም ጥቃት ወንጀል ክስ ተመስርቶበታል ይላል::

የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት 7ኛ ወንጀል ችሎትም፣ የዐቃቤ ሕግን ክስ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች መርምሮ ሲያበቃ፤ ተከሳሹ የተመሰረተበትን ክስ በሚገባ ሊከላከል ባለመቻሉ ታህሳስ 8 ቀን 2007 ዓ.ም ጥፋተኛነቱ ተረጋግጧል::

በዚህም መሠረት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት ያዳመጠው ችሎቱ፤ ተከሳሽ ምንም ዓይነት የቅጣት ማቅለያ አለማቅረቡን እና ዐቃቤ ሕግ በበኩሉ ድርጊቱ በተደጋጋሚ ጊዜ የተፈፀመ ስለመሆኑ በመጥቀሱ የቅጣት ማክበጃ በማቅረቡ፤ የወንጀሉን መካከለኛ ደረጃነት በአንድ እርከን ከፍ አድርጎታል:: በመሆኑም ተከሳሹ ዕድሜው 13 ዓመት ባልሞላው እና የአምስት ዓመት ዕድሜ ባለው ህጻን ልጅ ላይ በፈፀመው የግብረ-ሰዶም ጥቃት ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ በ20 ዓመት እስራት እንዲቀጣ ሲል ችሎቱ የቅጣት ውሳኔ አስተላልፏል::

# በባህርዳር ሰልፍ ለጥቃት የተጋለጡ ወገኖች ጉዳይ እንዲጣራ አራት ፓርቲዎች ጠየቁ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በባህርዳር ከተማ ለልማት ተፈልጓል የተባለ ቦታን ታቦት የምናወጣበት ነው በሚል ተቃውመው ሰልፍ በወጡ ዜጎች ላይ የደረሰውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት አራት የፓለቲካ ፓርቲዎች በማውገዝ ጉዳዩ በአስቸኳይ እንዲጣራ ጠየቁ::

ሰማያዊ ፓርቲን ጨምሮ ዘጠኝ የፖለቲካ ድርጅቶችን ያቀፈው ትብብር ባወጣው መግለጫ የባህርዳር ከተማዋ ነዋሪዎች ባዶ እጃቸውን ሆነው በሰላማዊ መንገድ ባሰሙት የተቃውሞ ድምጽ መንግስት የህዝቡን ጥያቄ ለማፈን በወሰደው ዘግናኝና አሰቃቂ በጥይት የታገዘ የኃይል እርምጃ እስካሁን የአምስት ንፁኃን ዜጎች ህይወት መቅጠፉን አስታወሶ፣ ቤተክርስቲያን አገልጋይ የሆኑ አዛውንት እማሆይንና አካል ጉዳተኛ ጨምሮ በርካቶችን በማቁሰል የአካል ማጉደል ማድረሱ፣ በምንም መለኪያና ሁኔታ፣ የሞራል መከራከሪያ ሊቀርብለት የማይችል ህገወጥና ኃላፊነት የጎደለው "መንግሥት ነኝ" ከሚል አካል የማይጠበቅ ዘግናኝ የአረመኔ ተግባር ነው ብሏል:: የኃይል እርምጃው እስከዛሬ "ይህ መንግሥት የማን ነው፣ የቆመውስ ለማን ነው?" ለሚለው ተደጋጋሚ ጥያቄ "የሥልጣኑና ለሥልጣኑ ብቻ" መሆኑን በግልጽ ያሳየበትና በህገ አራዊት ስለመመራቱ የማያሻማ ምላሽ የሰጠበት በመሆኑ፣ ትብብሩ እርምጃውን ከማውገዝ አልፎ፣ የተወሰደው እርምጃ እንዲፈጸም ትዕዛዝ በሰጡ ባለሥልጣናትና እርምጃ በወሰዱት ላይ ተገቢው ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ፣ ለተጎጂዎችና ቤተሰቦቻቸው ካሳ እንዲከፈል ጠይቋል::

የኢትየጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ በበኩሉ የኢህአዴግ አገዛዝ በሰላማዊ አግባብ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ ባደረጉ የባሕር ዳር ከተማ ነዋሪ በሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤቴክርስቲያን እምነት ተከታዮች ላይ ታህሳስ 10 ቀን 2007 ዓ ም የወሰደውን ጭካኔ የተሞላበት የኃይል እርምጃ አውግዟል:: አገዛዙ ሕገመንግሥታዊ የመቃወም መብታቸውን በሰላማዊ አግባብ ለመጠቀም በሞከሩ ሰላማዊ ዜጎች ላይ የሕይወት ማጥፋትና የአካል መጉደልን ጨምሮ የተወሰደው ይህ የኃይል እርምጃ ቀደም ሲልም የሌሎች ሀይማኖቶች ተከታይ በሆኑትና በተለያዩ አካባቢዎች በሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ላይ በተደጋጋሚ ሲፈጸም የቆየ በመሆኑ የሥርዓቱን ኃላፊነት የጎደለው አምባገነናዊ ባሕሪይ ገላጭና በምንም መልኩ ተቀባይነት የሌለው ስለሆነ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ተባብሮ ሊታገለው የሚገባ መሆኑን መድረክ ያምናል::

በዚሁም መሠረት በዚህ ኃላፊነት በጎደለው አምባገነናዊ እርምጃ በዜጎቻችን ላይ ለደረሰው ጉዳት የኢህአዴግ አገዛዝ ኃላፊነት ወስዶ በጥቃቱ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖቻችን በአስቸኳይ ካሳ እንዲከፍልና ጥቃቱን የፈጸሙ ወንጀለኞችን ለፍርድ እንዲያቀርብ መድረክ ጠይቋል::

**ፓርቲው አያይዞም ይህ አይነቱ ድርጊት ሕገ-መንግሥታዊ ያልሆነ ተግባር ነው ብሏል**

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) ታህሳስ 10 ቀን 2007 ዓ.ም ባወጣው መግለጫ በመንግስት የጸጥታ ሃይሎች የተወሰደውን እርምጃ በማውገዝ ኢህአዴግ ቤተ እምነቶችን በየምክንያቱ መዳፈር የጀመረው ዛሬ አይደለም ብሎአል:: ገዥው ፓርቲ ከአሁን በፊት በሙስሊሙ ህብረተሰብ ላይ የፈፀመው ግፍና ያፈሰሰው ደም ሳይደርቅ አሁን ደግሞ በባህር ዳር ከተማ የኦርቶዶክስ ኃይማኖት ተከታዮች ላይ የወሰደው የኃይል እርምጃ ለሰው ህይወት መጥፋትና ለአካል መጉደል ምክንያት በመሆኑ እነዚህ ወንጀሉን የፈፀሙ፣ ያዘዙና ያስፈፀሙ አካላት በየደረጃው በህግ ፊት ቀርበው እንዲጠየቁ ለማድረግ አስፈላጊውን ትግል እንደሚያደርግ አስታውቋል::

ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ በበኩሉ ኢህአዴግ በአማራ ክልል የኦርቶዶክስ ምዕመናን በጠየቁት ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ጥያቄ በጦር ማሣሪያ ምላሽ መሰጠቱ የዜጎችን ሕገ-መንግሥታዊ መብት እና ዓለም አቀፋዊ ሕግ ያልተከተለና አምባገነንነቱን የሚጠቁም ነው ብሏል:: መንግሥት ህጋዊ እርምጃ እንዲወስድም ፓርቲው ጠይቋል::

ፓርቲው ከትናንት በስቲያ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳሳወቀው፣ ገዢው ፓርቲ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ሕገ-መንግስታዊ መርሆዎችን በመጣስ የዜጎች ፍትሓዊና አስተዳደራዊ ጥያቄ በሰላማዊ መንገድና በውይይት መፍታት ሲችል በጠመንጃ አፈሙዝ ህዝቡን ለማንበርከክ እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ አግባብነት የሌለውና ሊወገዝ የሚገባው ተግባር መሆኑን ያመለክታል:: ፓርቲው አያይዞም ይህ አይነቱ ድርጊት ሕገ-መንግሥታዊ ያልሆነ ተግባር ነው ብሏል::

በባህርዳር ከተማ እና በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ዜጎች መብታቸውን በሰላማዊ ሰልፍ በመጠየቃቸው በመንግሥት ኃይሎች በተወሰደባቸው የጥይት እሩምታና ግድያ ጉዳት እየደረሰባቸው በመሆኑ ከፍተኛ ሀዘን እንደተሰማው የገለፀው ፓርቲው፤ ጉዳት ለደረሰባቸው ቤተሰቦች መንግሥት እንደ ጉዳቱ መጠን ካሳ እንዲከፍላቸው እና ድርጊቱን በፈፀሙ ኃይሎች ላይም በአስቸኳይ አጣርቶ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወስድ ጠይቋል::

መንግሥት እንደመንግሥት ያወጣውን ሕገ-መንግሥትና የህግ የበላይነት እንዲሁም የዜጎች ሰብዓዊ መብትን ሊያከብር እንደሚገባው የገለፀው ፓርቲው፣ በሀገራችን ህዝባዊ ስብሰባዎችና ሰላማዊ ውይይቶችን መንግሥት ሊያበረታታ ካልቻለ ግን በዚህ ዓመት የሚደረገው አገር አቀፍ ምርጫ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ መሆኑን አስታውቋል::

ጠ/ሚኒስትር ኃ/ማርያም ደሳለኝ ከትላንት በስቲያ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ በባህርዳር የተከሰተው ሁኔታ መንግስት ተገቢውን ማጣራት እንደሚያደርግ መናገራቸው ይታወሳል::■

## የኢትዮጵያ ዓመታዊ የነዳጅ...

የሚሆነውን የውጪ ምንዛሪ ለነዳጅ ግዢ የምታውል መሆኑን የገለፁት ባለሙያው፤ መንግስት ኤክስፖርቱን ከማጠናከር ይልቅ ከውጪ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዲያስፖራዎች በሚገኝ ገቢ ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑን ገልፀዋል::

ከኤክስፖርት ገቢው በላይ ውጪ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የሚላከው የውጪ ምንዛሪ ከፍተኛ መሆኑን የገለፁት ባለሙያው፤ መንግስት ዲያስፖራውን በተለይም በቤት ልማት ፕሮግራሞቹ ላይ በማሳተፍ በዚህ አቅጣጫ የሚገኘውን ገቢ ማጠናከሩን የመረጠ በሚመስልበት ደረጃ የቀጠለ መሆኑን ገልፀዋል::

በአሁኑ ሰዓት የነዳጅ ዋጋ በዓለም አቀፍ ደረጃ መቀነሱ እንደአገር እንደዚሁም በኢቦላ ወረርሽኝ ስጋት ጉዳት እየደረሰባቸው ካሉት የአፍሪካ አየር መንገዶች መካከል አንዱ የሆነውን የኢትዮጵያ አየር መንገድ በከፍተኛ ደረጃ የሚጠቀም መሆኑን ባለሙያው ገልፀዋል:: ከዚህ ውጪ ግን ነዳጅ ዋጋ እየወረደ መሄድ በተለይ ለኢትዮጵያ የባቡር ፕሮጀክት አበዳሪ ለመሆን ፍላጎት ያሳየችውን የሩስያን አኮኖሚ ክፉኛ እየጎዳ በመሆኑ በዚህ በኩል የታሰበውን ብድር አሳሳቢ የሚያደርገው መሆኑን ባለሙያው ጨምረው ገልፀዋል::

ኢትዮጵያ በኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት በኩል ቤንዚን፣ ጄትኤ ኬሮሲን፣ ነጭ ናፍጣ፣ ቀላል ጥቁር ናፍጣና ከባድ ጥቁር ናፍጣን በፈሳሽ ነዳጅነት ከውጪ የምታስገባ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ለሲሚንቶ ፋብሪካዎች ለኢነርጂ ግብአትነት የሚያገለግል የድንጋይ ከሰልንም ታስገባለች:: ለዚህም ከ2መቶ ሚሊዮን ብር በላይ በየዓመቱ ወጪ ይደረጋል::

የአገሪቱን ከፍተኛ የውጪ ምንዛሪ መጠን እየወሰደ ያለው ነዳጅ መሆኑን የገለፁልን አንድ የንግድ ሚኒስቴር ኃላፊ፤ ኢትዮጵያ ከኤክስፖርት ከምታገኘው ገቢ አንፃር ለነዳጅ የምታወጣው ገቢ መጠን ከፍተኛ ቢሆንም ከኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ከውጪ ከሚኖሩ ኢትዮጵያን የሚላከው ገንዘብ፣ ከባንኮች የሀዋላ አገልግሎት እንደዚሁም ከቱሪዝም የሚገኙት የገቢ መጠኖች ተደማምረው የተወሰነ ድጋፍ የሚያደርጉ መሆኑን ገልፀውናል:: ሆኖም የአንድን አገር የውጪ ምንዛሪ ገቢን የአገልግሎት ዘርፍ ላይ ማንጠልጠል ስለማይገባ በሚላኩ ምርቶች ላይ ላለው ገቢ ትኩረት ሊደረግ እንደሚገባ ኃላፊው ጨምረው ገልፀዋል::

## የአዲስ አበባ ትራንስፖርት...

ዋና የሥራ ሂደቶች ነበሩ:: ይሁንና የከተማዋ አጠቃላይ የትራንስፖርት እንቅስቃሴ በከፍተኛ ደረጃ እየሰፋ በመሄዱ አደረጃጀቱን በሥራ ሂደት ደረጃ ወስኖ ማስቀመጡ ብዙም ወደፊት ማስኬድ ስላልተቻለ አደረጃጀቱን መቀየሩ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ መሆኑን አቶ ውድነህ ጨምረው ገልጸውልናል::

በአዲሱ አደረጃጀት መሰረት የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ጉዳዮች ባለስልጣን፣ የህዝብ ትራንስፖርት ባለስልጣን እንደዚሁም የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ የሚባሉ አዳዲስ ተቋማት ይኖራሉ:: እንደ ኃላፊው ገለፃ ተቋማቱ በተዋረድ ምን አይነት አደረጃጀት እንደሚኖረቸው እና የሚይዙትን የሰው ኃይል ሁኔታ ለመወሰን ባለሙያዎች ሰሞኑን በደብረዘይት የሥራ አመራር ኢኒስቲቲዩት ገብተው ሰፊ ሥራ በመስራት ላይ ናቸው:: የኃላፊዎቹን ለውጥ በተመለከተ የከንቲባው ጽህፈት ቤት ያከናወነው መሆኑ ታውቋል::

የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ እየሰፋ ካለው የከተማዋ ትራንስፖርት እንቅስቃሴ አኳያ ሥራውን በሚገባ መወጣት አልቻለም የሚሉ ወቀሳዎች ሲሰነዘሩበት ቆይተዋል:: ሲደርሱበት ከነበሩት ወቀሳዎች መካከል ከአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ቁጥጥርና ክትትል ጋር በተያያዘ እንደዚሁም የትራንስፖርት አቅርቦትና ቁጥጥርም ጋር በተያያዘም ኃላፊነቱን በሚገባ ሊወጣ አልቻለም በሚል ነው:: በርካታ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት የትራንስፖርት ሚኒስቴርም የአፈፃፀም ግምገማ ሳያሟሉ ለአሽከርካሪዎች ሥልጠና ሲሰጡ የቆዩ ሲሆን ቢሮው እርምጃውን የወሰደው ዘግይቶ መሆኑ በበርካቶች ዘንድ ሲያስወቅሰው ቆይቷል:: ከዚሁም በተጨማሪ ከሌሎች የከተማዋ ቢሮዎች ጋር በመተባበር የትራፊክ ፍሰትን የሚያውኩ የጎዳና ላይ ንግዶች፣ ሕገወጥ የፓርኪንግ ሥርዓቶች፣ የመንገድ ላይ ተሽከርካሪ እጥበቶችን፣ የመንገድ ላይ ጋራዦችን በሚገባ መከላከል አልቻለም የሚሉ ወቀሳዎች ሲቀርቡበትም ቆይቷል:: ከዚህም በተጨማሪ በተለይ በሥራ መውጫና መግቢያ ሰዓቶች ያለውን የከተማዋን የትራንስፖርት አቅርቦት ችግር መፍታት አለመቻሉም እንደአንድ ችግር ሲነሳ ቆይቷል::




# ተጨማሪ ኢንቨስትመንቶችን እየሰራ ያለው
# ካስትል ወይን ጠጅ

በፀጋው መላኩ

ኢትዮጵያ በወይን ጠጅ ምርት ረዘም ያሉ ዓመታትን ብታስቆጥርም አገሪቱ ካላት ተፈጥሯዊ እምቅ አቅም አኳያ ግን ብዙም ርቀት የተጓዘችበት ሁኔታ የለም። ቀደም ሲል በግለሰብ ባለሀብቶች እጅ የነበሩት የወይን ጠጅ አምራች ኩባንያዎች በደርግ መንግሥት ከተወረሱ በኋላ በዘርፉ ደፍሮ የገባ የግል ባለሃብት አልነበረም። ይሁንና በኢትዮጵያ በቢራ ማምረት ሥራ የተሰማራው የፈረንሳዩ ካስትል ኩባንያ ደፍሮ በመግባት ከአዲስ አበባ 160 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ዝዋይ ከተማ አቅራቢያ ከ2008 ጀምሮ የወይን ጠጅን በማምረት ላይ ይገኛል። ኩባንያው ምርቶቹን ለአገር ውስጥ ገበያ ከማቅረብ ባለፈ ለውጪ ገበያ ኤክስፖርት በማድረግም ላይ ነው። ከሰሞኑ በርካታ ጋዜጠኞች በቦታው በመገኘት የወይን ጠጅ ፋብሪካውን እንደዚሁም በአዋሳ የሚገኘውን የቢጂአይ የቢራ ፋብሪካም ጎብኝተዋል።


ካስትል ኩባንያ በዝዋይ ፋብሪካው ዘጠኝ አይነት የወይን ጠጅ ምርቶችን ያመርታል። የምርቶቹ አይነቶች አኬዥያ ድራይ ሬድ፣ አኬዥያ ሚዲየም ሰዊት ኋይት፣ አኬዥያ ሚዲየም ሰዊት ሬድ፣ ሪፍት ቫሊ ሜርሎ፣ ሪፍት ቫሊ ሻርዶኔ፣ ሪፍት ቫሊ ከበርኔት ሶቪኒዮ፣ ሪፍት ቫሊ ሲራ ተብለው የሚጠሩ የወይን ጠጅ ምርቶችን የሚያመርት ሲሆን፤ ከዚህም በተጨማሪ ከእያንዳንዱ የወይን ዛፍ አንዳንድ ዘለላ በልዩ ሁኔታ ተመርጠው ከሚሰበሰቡ የወይን ዘለላዎች የሚመረቱ ሁለት የወይን ጠጅ ምርቶችንም ያመርታል። እነዚህ ሁለት አይነት ምርቶች ፐሪስቲጂኒየስ ወይን በመባል የሚታወቁ ሲሆን ለሸራተን አዲስ ሆቴል እንደዚሁም ለኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ መስተንግዶ አገልግሎት የሚውሉ መሆኑ ታውቋል።

በአውሮፓ የወይን እርሻዎች ወይንን ማምረት የሚቻለው በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነው። እንደባለሙያው ገለፃ ለዚህም ምክንያቱ ከአንድ ወቅት (Season) በላይ የአብዛኛው አውሮፓ ወቅት በረዶአማ በመሆኑ ነው። ከኢትዮጵያ የአየር ሁኔታ አንፃር ግን ወይንን በዓመት ሁለት ጊዜ ማምረት የሚቻልበት ሁኔታ መኖሩ ተመልክቷል።

ይህንንም ተከትሎ የካስትል የወይን ጠጅ ምርቶችንም በዓመት ሁለት ጊዜ ማምረት የሚቻልበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር። ሆኖም ከውጪ የገባው የወይን አትክልት ዝርያ ከአርባ አምስት ዓመት እስከ ሀምሳ ዓመት እየተገረዘ የሚያገለግል በመሆኑ በዓመት ሁለት ጊዜ ምርቱን መሰብሰቡ በወይን ዝርያው ላይ ጫናን ሊያሳድር ይችላል ተብሎ በመታሰቡና እንደዚሁም የምርቱን የጥራት ደረጃ ለመጠበቅ ሲባል ምርቱ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ እንዲሰበሰብና እንዲመረት የተደረገ መሆኑን ኃላፊዎቹ ገልፀውልናል።



**ካስትል ወይን በአሁኑ ሰዓት በ162 ሄክታር የወይን አትክልት ልማትን እያካሄደ ሲሆን፤ በቀጣይም በሚኖረው የማስፋፋት ስራ አንድ መቶ ሄክታር የእርሻ ቦታን በመጨመር ከበርኔረት ፍራንስ፣ ማልቤክና ሶቪኒዮ የተባሉ የወይን ዝርያዎችን ከውጪ አስመጥቶ ለመትከል በዝግጅት ላይ ነው።**





የወይን አትክልት ዝርያዎቹ በኢትዮጵያ የሚገኙ ሳይሆኑ ከውጪ በተለይም ከፈረንሳይ የሚገቡ ናቸው። ከባለሙያዎቹ ገለፃ መረዳት እንደቻልነው በአሁኑ ሰዓት የወይን አትክልት የስሩ የዝርያ አይነትና ከዚያ በላይ ያለው አትክልቱ ክፍል ዝርያ የተለያዩ ናቸው። ለዚህም ምክንያቱ በአንድ ወቅት በዓለም ላይ ፍሎግዜራ የተባለ አፈር ወለድ የወይን በሽታ ተከስቶ የወይንን ዘር ከምድረ-ገፅ እስከማጥፋት ደረጃ መፈታተኑ ነው።

በዚህ ወቅት ግን ከሁሉም የወይን ዘሮች በተለየ ሁኔታ አንድ ወይን ዝርያ አይነት በሽታውን መቋቋም በመቻሉ የሱ ዘር ነው ለወይኑ ስርነት በማገልገል ላይ ያለው። ወይኑ በተገረዘ በአምስት ወራት ጊዜ ውስጥ ምርቱ ደርሶ የሚሰበሰብ ሲሆን የሚሰበሰብበት ጊዜም በየካቲትና በመጋቢት አካባቢ ነው። ከምግብና መጠጥ ደህንነት አኳያ ከምርቱ ተከላ ጀምሮ ያለው ሂደት ከብረት ንክኪ ነፃ ነው። ወይኑ የሚገረዘው ስቴይኒለስ ስቲል በሆነ መቀስ ሲሆን በተመሳሳይ መልኩም የምርት ስብሰባውም ሆነ የተጠመቀው ወይን በጠርሙስ ከመታሸጉ በፊት የሚቀመጥበት እቃም እንደዚሁ ከብረት ንክኪ ነፃ ነው። የእርሻው ኢንቬስትመንት ብቻ እስከ አንድ መቶ ሃምሳ ሚሊዮን ብር የኢንቬስትመንት ወጪን ጠይቋል።

እ.ኤ.አ በ2008 በነበረው ዋጋ አንድ የወይን ችግኝ 26 ብር ይሸጥ የነበረ ሲሆን፤ አሁን ግን በየጊዜው የዶላር ዋጋ እየናረ ከመሄዱ ጋር በተያያዘ የአንዱ ችግኝ ዋጋ ወደ አርባ ሶስት ብር የደረሰ መሆኑን ከባለሞያዎቹ ገለፃ መረዳት ችለናል። ካስትል ወይን በአሁኑ ሰዓት በ162 ሄክታር የወይን አትክልት ልማትን እያካሄደ ሲሆን፤ በቀጣይም በሚኖረው የማስፋፋት ስራ አንድ መቶ ሄክታር የእርሻ ቦታን በመጨመር ከበርኔረት ፍራንስ፣ ማልቤክና ሶቪኒዮ የተባሉ የወይን ዝርያዎችን ከውጪ አስመጥቶ ለመትከል በዝግጅት ላይ ነው። ካስትል የወይን ጠጅ በአሁኑ ሰዓት ለዩኒቨርስቲዎች የመስክ ምርምር አገልግሎት ጭምር እየሰጠ ሲሆን፤ በርካታ ተማሪዎችንም በስራ ላይ ልምምድ (Apparentship) ተቀብሎ በማስተናገድ ላይ ነው።

በገፅ 21




# ኢትዮጵያ በምግብ ዋስትና ረገድ ቀሪ የቤት ሥራዎቿ ምንድን ናቸው?

- ስለምግብ ዋስትና በአጭሩ. . .
- በቀጣይ ዓለም በምግብ ዋስትና የሚፈተንባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች፣
- ኢትዮጵያ በዓለም አቀፉ የምግብና እርሻ ድርጅት /ፋኦ/ በምን መስፈርት ተመርጣ ተሸለመች?

በበላይ ከአዳማ

የእርሻ ሥራ የዛሬ 10ሺ ዓመት እንደተጀመረ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: በወቅቱ ጥንታዊ የስልጣኔ ሀገራት የሆኑት የግብጽና የቻይና ህዝቦች የዕለት ጉርሳቸውን ለማግኘት ይታትሩ ነበር:: ይሁንና መሬት አንድ ጊዜ የሰጧትን ዛቅ አድርጎ የተትረፈረፈ ምርት እንደምትሰጠው ሁሳ ባዶ እጅ የምታስቀርበትም ጊዜ ነበር:: እናም የሁለቱ ሀገራት ነገስታት በተለይ ከዕለት ጉርስ የተረፈውን ምርት ለነገ ክፉ ቀን በሚል ከዚያም ከዚህም ቆንጥረው ያስቀምጡና የምግብ እጥረት ሲከሰት መልሰው ለዜጎቻቸው በማከፋፈል ከረሀብ ይታደጓቸው ነበር:: ይህ ሁኔታ ግብጽና ቻይናን ጨምሮ በሌሎችም አንዳንድ ሀገራት የዜጎቻቸውን የምግብ ዋስትና የሚያረጋግጡበት አንዱ መንገድ ሆኖ ለብዙ ዓመታት እንደዘለቀ ይነገራል::

- ስለምግብ ዋስትና ባጭሩ. .

የምግብ ዋስትና ትርጓሜ በዓለም የማህበረሰብ እድገትና የለውጥ ሂደት ውስጥ የተለያዩ ፍቺዎችን አስተናግዷል:: አስቀድመን እንዳነሳነው በጥንታዊዎቹ ግብጽና ቻይና አንደኛው የህዝቦቹ የምግብ ዋስትና ማረጋገጫ መንገድ የሁለቱ ሀገራት ነገስታት በትርፍ ምርት ወቅት ያከማቹትን በችግር ጊዜ መልሰው ለተራበው በማከፋፈል ነበር:: ይህ በእርግጥ አሁንም ቢሆን መልኩን ቀየር አድርጎ ተግባራዊ እየሆነበት ያለባቸው ሁኔታዎች በአንዳንድ ሀገራት መስተዋሉ አልቀረም:: ይሁንና እ.ኤ.አ. ከ1970ዎቹ ወዲህ በተባበሩት መንግሥታት ስር አንድክንፍ ሆኖ የተቋቋመውና መቀመጫውን ሮም ያደረገው የአለም የምግብና እርሻ ድርጅት /FAO/ ቢያንስ የምግብ ዋስትና ምንነት በዓለም ገቢ ሀገራት ወጥ የሆነ ትርጓሜ እንዲኖረው አስተዋውቋል:: እናም ፋኦ አንድ ሰው፣ ቤተሰብ፣ አካባቢ፣ እንዲሁም ክልል፣ ሀገር አህጉርና ዓለም የምግብ ዋስትናቸውን አረጋግጠዋል የሚባለው መቼ ነው? ምንስ ተሟልቶ ሲገኝ ነው ለሚለት ጥያቄዎች ዝርዝር ያሉ ምላሾችን አስቀምጧል::

በዚሁ መሰረት በተለያዩ ደረጃዎች የምግብ ዋስትና ተረጋገጠ የሚባለው ሁሉም ሰው፣ በፈለገው ጊዜ ለሰውነቱ ተስማሚና ለጤናው መሟላት አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ እና የተመጣጠኑ ምግቦን መርጦ ማግኘት እንዲሁም መግዛት ሲችል ነው:: ይህም አስፈላጊው የምግብ አቅርቦት ኖሮም ዜጎች የግድ የምግዛት አቅም /purchasing power/ ሊኖራቸው እንደሚገባ ያመለክታል:: እናም በአንድ ሀገር የቱንም ያህል የተትረፈረፈ ምርት እንኳን ቢኖር ዜጎች የመግዛት አቅም ከሌላቸው በዚያች ሀገር የምግብ ዋስትና ሙሉ በሙሉ ተረጋግጧል ማለት አይቻልም::

- ኢትዮጵያ በዓለም አቀፉ የምግብና እርሻ ድርጅት /ፋኦ/ በምን መስፈርት ነው ተመርጣ የተሸለመችው? ቀሪ የቤት ሥራዎቿስ ምንድን ናቸው?

ከሰሞኑ በጣልያኗ ርዕሰ መዲና ሮም አንድ የዕውቅናና የሽልማት ስነሥርዓት ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ነበር:: የዚህ ፕሮግራም ዓላማ ደግሞ እ.ኤ.አ. ከ1990 — 2015 ባሉት ጊዜያት የተቀመጠውን የምዕተ ዓመቱን የልማት ግብ ያሳኩ ሐገራትን መርጦ ማሳወቅና ለተሸላሚነት ማብቃት ነበር:: ለመሆኑ እነዚህ በሶስት ምዕራፍ የተከፋፈሉት የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ማጠንጠኛቸው ምንን መሰረት ያደረጋል ወደሚለው ስናልፍ አስቀድመን የምናገኘው ሀገራት ዜጎቻቸውን ከአስከፊ ድህነት ውስጥ ለማውጣት ያደረጉት ጥረትና ያስመዘገቡት ውጤት ምን ይመስላል የሚለውን ነው:: የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እና ጾታን መሰረት ያደረገ የገቢ ልዩነት ችግርን መቀነስ የሚሉት ሌሎቹ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ናቸው:: የፋኦ መረጃ እንደሚያመለክተው ከሶስቱ ምዕራፎች በአንደኛው ዙር የተቀመጠው ግብ ቀናት በቀሩት የ2015 አዲሱ የፈረንጆች ዓመት በዓለም ላይ ከሚገኙት ከ842 ሚሊዮን በላይ የሆኑ የተመጣጠነ የምግብ እጥረት በከፍተኛ ሁኔታ የሚታይባቸውን ሰዎች ቁጥር በግማሽ መቀነስ ይላል:: ግቡ ከወዲሁ አስቀድሞ የተሳካ መሆኑን ገልጾ አሁንም ቢሆን ግን በዓለም ዙሪያ በሚገኙ ድሃ ሀገራት እድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ቁጥራቸው 94 ሚሊዮን የሚሆኑ ህጻናት አሁንም በተመጣጠነ ምግብ እጦት ይሰቃያሉ:: በዚህም ምክንያት ከአማካይ የክብደት መጠናቸው በታች እንዲሆኑ ግድ ሆኗል::

ኢትዮጵያን በተመለከተ የሀገሪቱ መንግሥታት ግብርና መር የኢኮኖሚ ስትራቴጂ ነድፎ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ከጀመረ ሁለት አስርት ዓመታትን ዘሏል:: በተለይ ላለፉት 11 ዓመታት ሀገሪቱ ላስመዘገበችው ፈጣንና ተከታታይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት ዘርፉ የተወጣው ወይም ያበረከተው ድርሻ በቀላሉ የሚታይ አይደለም:: እተገባደደ ባለው የመጀመሪያው ምዕራፍ የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ የግብርና ዘርፍ ዋና ኢኮኖሚ እድገት ምንጭ ሆኖ እንዲቀጥል እና በየዓመቱም በአማካይ የ8.6 በመቶ እድገት እንዲያስመዘግብ ታቅዶ ሲሰራ ቆይቷል:: እናም ከ2003-2005 ባሉት ሶስት ዓመታት የግብርና ዘርፍ በአማካይ በየአመቱ የ7 በመቶ እድገት ያስመዘገበ ሲሆን የዋና ዋና የምግብ ሰብሎች ምርት ከእቅዱ መነሻ ዓመት ጀምሮ ባሉት ተከታታይ አመታት እየጨመረ መጥቷል:: የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መረጃ እንደሚያመለክተውም በእቅድ አመቱ የነበረው የዋና ዋና ሰብሎች አጠቃላይ የሐገሪቱ ምርት 207 ሚሊዮን ኩንታል ያህል ሲሆን ዘንድሮ አስቀድሞ እንደተተነበየው ይኸው የዋና ዋና የምግብ ሰብሎች የምርት መጠን በከፍተኛ ሁኔታ አድጎ ከ300 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ይደርሳል ሲል መንግሥት አስታውቋል:: በእርግጥ በከፍተኛ እድገት አማራጭ የተያዘውን በ2002 የነበረውን የ202 ሚሊዮን ኩንታል የሰብል ምርት በእጥፍ ለማሳደግ የተያዘው ግብ ሊሳካ አልቻለም:: ያም ሆኖ ሀገሪቱ ከምዕተ አመቱ የልማት ግቦች ከሶስቱ አንዱ የሆነውን የምግብ ዋስትና የማረጋገጥ ሥራ በተጨባጭ አከናውና ተገኝታለች በሚል ነው:: በተባበሩት መንግስታት የአለም የምግብና እርሻ ድርጅት ታጭታ ለእውቅናና ለሽልማት የበቃችው:: በድርጅቱ መቀመጫ ሮም በተካሄደው በዚህ ፕሮግራም ላይ የግብርና ሚኒስትሩ አቶ ተፈራ ደርበው ተገኝተው ከፋኦ ዋና ዳይሬክተር ጆዜ ግራዚያኖ ዳሲልቫ እጅ ዲፕሎማ ተቀብለዋል::

ሽልማቱንም ከተቀበሉ በኋላ ባሰሙት መልዕክት ሐገሪቱ ለግብርና ዘርፍ በሰጠችው የላቀ ትኩረት ምርትና ምርታማት እያደገ መምጣቱን ገልጸው ለተገኘው ውጤትም መንግስት፣ የግብርና ባለሙያዎች፣ እና አርሶ አደሩን አመስግነዋል:: በእርግ ይህ ከሰሞኑ ሀገሪቱ በምግብ ዋስትና ረገድ ያገኘችው አለም አቀፍ ዕውቅና በራሱ እንደ አንድ ጥሩ ስኬት ሊወሰድ ይችላል:: ነገር ግን የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ሂደት የተሟላ ለማድረግ ቀሪ ሥራዎች አሉ:: ይህም አንድ ሀገር በሀገር ደረጃ የምግብ ዋስትናን አረጋገጠች ሲባል ሁሉም ዜጋ በቂና የተመጣጠነ ምግብ አግኝቷል ለማለት አስቀድሞ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች አሉ:: እነዚህም ድህነትን መቀነስና የዜጎችን የመግዛት አቅም ከፍ ለማድረግ ብዙ ሥራዎች መሥራትን ይጠይቃል:: ሌላው የመግዛት አቅሙ እንኳን ተሟላ ቢባል በአስፈላጊው ጊዜ በቅርበት አግኝቶ መሸመት የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችም ሊፈጠሩ ይገባል::

ሁለቱ ያነሳናቸው ነጥቦች ተሟልተው ካልተገኙ የምግብ ዋስትናን በሀገር አቀፍ ደረጃ ብቻ ማረጋገጥ በቂ ሊሆን አይችልም:: በመሆኑም መንግስት በቀጣይ የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚታትረውን ያህል የተጠቀሱትን ቀሪ የቤት ሥራዎችም በአግባቡ መከወን ይጠበቅበታል ማለት ነው:: ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ኢትዮጵያን ጨምሮ አለም በቀጣይ በምግብ ዋስትና ረገድ ፈታኝ ሁኔታዎች እንደተጋረጠባቸው ነው መረጃዎች የሚጠቁሙት እነዚህ ፈታኝ ሁኔታዎች ምንድናቸው? መፍትሄዎቹስ?

- በቀጣይ ዓለም በምግብ ዋስትና የሚፈተንባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች

ፋኦ አንድ ሁለት ብሎ የዘረዘራቸው ዓለምን በቀጣይ በምግብ ዋስትና ረገድ የሚያጋጥሙ ፈተናዎች በዋናነት የሚከተሉት ናቸው:: በዋናነት የውሃ እጥረት የተጠበቀውን ያህል ለማምረት በሚደረግ ጥረት እንቅፋት ስለመሆኑ ይገልፃል:: የህዝብ ቁጥር መጨመርና በአንዳንድ ሀገራት እየተመዘገበ ያለውን የኢኮኖሚ እድገት ተከትሎ የዜጎች የገቢ መጨመርና ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚከሰተው የመሰረታዊ እና የተመጣተነ የምግብ ፍላጎት ማደግ ሌሎች ከፍት ለፈታችን የተቀኑ ስጋቶች ናቸው ይላል:: ዜጎች የየራሳቸው የአመጋገብ ባህል ከመከተል ይልቅ የምዕራባውያንን የአመጋገብ ዘይቤ መከተል በአቅርቦትና በፍላጎት ላይ ከፍተኛ ክፍተት እየፈጠረ ይገኛል ነው የተባለው:: ለአብነትም ከዓለም ህዝብ 3 ቢሊዮን ያህሉ የምዕራባውያንን የአመጋገብ ባህል የሙጥኝ በማለቱ የስጋና ዶሮ ምግብ አቅርቦት ቀላል የማይባል ጫና ፈጥሯል::


ከህዝብ ቁጥር መጨመር ጋር በተያያዘም በቻይና ብቻ በየዓመቱ 8 ሚሊዮን አፎች /Macthus theory/ በዚያች 1ነጥብ 4 ቢሊዮን ህዝብ ባለባት ሀገር ሌላ ምግብ ፈላጊዎች ናቸው:: ያም ሆኖ አሁንም በቻይና በአማካይ አንድ ሰው የሚመገበው የስጋ መጠን በተመሳሳይ ከአሜሪካዊው በግማሽ ያህል ያነሰ ነው:: በውሃ አጠቃቀም ኢፍትሃዊነት ምክንያት ዛሬ ላይ በህንድ 190 ሚሊዮን በቻይና ደግሞ 130 ሚሊዮን የሚሆነው በሞተር ውሃ ስቦ በመስኖ የሚያለማው ህዝብ ከፍተኛ ሽኩቻ ውስጥ ይገኛል::

ችግሩ በተለይ የውሃ እጥረት ሲያጋጥም የተባባሰ ይሆናል:: በዚህም ምክንያት እ.ኤ.አ ከ1950-2000 አስገራሚ በሆነ ፍጥነት በአለም ላይ በመስኖ ልማት የተሳተፈው የህዝብ ቁጥር ከ250 ሚሊዮን በሶስት እጥፍ አድጎ 750 ሚሊዮን ቢደርስም ባለፉት አስር ዓመታት ግን የጨመረው 10 በመቶ ብቻ ሆኗል:: ከዚህም ሌላ ዋነኛ የሩዝ አምራችና ተጠቃሚዎች በሆኑት ጃፓንና ቻይና ምርትና ምርታማነት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አንጻራዊ የእድገት ቅናሽ ማሳየቱ ሌላው የምግብ ዋስትና ስጋት ተብሏል:: በጃፓን እ.ኤ.አ ከ1880 — 1996 በከፍተኛ መጠን ያደገው የሩዝ ምርትና ምርታማት ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ባለበት እየረገጠ ይገኛል:: ከቻይናም ዓመታዊ የሩዝ ምርት ብዙም ፈቅ ሳይል 4 በመቶ ላይ ቀርቷል:: እናም የብዙ ህዝብ ባለቤት በሆኑት ሁለት ሀገራት ዋነና ምግብ የሆነው የሩዝ ምርት መሻሻል ካላሳየ ዳፋው ለሴትም ይተርፋል ነው የተባለው::

ከዓለም የበቆሎ ምርት 40 በመቶውን በምታመርተው አሜሪካም ቢሆን ተመሳሳይ አንጻራዊ የምርትና ምርታማነት ቅነሳ ነው የተስተዋለው:: በስንዴ ምርት አለምን በሚመሩት በካናዳ፣ አርጀንቲና ፈረንሳይ እና ጣልያንም ችግሩ በተመሣሣይ ቀጥሏል:: እነዚህ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እንቅፌት ይሆናሉ ተብሎ ከፍተኛ ስጋት ባለበት ሁኔታ የአለም ባንክ እ.ኤ.አ በ2030 የዓለም ህዝብ 8 ቢሊዮን ይደርሳል ማለቱ ሌላው እንቅልፍ የሚነሳ ጉዳይ ሆኗል:: እናስ መፍትሄው ከወዴት ነው? አዎን ባለሙያዎች የመፍትሄ እርምጃዎቹ የተወሰኑ ግለሰቦችና ሀገራት ብቻ ሳይሆን የመላው አለምን ቁርጠኝነት ይጠይቃል ይላሉ:: የመፍትሄው ዋነኛ ማጠንጠኛ ያሉት ደግሞ በምርትና ምርታነት ላይ ተፅዕኖ እያሳደረ ያለውን የአካባቢ አየር ንብረት መዛባት ችግርን መሰረታዊ በሆኑ ደረጃ መፍታት ያስፈልጋል:: ለዚህ ደግሞ በሚለቁት በካይ ጋዝ መጠን በአካባቢ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚያደርሱ ሀገራ የአንበሳውን ድርሻ ይይዛሉ:: ከዚህ አንጻር ለፖለቲካ ፍጆታነት እና ለኢኮኖሚ የበላይነት በሚል በእርምጃው ላይ የሚስተዋሉ መለስ ቀለሶች ማንንም የማይጠቅም መሆኑን ሊረዱት ይገባል ባይ ናቸው:: የውሃ አጠቃቀምን ማሻሻል ብሎም የተፈጥሮ ሥነ ምህዳርን መንከባከብ ዓለም ከፊት ለፊቷ የተደቀነባትን የምግብ ዋስትና አደጋ ለመከላከል ብሎም ለመቀልበስ ያስችላታልና ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል ይላሉ ባለሙያዎቹ

**ሽልማቱንም ከተቀበሉ በኋላ ባሰሙት መልዕክት ሐገሪቱ ለግብርና ዘርፍ በሰጠችው የላቀ ትኩረት ምርትና ምርታማት እያደገ መምጣቱን ገልጸው ለተገኘው ውጤትም መንግስት፣ የግብርና ባለሙያዎች፣ እና አርሶ አደሩን አመስግነዋል**






# "የክፉ ቀን ደራሿ" አርቲስት

በአሁኑ ወቅት በጣት ከሚቆጠሩትና በሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት ከሚገኙት አንጋፋ ተዋንያን መካከል አንዷ ናት፤ አርቲስት ፍሬህይወት ባህሩ። በ1969 ዓ.ም "ሀ" ብላ ሀገር ፍቅርን ተቀላቀለች። ፍሬሕይወት ከሰራቻቸው የመድረክ ሥራዎች ጉድ ፈላ፣ ቀዩ ማጭድ፣ ታጋይ ሲፋለም፣ የቀለጠው መንደር ረመጥ እና ፎርፌ ጥቂቶቹ ሲሆኑ፤ በፊልም ደግሞ ትውልድ፣ ጉራማይሌ፣ መፈንቅለ ሴቶች፣ አይሁሽ፣ ወራሽና ድባቡ ይጠቀስለታል። ይህም ብቻ ሳይሆን በበርካታ የሬዲዮና የቲቪ ድራማዎቿ ትታወቃለች። ከአንጋፋዋ አርቲስት ፍሬሕይወት ባህሩ ጋር ያደረግነውን አዝናኝ ቆይታ እነሆ፡-

በአሸናፊ ደምሴ

**ሰንደቅ፡- ወደሀገር ፍቅር እንዴት መጣሽ ከሚለው ብንጀመርስ?**

ፍሬህይወት፡- ከትምህርት ቤት በቀጥታ ነው ወደሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት የመጣሁት። በአርበኞች ትምህርት ቤት በስካውት አባልነቴና በሩጫ እታወቅ ነበር። በኋላ ላይ ሀገር ፍቅር ማስታወቂያ ወጥቷል ሲባል ከሰፈር ልጆች ጋር ሄጄ ተመዘገብኩ። ባይገርምህ የተመዝጋቢው ቁጥር ከ500 በላይ የነበረ ቢሆንም ከዚያ መካከል በፈተና ተጣርተን ያለፍነው ግን ወንድ ስምንት፤ ሴት ስምንት በአጠቃላይ 16 ልጆች ነበርን። ያኔ ታዲያ ሁለገብ መሆን አለብህ። ድምፅ ትጫወታለህ፣ ውዝዋዜ ትሰራለህ፤ ትተውናለህ፤ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም መድረክ አስተዋዋቂም ትሆናለህ። እኔ ለብዙ ዓመታት ውዝዋዜውንና ቴአትሩን በጥምረት ስሰራ ቆይቼ፣ ከ15 ዓመታት ወዲህ ግን ሙሉ በሙሉ ወደቴአትር ክፍል ተዛውሬ እየሰራሁ እገኛለሁ።

**ሰንደቅ፡- ፍሬሕይወት በተለየ መልኩ የምትታወቂው ብዙ አርቲስቶችን ተክተሽ ሳትቸገሪ በመስራትሽ ይመስለኛል። ስመሆኑ ምን ያህል ሥራዎችን ተተክተሽ ሰርተሻል?**

ፍሬህይወት፡- ከማስታውሳቸው መካከል ለምሳሌ "ጉድ ፈላ" የተሰኘ ቴአትር ላይ አንዲት "አክተር" ቀርታ ድንገት ተጠርቼ ወጥቼ በደንብ ሰርቻለሁ። "ቀዩ ማጭድ" ቴአትር ላይ ደግሞ አሰለፈች አሽኔ ነበረች የምትሰራው፣ የገበሬ ሚስት ሆና በኋላ ታማ ሆስፒታል ስትገባ እኔ እንድሰራው ተደርጓል። ሦስተኛው "ታጋይ ሲፋለም" የተሰኘ ቴአትር ነው። ይህ ቴአትር የሶማሌን ጦርነት የሚያሳይ፣ ቶክስ እና መገለባበጥ ያለበት ቴአትር ነበር። ይህም ቴአትር የአሰለፈች አሽኔ ነበር በይ እንደጀመርሽው አንቺው ተወጪው ተብዬ ገብቼ ሠርቻለሁ። ሌላው በብዙዎች ዘንድ የሚታውቀው ሙናዬ መንበሩን የተካውበት "የቀለጠው መንደር" ቴአትር ነው። ባይገርምህ ሙናዬ ጓደኛዬም ስለነበረች አብራኝ ነው ብዙ ጊዜ የምትሆነው። በዚህ ምክንያት ቃለ-ተውኔቷን በደንብ አውቀዋለሁ። በዚህ ስራ መድረክ ላይ አብረን ነበርን። ያን ጊዜ ሥራ አስኪያጇ ደውላ "ዛሬ የሙናዬን ቦታ ተክተሽ የምትሰሪው አንቺ ነሽ" ስትለኝ እኔ ሙናዬ ታማ አጠገቧ ነበርኩ።

**ሰንደቅ፡- ቃለ-ተውኔት ለመያዝ አትቸገሪም ማለት ነው?**

ፍሬህይወት፡- ይመስገነው ያኔ ወጣት እና ለስራው በጣም ፍቅሩ ስላለኝ ነው መሰለኝ ተቸግሬ አላውቅም። ሁሉንም ተክቼ ስሰራ አሪፍ ነበርኩ፤ ብዙዎች እንደውም "የክፉ ቀን ደራሽ" ነው የሚሉኝ (ሳቅ) . . . በተለይ

> **ይመስገነው ያኔ ወጣት እና ለስራው በጣም ፍቅሩ ስላለኝ ነው መሰለኝ ተቸግሬ አላውቅም። ሁሉንም ተክቼ ስሰራ አሪፍ ነበርኩ፤ ብዙዎች እንደውም "የክፉ ቀን ደራሽ" ነው የሚሉኝ**

ግን "የቀለጠው መንደር" ሲሰራ እኔና ሙናዬ በመድረክ ላይ የምንሰዳደበው ነገር ብዙ ስለነበር እርስ በእርስ እንተዋወቅ ነበር። በቴአትሩ ላይ ጥናቱ የተወሰነ ሆኖ ድንገቴ ፈጠራ ይበዛው ስለነበር ድንገት መንገድ ላይ ሰዎች ተጣልተው ሲሰዳደቡ ሳይ ማስታወሻ እይዛለሁ፤ ሙናዬም እንደዚሁ ታደርግ ነበር። በኋላ መድረክ ላይ ስንገናኝ በነገር መጠዛጠዝ ነው። (ሳቅ) በመሆኑም የቀለጠው መንደር ብዙም አልከበደኝም። ነገር ግን በሳምንቱ ሙናዬ አረፈች። ያኔ እኔ መሆኔ ታወቀ ማለት ነው፤ ተመልካቹ ቢያዝንም በስራዬ ተደስቶ ነበር።

**ሰንደቅ፡- ብዙዎች በስራዎችሽ ቢያውቁሽም ለጥሪ ጊዜ ኮሚዲያን ናት ይላሉ፤ በዚህ ትስማሚያለሽ?**

ፍሬህይወት፡- ለብዙዎች እምታታባቸዋለሁ። አብዛኞቹ የምሰራቸው ስራዎች የሚያስቁ ስለሆኑ ኮሜዲያን የሚሉኝ አሉ። ነገር ግን ሁለገብ አርቲስት ነኝ ብዬ ነው ራሴን የምገልጸው። ለምን ቢባል የሰጡንን መስራት እችላለሁ።

**ሰንደቅ፡- ብዙ ኮሜዲያን ከሰሯቸው ስራዎች በላይ በቅርቡ በተለቀቀው የ8100**

በገፅ 20



# አንዳንድ

በመስከረም አያሌው

## ተጋፍታ ትግባ

ሚስቱ የሞተችበት አንድ ገበሬ ከነበሩት ጥንድ በሬዎች አንዱን አርዶ አርባዋን አስቆርቦላት ነበር:: ሌላ ጊዜ የንስሐ አባትየው ወደ ባል መጥተው በመፅሐፈ ሲራክ ለሙታን መታሰቢያ ማድረግ ምን ጥቅም እንዳለው ጠቅሰው ሲያስተማሩት እንዲያው በደፈናው "አሁን ደግሞ ሰማኒያዋን አስቆርብላት" አሉት:: ገበሬውም መልሶ "ካሉኝ ጥንድ በሬዎች አንዱን አርጄ አርባዋን አስቆርቤያለሁ:: አሁን ደግሞ ሰማኒያዋን ማስቆረብ ካስፈለገ ቀሪውን አንድ በሬዬን ማረድ ሊኖርብኝ ነው:: ታዲያ ልጆቼን በምን ላሳድግ? አላቸው:: የንሰሃ አባቱም "አርባዋን ስላስቆብክላት ወደ ገነት ለመግባት ተቃርባ ከበሩ ላይ ቆማ ትገኛለች:: ሰማንያዋን ካላስቆረብክላት ግን በዚያው እንደቆመች መቅረቷ ነው" ሲሉ ያልተፃፈ መመሪያ አነበነቡለት::

ገበሬው በንግግራቸው ተገርሞ "እንግዲህ እርስዎ እንዳሉት ከሆነ እኔ አቅሜ የፈቀደልኝን መጠን አርባዋን አስቆርቤ ከበር አድርሻታለሁ:: ከአሁን በኋላ ግን ተጋፍታ ትግባ" ሲል መለሰላቸው ይባላል::

አንድ ጊዜ ደግሞ አንድ ባለፀጋ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው ባለሞያ የሆኑ ሚስታቸው ጥሩ የአርባ ድግስ አዘጋጅተው ካህናትና ቤተ ዘመዱን ሁሉ ጠርተው ያስተናግዳሉ:: ለግብዣውም ቁርጡና ክትፎው፣ ዝልዝል ጥብሱ ወዘተ በጠጅና አረቄው፣ ከፊልተር ጠላው ጋር አቀረቡ:: መስተንግዶ እጅግ የሚያስደስት ስነበር መሪ ጌታው ተደንቆ አንድ ዲያቆን ይልክና ከቤተ ክርስቲያን ከበሮ አስመጥቶ ሲወርብ ቆየ:: ወረቡም ወደ ቸብቸቦ ወይም ወደ ማህሌት ገንቦ ሲመለስ ዲያቆናቱ እስክስታ መውረድ ጀመሩ::

ከተጋባዦችም ቤተ ዘመድ መካከል አንዳንዱ ስለነሸጠው ወደ ካህናቱ ደብለቅ እያለ እስክስታ መውረድ ሲጀምር የተዝካሩ ቤት ሠርግ ቤት መሰለ:: በዚህ ምክንያት አስቀራቢዋ የሟች ሚስት ገርሟቸው "ምነው መሪጌታ አልበዛም እንዴ? ይህ እኮ የአርባ ድግስ እንጂ ሰርግ ቤት አይደለም" አሉ:: መሪ ጌታውም ካፈርኩ አይመልሰኝ እንደተባለው "አቶ እከሌ እኮ ገና በህይወተ ስጋ ሳሉ የጽድቅን መንገድ የተከተሉ ቀራቢ ናቸው:: እርሳቸውን ለመሰለ ጻድቅ ሰው እግዚአብሔርን በመዝሙር ማክበር እንጂ ለቅሶ ምናቸው ነው" ሲለ መለሱ ይባላል::

አምስተኛ ጉባኤ - የአባቶች ጨዋታ -
መጋቤ አእላፍ መክብብ አጥናው■

## ለማኙ ነስሩዲን

ነስሩዲን ሁልጊዜ ወደ ገበያ ለልመና ቢወጣም ሰዎች ግን ምጽዋት ከመቸር ይልቅ አንዲት የሸወዳ ብልሃትን እየተጠቀመ ይሳለቁበት ነበር::ሁለት ሳንቲሞች ያቀረቡለታል:: የአንደኛው ሳንቲም ዋጋ ከሌላኛው በአስር እጥፍ ይበልጣል:: እርሱ ግን ሁሌ ያነሰ ዋጋ ያለውን ሳንቲም መርጦ ይቀበላል:: በከተማው በጠቅላላ ይህ ወሬ ተነዛ:: በየቀኑ የተለያዩ ሰዎች ወሬውን ለማረጋገጥ ይመጡና ሁለት ሳንቲሞች ያሳዩታል:: ትንሽ ዋጋ ያላትን ይመርጣል::

አንድ ቀን ታዲያ ቸርነት ያልተለየው ሀብታም ሰው ነስሩዲን ላይ የሚዘንበው ስላቅ ስለታከተው ወደ ገበያው ዳርቻ ወሰደውና እንዲህ አለው:: "ሰዎች ሁለት ሳንቲም ሲያቀርቡልህ ከፍ ያለ ዋጋ ያለውን ልትመርጥ ይገባል:: ያን ካደረግህ አንደኛ ነገር ቶሎ ሀብታም ትሆናለህ:: ሁለተኛ ሰዎችም አያሾፉብህም" አለው:: "ጥሩ ምክር ይመስላል" አለ ነስሩዲን::

ቀጠለናም "ነገር ግን ትልቅ ዋጋ ያለውን ሣንቲም መምረጥ ከጀመርኩ ሰዎች ወደኔ መምጣት ያቆማሉ:: ገንዘቡን የሚቸሩኝ እኮ ከነሱ የባሰ ደደብ እንደሆንኩ ወይንም ከእኔ የተሸለ እውቀት እንዳላቸው ስለሚያስቡ ነው:: ይህንን ብልሃት በመጠቀም ምን ያህል ብር እንዳጠራቅምኩ ታውቃለህ? ወዳጄ ሆይ ቂል መስለህ መታየት ያን ያህልም የከፋ ነገር የለውም:: እንዲያውም የበለጠ ጠቢብ እየሆንክ ነው" አለው::

እነሆ በረከት -
ከወንድይራድ ገ/አምላክ■

## ጥቂት የዓለማችን ውድ ቀብሮች

### ታላቁ አሌክሳንደር

ታላቁ አሌክሳንደር የጥንቷን መቄዶኒያን ግዛት ያስተዳደረ ንጉስ ነው:: ይህ ንጉስ በአገዛዝ ዘመኑ አንድም ውጊያን ያልተሸነፈ በመሆኑ ውጤታማው ኮማንደርም ይባላል:: ይህ ንጉስ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ823 ሲሞት የተቀበረው በወርቅ ሳጥን እንደሆነ ይነገራል:: የዚህን ንጉስ አስክሬን ወደ ቀብር ቦታ ለመውሰድ ከወርቅ የተሰሩ እና በ60 ፈረሶች የሚጎተት ሰረገላ ጥቅም ላይ ውሏል:: ለዚህ ንጉስ ቀብርም 600 ሚሊዮን ዶላር ወጪ ተደርጓል::■

### ሮናልድ ሬገን

ሮናልድ ሬገን አሜሪካን ከ1980 እስከ 1988 ያስተዳደሩ ፕሬዝዳንት ነበሩ:: እኚህ ሰው ታክስን በመቀነስ በአሜሪካ ህዝብ ዘንድ ተወዳጅ መሪ ነበሩ:: ሬገን እ.ኤ.ኤ. በ2004 ህይወታቸው ሲያልፍ ረጅም የሀዘን ጊዜ ታውጆ ነበር:: በእርሳቸው የቀብር ቀን በርካታ የስቶክ ገበያዎች ተዘግተዋል፤ የፌዴራል ሰራተኞችም ስራ እንዳይገቡ ተደርጓል:: ይህ ቀብር ታዲያ በአጠቃላይ 400 ሚሊዮን ዶላር ወጪ ተደርጎበታል::■

### ኪም ጆንግ ኢል

የሰሜን ኮሪያ ንጉሳዊ መሪ ኪም ጆንግ ኢል ከ1994 እ.አ.አ. እስከ 2011 ይህችን ሀገር መርተዋል:: እኚህ ሰው ህይወታቸው ሲያልፍ በሀገሪቱ ህዝብ ላይ ካስከተለው ከባድ እና አስደንጋጭ ሀዘን በተጨማሪም ሀገሪቱን ከፍተኛ ወጪ አስወጥቷል:: አብዛኛው የሀገሪቱ ንብረት የእኚህ ሰው ስም የተፃፈበት በመሆኑ የእነዚህን ነገሮች ስም ለመቀየር በርካታ ዶላሮች ወጪ ተደርገዋል:: ለንጉስ መቀበሪያ የሚሆን ሳጥን ከራሺያ የተገዛ ሲሆን፣ በአጠቃላይ ለዚህ ቀብር ስነስርዓት 40 ሚሊዮን ዶላር ወጪ ሆኗል::■

### ጆን ኤፍ ኬኔዲ

ጆን ኤፍ ኬኒዲ በአሜሪካች ዘንድ እጅግ የሚወደዱ ፕሬዝዳት ሲሆኑ፤ እ.ኤ.አ. በ1963 ዓ.ም በመኪና በመጓዝ ላይ እንዳሉ ጥይት ተተኩሶባቸው ህይወታቸው አልፏል:: ኬኔዲ ከባለቤታቸው እና ከሁለት ልጆቻቸው ጋር ከሁለት ወንድሞቻቸው መቃብር ጎን የተቀበሩ ሲሆን፣ ለዚህ የቀብር ስነስርዓትም በአጠቃላይ 15 ሚሊዮን ዶላር ወጪ ተደርጓል::n

### ጆን ፖል ዳግማዊ

እኚህ ሰው በታሪክ ለረጅም ዓመታት ያገለገሉ የካቶሊክ ጳጳስ ናቸው:: ከ1978 እስከ 2005 እ.ኤ.አ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን በማስተዳደር ከሚኒዝምን ከፖላንድ ለማስወጣት እና ህዝቡም ከሌሎች ሀገራት ህዝብ ጋር ግንኙነት እንዲኖረው ያደረጉ ታላቅ ሰው ናቸው:: እኚህ ሰው በ2005 ዓ.ም ሲሞቱ ከሰሜን ኮሪያ፣ ከኩባ እና ከሌሎች ሀገራት የሀዘን መግጫዎች ተልከዋል:: ይህ ቀብር በታሪክ በርካታ የዓለም መሪዎች የተሰበሰቡበት ቀብር ሲሆን፤ በቀብሩ ላይም አራት ንጉሶች፣ አምስት ንግስቶች፣ 70 ፕሬዝዳቶች እና ጠቅላይ ሚኒስትሮች እንዲሁም 14 መሪዎች እና የሃይማኖት አባቶች ተገኝተውበታል:: ለዚህ ቀብርም 11 ነጥብ 9 ሚሊዮን ዶላር ወጪ ሆኗል::■

### ልዕልት ዲያና

ልዕልት ዲያና በ1997 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ስትለይ በቤተሰቦች ትዕዛዝ መሠረት የሀገሪቱ ሰንደቅ አላማ በግማሽ ዝቅ ብሎ እንዲውለበለብ በመደረጉ በህዝብ ዘንድ ቅሬታን አስነስቶ በር:: የልእልቷ ቀብር ከፍተኛ ዝግጅት የተደረገበት የቀብር ስነስርዓት ሲሆን፤ ለዚህ ቀብርም 11 ነጥብ 8 ሚሊየን ዶላር ነበር የወጣው::■

### ዊንስተን ቸርችል

ሰር ዊንተን ቸርችል የአሜሪካ ጠቅላይ ሚኒስትር በመሆን ከ1940 እስከ 45 እንዲሁም በድጋሚ ከ1951 እስከ 1955 መርተዋል:: ቸርችል ከሀገር መሪነታቸው በተጨማሪም ታዋቂ ፀሐፊ እና በስነፅሁፍ የኖቤል ተሸላሚም ናቸው:: እኚህ ሰው እ.ኤ.አ በ1965 ሲሞቱ ለልዑላን ቤተሰቦች በሚደረግ ብሔራዊ የቀብር ስነ ሥርዓት ነበር የተቀበሩት:: እስከ አሁን ድረስ በቀብር ስነ ሥርዓት ላይ ተገኝተው የማያውቁ የሀገር መሪዎች የተሰበሰቡበት የቀብር ስነሥርዓት ተብሎ የተቀመጠው ይህ ቀብር የወጣበት 4 ነጥብ 2 ሚሊዮን ዶላር ነው::■

### ማርጋሬት ታቸር

ተወዳጇ እና አሜሪካን ከ1979 እስከ 1990 በጠቅላይ ሚኒስትርነት የመሩት:: እኚህ ሴት በ2013 በስትሮክ ምክንያት ሞተዋል:: ለእኚህ ሴት ቀብር ማስፈፀሚያ ከመንግስት እና ከግብር ከፋዮች ለፀጥታ፣ ለፖሊስ፣ ከቀብር ቦታ እና ለለንደን አምቡላንስ በአጠቃላይ የወጣው ወጪ 1 ነጥብ 8 ሚሊዮን ዶላር ነበር::■

### ማይክል ጃክሰን

ታዋቂው የፖፕ ሙዚቃ አቀንቃኝ በአለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ ያደረጉትን በርካታ ሙዚቃዎች በመስራት ቀዳሚውን ስፍራ መያዝ የቻለ አርቲስት ነበር:: ይህ አርቲስት እስከ አሁን ድረስ በግልፅ ባልታወቀ ምክንያት እ.ኤ.አ በ2009 ህይወቱ ሲያልፍ መላው አለም በህዘን እንባ ተራጭቶ ነበር:: ለዚህ ታዋቂ አቀንቃኝ ቀብር ማስፈፀሚያም የአንድ ሚሊዮን ዶላር ወጪ መደረጉ ተገልጿል::

## ህይወት ደምናብን

እውነት ደንዝዘናል፣
ብልጭልጭ ብርቅርቅ
ነገር አታሎናል::
እውነትም ፈዘናል፣
ማስተዋል መገንዘብ፣
መስማት ተስኖናል::
የምርምር ከፍተናል፣
ውስጣችን አቂሞ
ነገር ተጣብቶናል፣
ልባችን አርቆ
ተንኮል አሲረናል፣
ከኛው ተጣልተናል::
ዘመን ዘመን ሸሮ፣
ሆድ ጀርባውን ክዶ
በኛው ላይ አሲሮ
እኛን በኛው ቀብሮ::
ሳቃችን ለይምሰል፣
ደስታችን ለቅፅበት፣
ተፈጥሮን ረስተን
ሞታችንን ታቅፈን
ማዘን እናውቀበት::
እውነት ደንዝዘናል፣
እውትም ፈዘናል፣
ውሸት ተምረናል፣
ህይወት ደምናብን፣
ከሰው ተራ ወርደን
ትውልድ አርክሰናል
ታሪክ ቀይረናል::

ቋጠሮ -
በማህደር ሽፈራው■

ኪነ-ጥበብ እና ባህል

# ያ ትውልድ እና ይህ ትውልድ

በጥበቡ በለጠ

የኢሕአፓ (የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ) መስራቹና ከፍተኛ አመራሩ ውስጥ የነበረው ክፍሉ ታደሰ "ያ ትውልድ" እያለ የሚጠራው የኢትዮጵያ ወጣት አለ፤ ነበረ። እኔ ደግሞ "ይህ ትውልድ" የምለው በዚህ እኔ ባለሁበት ዘመን ውስጥ አብሮኝ የሚኖረውን፣ የማውቀውን፣ የሚያውቀኝን ኢትዮጵያዊ ወጣት ነው። ክፍሉ ታደሰ ያ ትውልድ ብሎ ስለ ራሱ ትውልድ ሦስት ተከታታይ መፃሕፍትን አሳትሞለታል፤ ዘክሮታል። እርግጥ ነው፤ እኔ ደግሞ ስለዚህ ስለ እኔ ዘመን ትውልድ በየኮሪደሩ ከማወራው በስተቀር መፅሐፍ አላሳተምኩለትም። ግን እስኪ ወግ እንጠርቅ!

"ያ ትውልድ" ውስጥ በስፋት ተንፀባርቆ ይታይ የነበረው ለአዲስ አስተሳሰብ፣ ለለውጥ፣ ወደፊት ለመጓዝ፣ ጨለማውን ሰንጣጥቆ ወጥቶ ብርሃን ለማየት ወኔ፣ ቆራጥነት አይበገሬነት ይታይበት ነበር። ከዚህ ሌላ በዓለም አቀፍ ደረጃ ይቀነቀኑ ስለነበሩ ትኩስ ፖለቲካዊ አጀንዳዎችና ፍልስፍናዎች የማንበብ የማወቅና ከዚያም የመተግበር እንቅስቃሴዎችን ያዘወትራል።

በአንጻሩ ደግሞ "ያ ትውልድ" ለዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ቅርብ አልነበረም። በርካታ መረጃዎች በየቀኑ አይጎርፉለትም። አእምሮውን የሚያስጨንቀው የሚያስጠብበው በሚከተለው የፍልስፍና መንገድ ብቻ ነው። እንደ ጥያቄ ያነሳውን ነገር ቀጥተኛ ምላሽ ካላገኘ ራሱን ለመሰዋት የተዘጋጀ ነበር።

ከዚህ አንጻር የእኔን ዘመን ትውልድ ሳየው ብዙ ልዩነቶችን አገኝበታለሁ። እርግጥ ነው፤ በዚህ በአሁኑ ትውልድ እና በያ ትውልድ መካከል አንድ የተዘነጋ ትውልድ አለ። ይህም የደርግ ዘመን ወጣት (አኢወማ) እየተባለ ይጠራ የነበረው ነው። አ.ኢ.ወ.ማ. ማለት (የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ወጣቶች ማሕበር) ነው። ይህ ማህበር ደግሞ በማርክሲስት ሌኒኒስት ፍልስፍና የተጠመደ፣ በግድ እነዚህን ፍልስፍናዎች እንዲያውቅ የሚደረግ፤ ደርግ ያሳትመው የነበረው "ሠርቶ አደር" እየተባለ የሚጠራውን ጋዜጣ በግዴታ የሚያነብ በአጠቃላይ ብኩን ወጣት ነበር።

ይህ ብኩን ወጣት ከክፍሉ ታደሰ "ያ ትውልድ" ምንም ነገር እንዳይቀበል ተደርጓል። ወደዚህ ትውልድ ደግሞ ያወረሰው ያስተላለፈው ነገር እምብዛም ነው። ስለዚህ ክፍተት ያለበት ቦታ ነው።

ከዚህ ክፍተት በኋላ የተፈጠረው ደግሞ ዛሬ እስከ 35 ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ ያለው ወጣት ነው። ይህ የወጣት ክፍል በብዙ ችግሮች ውስጥ አልፎ የሚገኝ ነው። ለምሳሌ የነገዋን ብርሃን አሻግሮ እንዳይመለከት በ1980ዎቹ ውስጥ በሀገሪቱ አንድ አሸባሪ ክስተት ተፈጠረበት። ይህም የHIV ኤድስ ቫይረስ በስፋት መሰራጨት እና እሱን ተከትሎ ደግሞ ከየቤቱ የሚረግፈው ሰው ብዛቱ የትየለሌ ሆነ።

ከቫይረሱ በላይ ደግሞ ስለዚሁ በሽታ ማስተማሪያና ግንዛቤ መስጫ ተብሎ በየቀኑ የሚሠራጨው ማስታወቂያ፣ ማስፈራሪያ የወጣቱን ሃሳብና አመለካከት የሰለበው ይመስለኛል። በየቀኑ ተጠንቀቅ፣ እንዳትያዝ፣ ራስህን ጠብቅ፣ ውልፍጥ፣ መመናቀር፣ መንቀዥቀዥ የለም! ወዘተ የሚሉት የማስፈራሪያ ኃይለ ቃሎች በዚህ ዘመን የተፈጠረውን ወጣት የአእምሮ እስር ቤት ውስጥ የከተቱት ይመስለኛል። በነፃነት እንዳያስብ፣ የፈቀደውን እንዳያደርግ ማህበራዊ ጫና የተፈጠረበት ዘመን ነው።

ከዚህ ሌላ የሀገሪቱ ስርዓትን አስተሳሰብም ጭምር ወደ ሌላ ምዕራፍ የተገባበት ወቅት ነው። ሰዎች በአንድነት፣ በሕብረብሔርነት ሲያስቡት የነበረው




ፍልስፍና ተቀይሮ ወደ ተለያዩ ጎሳና ቀበሌያዊ ተኮር ምዕራፎችም የተገባበት ዘመን ነው። ከሕብረብሔርነት ይልቅ እስኪ ማንነቴን፣ ትውልዴን፣ ቋንቋዬ፣ መንደሬን በቅድሚያ ላጥናው የተባለበት ወቅት ነው። ለጥናት ተብሎ እዚያው ቀበሌያዊ በሆነ አስተሳሰብ ውስጥ ገብቶ የተቀረበት ዘመን ነው። አያሌ የፖለቲካ ቡድኖች የተፈሩበት፣ ከዚያም አልፎ እነዚህ ቡድኖች ደግሞ ዋነኛ ትኩረታቸው ለተደራጁበት ቋንቋ እና ጎሳ መሆኑ ነው። ስለዚህ ትልቁን ሀገራዊ ስዕል ለማየት መጀመሪያ ወደ ስር ወርደን ቀበሌያችንን እንወቅ የተባለበት ዘመን ነው። ስለዚህ የዚህ ዘመን ወጣት ከያ ትውልድ አፈጣጠር የሚለይበት ዋነኞቹ ምክንያቶች እነዚህ ይመስለኛል።

ታዲያ ይህን ትውልድ እና ያንን ትውልድ ለማወዳደር እነዚህ ከላይ የጠቀስኳቸው መረማመጃ ነጥቦች እንዲያዙልኝ እፈልጋለሁ። ምን እነዚህ ብቻ ሌላም አብዮት ተከስቷል። ከ1985 ዓ.ም በኋላ አያሌ የግል የፕሬስ ውጤቶች መጥተዋል። እነዚህ ፕሬሶች ጥቅምም ጉዳትም ነበራቸው። ጥቅማቸው ልዩ ልዩ አስተሳሰቦች በነፃነት እንዲንሸራሸሩ ያደርጋሉ። ያበጡ የሰው ልጆችን ስሜቶች ያስተነፍሳሉ። በመተንፈስ ምክንያት ለሌላ እርምጃ የማይዳረጉ ሰዎች ተፈጥረዋል።

በአንድ ወቅት ስለነፃ ፕሬስ በቀረበ ጥናት አንድ አስገራሚ ነገር ሰምቻለሁ። ይህም የነፃ ፕሬስ ጎጂነት ተብሎ የተሰነዘረ ሃሳብ ነው። ነፃ ፕሬስ የሰዎችን ስሜት በነፃነት ስለሚያስተነፍስ ለትግል፣ ለውግያ፣ ለጦርነት ለለውጥ የሚደራጁ የለም የሚል። ለጦርነት የሚደራጅ አለመኖሩ ጥሩ ነው። ግን ነፃ ፕሬስ ስለማያዋጋ ጎጂ ገፅታው ነው ተብሎ መጠቀሱ ገርሞኝ አልፏል። ለማንኛውም ይህ ትውልድ ነፃ ፕሬስ ስለነበረው ሁሉንም ነገር ሲያነብ ቆይቷል።

መች በዚህ ብቻ አቆመ። የኤፍ ኤም ሬዲዮ ዘመንም ወረረው። ወረረው ያልኩት አደነዘዘው ወደሚለው መስመር እንዲያስገባኝ ነው። ይህ ወጣት በእንግሊዝ ክለቦች፣ በእነማንችስተርና አርሴናል ፍቅር ተለክፎ ከጥቅም ውጭ እየሆነ ነው የሚሉ አሉ። እርግጥ ነው በየጊዜው በትውልዱ ውስጥ እየተፈራረቁ የሚመጡት የአስተሳሰብ ልዩነቶች መጨረሻ ላይ አንድ መሸሸጊያ መጠለያ ጥግ ይፈልጋሉ። ኤች.አይ.ቪ. ኤድሱ፣ የጎሣ ተኮር ፖለቲካው፣ የሬዲዮ ጣቢያዎች የትኩረት አቅጣጫዎች ባብዛኛው ለእንግሊዝ ሀገር ስፖርት መሠጠት፣ ተጨባጭ የሆነ አዳዲስ ስርዓታዊ ለውጦችን አለማየት፣ በመንግሥት መዋቅር ውስጥ የወጣቱ የስልጣን ውክልና እጅግ አናሳ መሆን ተደማምሮ የዚህን ዘመን ወጣት ሁሉንም ነገር እርግፍ አድርጎ የነሩኒ እና የነ ሜሲ የየእለት ሕይወት ተከታታይ አድርጎታል።

እኔ የዚህን ዘመን ወጣት ሃጢያቱን ለመቀነስ የተጠቀምኩባቸው መንደርደሪያዎቼ ተደርገው እንዳይወሰዱብኝ ከወዲሁ አሳስባለሁ። ይህ ወጣት በቴክኖሎጂ ውጤቶችም የተከበበ ነው። የዓለም መረጃዎችን ኪሱ ውስጥ አድርጎ ከያዛት ተንቀሳቃሽ ስልኩ ውስጥ ይዞ የሚኖር ነው። የፌስ ቡክ አብዮት ፈንድቶ በተለይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የደረሰ ወጣት ሁሉ ግንኙነት የፈጠረበት የተሳሰረበት ወቅት ነው።

እነዚህን የዘመኑን የመረጃ ቋቶች ጥሎ በአንድ አስተሳሰብና ፍልስፍና ውስጥ ተመስጦ የሚገባ ትውልድ አሁን የለም። ይህ ትውልድ ቀደም ብዬ በጠቀስኳቸው ነጥቦች የተከበበ፣ የተሠራ፣ የዚያም ውጤት ነው። ስለዚህ ትውልዱ የተፈጠረበትን የዘመን ዘር (ቅመም) በቅጡ ማወቅ ግድ ይላል።

አንዳንድ ሰዎች ይህን ትውልድ ሲወቅሱት ይደመጣል፤ ይነበባልም። የሚወቀሰው እንደ "ያ ትውልድ" ቆራጥ አይደለም፤ ራሱን አሳልፎ አይሰጥም፤ የሚያምንበት ዓላማ እና ፍልስፍና የለውም። አላማም ሆነ ፍልስፍና ከሌለው ደግሞ ተስፋ የሚጣልበት አይደለም እያሉ በተለያዩ ድረ-ገፆች ይወቅሱታል።

እኔ በበኩሌ ይህ ትውልድ ራሱን እና ቀጣዩን የሀገሩን እጣ ፈንታ እንዲረከብ፣ እንዲሰራ፣ ኃላፊነት እንዲሰማው የማድረግ ስራ በሁሉም ወገኖች ቢሰራ ነው ደስ የሚለኝ። ዛሬ በብዙ የስልጣን መንበር ላይ ያሉት ሰዎች የዚያ ትውልድ አባላት ናቸው። ዛሬ በተቃውሞ የፖለቲካ አስተሳሰብ ውስጥ ናቸው። ዛሬ በተቃውሞ የፖለቲካ አስተሳሰብ ውስጥ ያሉትም የዚያ ትውልድ አባላት ናቸው። ስለዚህ የዚህ ትውልድ እጣ ፈንታ የቱጋ እንደሆነ በቅጡና በውል አልታወቀ እያለ ነው።

ይህ ትውልድ ጨምሮ የሚቀጥለውም ትውልድ የተሻለ አስተሳሰብና አመለካከት እንዲኖረው የባሕል አብዮት መካሔድ አለበት። የባሕል አብዮት የምለው በሁሉም መስክ ነው። ለምሣሌ ትምህርታችን ላይ ትኩረት መደረግ አለበት። ኢትዮጵያዊ የሆነ የትምህርት ፍልስፍና እና አስተሳሰብ ያስፈልገናል። ዶ/ር እጓለ ገ/ዮሐንስ የከፍተኛ ትምህርት ዘይቤ ብለው ባሰናዱት መፅሀፍ ውስጥ እንደተጠቀሰው ትምህርታችን ኢትዮጵያዊ ግብ ያስፈልገዋል። በእንግሊዝ እግር ኳስ ጨዋታ የሚዋልል፣ የሚደባደብ፣ የሚገዳደል ትውልድ ማፍራት የለብንም።

ባሕል ስንል በሌላ መልኩ ታሪክን፣ ሃይማኖትን፣ ጥበብንም ይመለከታል። በሀገሩ ታሪክ የሚኮራ ትውልድ መፍጠር የየትኛውም ሃይማኖት ተከታይ ቢሆን ለሃይማኖቱ ታማኝ የሆነ፣ ፅናት ያለው ትውልድ ያስፈልጋል። ጥበብን ይውደድ ስል ማንበብን፣ መመራመርን፣ ማድነቅን፣ ሰውን መውደድን፣ ሀገሩን እና ሕዝቡን የሚታደግ ትውልድ ለማፍራት ዛሬ መጀመር የሚገባን ስራ አለ። ትውልድና ሀገር በሂደት ነው የሚገነቡት።

በአጠቃላይ "ያ ትውልድ" ላመነበት ፍልስፍና ብሎም አመለካት ራሱን ሰውቶ ያለፈው እኔ በበኩሌ የክብር ቦታ ሊያሰጠው ይገባዋል ባይ ነኝ። ምክንያቱም ሕይወቱን ከመስጠት ውጪ ሌላ ትልቅ ነገር የለምና ነው።

ይህ ትውልድ ደግሞ የራሱን ገመና የሚፈትሽበት ወቅት ነው። ሐገሬን አውቃታለሁ? ባህሌን፣ ታሪኬን፣ ማንነቴን መግለፅ እችላለሁ? ለሀገሬ ኢትዮጵያ እኔ ምንድን ነው ማድረግ የምችለው? በዚህች ፕላኔት ላይ ስኖር አላማዬ ምንድን ነው ብሎ እስኪ ዛሬን ያስባት። እናስባት። ሃሳቤ አላላቅም። ሣምንትም እቀጥልበታለሁ።n

በኪዳኔ መካሻ (የሕግ ባለሙያ)
Kidane1983@yahoo.com

# ሸማችና ነጋዴ

(ክፍል 2)

**- ጤናማ የንግድ ውድድርን ለማስፈን ለነጋዴው ሕጉ የሰጠው ጥበቃ ምንድን ነው?**
**- ፀረ የንግድ ውድድር ተግባራት የትኞቹ ናቸው?**
**- ከገበያ የበላይነት ጋር በተያያዘ ነጋዴው ላይ የተጣሉ ገደቦች፣**
**- ተገቢ ያልሆነ የንግድ ውድድር የሚባሉትስ የትኞቹ ተግባራት ናቸው?**

እንዴት ናችሁ? ሰላም ነው? ሳምንት ገበያውን ወደሚገራው አዋጅ ጉራ ብለን አንስተነዋል። አዋጁ 813/2006 ስለ ንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ የወጣውና በሥራ ላይ የሚገኝ አዋጅ ነው። በዚህ አዋጅ መሠረት ሸማች ተብለው ጥበቃ የተሰጣቸው እነማን እንደሆኑ፣ 'ነጋዴ' የሚባሉት የትኞቹ ሻጮችን እንደሆነ፣ የሸማቾችን መብቶች እና የነጋዴዎችን ግዴታ አንስተናል። በዛሬው ጽሁፍ ደግሞ ጤናማ የንግድ ውድድርን ለማስፈንና የሸማቾችን ጥቅም ለመጠበቅ በአዋጁ የተከለከሉ ተግባራትን ተገቢ የንግድ አሰራርና የሸማቾች ጥበቃን ተግባራዊ ለማድረግ በአዋጁ ኃላፊነት የተሰጣቸው ተቋማትን እንዲሁም በአዋጁ የተከለከሉ ተግባራትን መፈፀም የሚያስከትለውን ኃላፊነት እንመለከታለን። እንቀጥል፡-

**1. ጥበቃ ለሸማቹም ለነጋዴውም**

አዋጅ ቁጥር 813 ዓላማውን በመግቢያው ላይ እንዲሁም በአንቀጽ 3 ላይ ገልጾታል። ለነፃ ገበያ ውድድር አመቺነት ያለው ስርዓት ለማስፈን የንግዱን ኅብረተሰብ ከፀረ-ውድድርና ተገቢ ካልሆኑ የገበያ ተግባራት መጠበቅ አንዱ ሲሆን፤ ሌላው ሸማቹን የሚያሳስቱ የገበያ ሁኔታዎችን መከላከል ለደህንነቱና ለጤናው ተስማሚ የሆኑና ላወጣው ዋጋ ተመጣጣኝ የንግድ እቃዎችንና አገልግሎቶችን ማግኘት የሚችልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ሦስተኛው ደግሞ የሁለቱ ዓላማዎች ድምር ውጤት የሆነውን የኢኮኖሚ ልማትን ማፋጠን ነው። ስለዚህ ሕጉ ለሸማቹ ብቻ የወገነ ሳይሆን ነጋዴውም አንዱ የገበያው ተዋናይ በመሆኑ ጥበቃ አድርጐለታል። ከእነዚህ ጥበቃዎች አንዱ ፀረ-ውድድር የንግድ ተግባራትን የሚመለከት ሲሆን፤ እነኚህን ፀረ ውድድር የንግድ አሰራሮች ቀጥለን እንመልከታቸው

**2. የገበያ የበላይነትን አለአግባብ መጠቀም**

አንድ ነጋደ የገበያ የበላይነት አለው የሚባለው በአዋጅ አንቀጽ 6 መሠረት በግሉ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በአንድ የገበያ ክልል ውስጥ ዋጋን ወይም ሌሎች የንግድ ድርድር ሁኔታዎችን የመቆጣጠር ወይም የማጥፋት ወይም በግልፅ የመገደብ አቅም ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ነው። ነጋዴው የገበያው የበላይ መሆኑ የሚረጋገጠው ገበያው ውስጥ ያለው ድርሻ ወይም ሌሎች ወደገበያው እንዳይገቡ ለመከልከል ያለውን አቅም በማየት ሲሆን፤ ሌሎች አግባብነት ያላቸው መመዘኛዎችመ በተጨማሪ ነጋዴው የበላይነቱን መያዙን ለማረጋገጥ መለኪያ ይሆናሉ። የበላይነት መኖሩ ሊለካ የሚችለው በአንድ ገበያ ውስጥ ሲሆን፤ ገበያው ተወዳዳሪ ሊሆኑ የሚችሉ ወይም የሚተካኩ የንግድ እቃዎችንና አገልግሎቶችን የያዘ መሆን አለበት። ለምሳሌ እንደገበያው የሚባለው የህዝብ ትራንስፖርትን ብንመለከት የከተማና የክፍለሀገር ተብሎ በታክሲ በአውቶብስ ተብሎ የራሱ እንደ አንድ የገበያ ክልል ሊታይ ይችላል። መልከዓ ምድራዊ የገበያው ክልል ደግሞ የውድድር ሁኔታዎች በበቂ ሁኔታ አንድ ዓይነት የሆኑበትና ከአጐራባች ገበያዎች ካለው ሁኔታ የሚለይ መሆን አለበት። ይህ የገበያ የበላይነት በቁጥር ሊሰራ የሚችልበትን መጠን በአዋጅ አንቀጽ 6(5) የሚኒስትሮች ም/ቤት በሚያመጣው ደንብ ሊወሰን እንደሚችል ተደንግጓል።

ይሄን የበላይነት ነጋዴው በአግባቡ ተጠቅሞ ማስጠበቅ የሚችል ሲሆን፤ አለአግባብ ይህን የበላይነት በግልፅም ሆነ በስውር ተጠቅሞ የንግድ ስራ ማካሄድ ግን በአዋጅ አንቀጽ 5(1) ተከልክሏል። የበላይነትን አለአግባብ መጠቀም የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው።

<u>1.1. ምርትንና አቅርቦትን በተመለከተ</u>፡ - ማንኛውም ነጋዴ የበላይነቱን በመጠቀም ምርትን መገደብ፣ የንግድ እቃዎችን ማከማቸት ወይም በመደበኛው የንግድ መስመር እንዳይሸጡ ለማድረግ መደበቅ፣ ማገድ ወይም መያዝ አንዱ የገበያ የበላይነትን አለአግባብ የመጠቀም አሰራር ነው።

<u>1.2. ተወዳዳሪን መጉዳት</u>፡- ይህ ነጋዴው የገበያ የበላይነትን አለአግባብ በመጠቀም ከማምረቻ ዋጋ በታች በመሸጥ፣ የተወዳዳሪን ወጪ በማሳደግ ወይም የግብአቶችን ወይም የስርጭት መስመሮችን ቀድሞ በመቆጣጠር ተወዳዳሪ ላይ ያነጣጠረ ጐጂ ድርጊት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መፈፀምን የሚመለከት ነው።

<u>1.3. ኢ-ፍትሐዊ ዋጋ መወሰን</u>፡- ነጋዴው የበላይነቱን ተጠቅሞ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ፍትሐዊ ያልሆነ የመሸጫ ወይም የመግዣ ዋጋ ከወሰነ የበላይነቱን አለአግባብ ተጠቅሟል።

<u>1.4. ድርድርን አለመፍቀድ</u>፡- ግልጽና ወቅታዊ የገበያ አሰራርን በተቃራኒ መልኩ ነጋዴው በልማድ የሚያደርገውን ወይም ሊያደርገው የሚችለውን እንደማይችለው ሆኖ በመቅረብ በሚቀርቡለት አማራጮች ላይ ለመደራደር አለመፍቀድ ማለት ነው።

<u>1.5. ያለ አሳማኝ ኢኮኖሚያዊ ምክንያት የሚፈጠሩ ሁኔታዎች</u>፡- ገበያውን በበላይነት የያዘው ነጋዴ አሳማኝ ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች በሌሉበት የሚከተሉትን መፈፀም ለአዋጁ አፈፃፀም የበላይነትን አለአግባብ በመጠቀም የሚደረግ ድርጊት ተደርጐ ይቆጠራል።

-በቁጥጥሩ ስር ያለውን ተፈላጊ ግብአት ለተወዳዳሪው ወይም ሊሆን ለሚችለው ነጋዴ መከልከል

-በእቃዎችና አገልግሎቶች አቅርቦትና ግዢ ላይ በደንበኞች መሀል በዋጋና በሌሎች ሁኔታዎች ላይ ልዩነት መፈጠር

-ተወዳዳሪው የሆነውን ወይም ያልሆነውን የንግድ እቃ ወይም አገልግሎት መቀበልን አንድን ዕቃ ወይም አገልግሎት ከማግኘት ጋር ማያያዝ ወይም የሌላ ተወዳዳሪ እቃ እና አገልግሎት ማከፋፈል ወይም ማምረት ላይ ገደብ መጣል

-በገኘው ከሚፈለገው የንግድ እቃ ወይም አገልግሎት ጋር ግንኙነት ከሌለው የንግድ እቃ ወይም አገልግሎት ግዢ ጋር እንዲያያዝ ማድረግ

-የንግድ እቃዎችንና አገልግሎቶችን አቅርቦት በተመለከተ የት፣ ለማን፣ በምን ሁኔታ፣ መጠን ወይም በምን ያህል ዋጋ እንደገና መሸጥ ወይም ወደ ውጭ መላክ እንዳለበት ገደብ መጣል እና አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ የሚዘረዘሩ ሌሎች ተመሳሳይ ድርጊቶችን መፈፀም ናቸው።

በአዋጁ አንቀጽ 5(3) አሳማኝ ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች የሚባሉት፤

-የንግድ እቃዎችንና አገልግሎቶችን ጥራትና ደህንነት መጠበቅ

-ሌላው ተወዳዳሪ ከሰጠው ዋጋ ወይም ጥቅም ጋር መስተካከል

-ተወዳዳሪ ሆኖ መገኘትና አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጡ ደንቦች ላይ የሚዘረዘሩ ተመሳሳይ ድርጊቶች ናቸው።

**3.ፀረ-ውድድር የነጋዴዎች ስምምነቶችና የኅብረት አቋሞች**

በነጋዴው መሀል ጤናማ የሆነ ውድድር መኖሩ ለሸማቹም ለነጋዴውም ለአጠቃላይ እድገትም ጠቃሚ ነው። ሆኖም ይህ ጤናማ ውድድር እንዳይኖር የሚያደር የጥቂት (የተወሰኑ) ነጋዴዎች ድርጊቶች ገበያው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራሉ። ነጋዴዎቹ የሚያደርጉት 'ስምምነት' በሕግ ፊት የሚፈፀም ባይሆንም መግባባትን፣ በጽሁፍ ወይም በቃል የተፈፀመ ውልን እና የአሰራር ስርዓትን እንደሚያካትት በአዋጁ አንቀጽ 7(3) ላይ ተመልክቷል። በነጋዴው የሚያዝ ፀረ ውድድር የኅብረት አቋም ደግሞ ከላይ ያነሳነውን ስምምነት በማይመስል መልኩ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በየግል ነጋዴው የሚፈፀመውን ተግባር ለመተካት የሚፈፀም የትብብር ድርጊት ነው።

በዚህ መልኩ የጐንዮሽ ወይም ከላይ ወደታች ግንኙነት ባላቸው ነጋዴዎች መሀል ፀረ ውድድር ስምመነቶች እና አቋሞች ሊያዙ ይችላሉ።

የጐንዮሽ ግንኙነት የሚባለው በአንድ ገበያ ውስጥ ባሉ ተወዳዳሪ ነጋዴዎች መሀል የሚኖር ግንኙነት ሲሆን፤ የደረሱበት ስምምነት ወይም የተያዘው አቋም የንግድ ውድድርን የሚያግድ ወይም በጉልህ የሚቀንስ ይህ ስምምነት የሚያስገኘው የቴክኖሎጂ የአሰራር ቅልጥፍና ወይም ውድድርን የሚያጠናክር ጠቀሜታ ከሚያስከትለው ጉጂ ተጽዕኖው የሚያመዝን መሆኑን ማንኛውም ተሳታፊ ሊያስረዳ ካልቻለ ወይም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የመግዣ ወይም የመሸጫ ዋጋ ወይም ማንኛውንም የንግድ ገደብ መወሰን፣ ተመሳጥሮ መጫረት ደንበኞችን አቅራቢዎችን ክልልን ወይም የምርትና የአገልግሎትን አይነቶችን በኮታ በመመደብ የገበያ ድርሻን መከፋፈልን የሚመለከት ከሆነ በአዋጁ ላይ የተከለከለ ስምምነት ወይም አቋም መሆኑ ተደንግጓል።

በሌላ በኩል ግንኙነታቸው ከላይ ወደ ታች የሆነ የሚባሉት ነጋዴዎች ከደንበኞች ወይም ከአቅራቢዎች ወይም ከሁለቱም ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት የሚመለከት ሲሆን፤ ስምምነቱ ወይም የኅብረት አቋሙ ለንግድ ውድድር ለአሰራር ቅልጥፍና፣ ለቴክኖሎጂ የሚያበረክተው ጥቅም አሉታዊ ተፅዕኖዎቹ እንደሚያመዝን የስምምነቱ ወይም የኅብረት አቋሙ አባላት መሀል ማንኛቸውም ሊያስረዱ ካልቻሉ ወይም ዝቅተኛ የመልሶ መሸጫ ዋጋን የሚወስን ከሆነ በአዋጁ አንቀጽ 7(2) የተከለከለ ተግባር ነው።

**4. ውድድርን የሚጐዳ ውህደት**

በነጋዴው መካከል መኖር ያለበትን ጤናማ ውድድር ከሚጐዱ ተግባራት መካከል የተለያዩ ነጋዴዎች በአንድ በመዋሀድ በመካከላቸው ሊኖር የሚችለውን ውድድር የሚያጠፉበት ሌሎች በተናጥል በገበያው የሚሳተፉ ተወዳዳሪ ነጋዴዎች የነበራቸውን የገበያ አቅም አጥተው ከጨዋታው እንዲወጡ የሚያደርጉበት ተግባር ነው። በመሆኑም በአዋጁ አንቀጽ 9 በንግድ ውድድር ላይ ጉልህ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያስከትሉ ወይም ሊያስከትሉ የሚችሉ ስምምነት ወይም ትስስር ውስጥ መሳተፍ ለማንኛውም ነጋዴ የተከለከለ ተግባር ነው። የውህደት ስምምነት ሙሉ በሙሉ ባይከለከልም በአዋጁ በንግድ አሰራርና ከሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ፈቃድ የማግኘት ቅድመ ሁኔታ ተጥሎበታል። ውህደት የሚባለው በግላቸው ይንቀሳቀሱ የነበሩ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የንግድ ማኅበራትን መቀላቀል ወይም አንድ ዓላማ ያለው የንግድ ሥራ ለማከናወን ሁሉንም ወይም ከፊሉን ሀብታቸውን ሲያቀላቅሉ ነው።

በነጋዴው መሀል ጤናማ የሆነ ውድድር መኖሩ ለሸማቹም ለነጋዴውም ለአጠቃላይ እድገትም ጠቃሚ ነው። ሆኖም ይህ ጤናማ ውድድር እንዳይኖር የሚያደር የጥቂት (የተወሰኑ) ነጋዴዎች ድርጊቶች ገበያው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራሉ

በሌላ መልኩ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የንግድ ማኅበር አክሲዮኖች ሴኩሪቲዎች ወይም ንብረቶችን በአንድ ወይም በብዙ ሰዎች በግዢ ወይም በሌላ መንገድ የራስ በማድረግ የሌላ ሰውን የንግድ መደብርን አመራር መቆጣጠርም በአዋጁ አንቀጽ 9(3)(ለ) ላይ እንደውህደት እንደሚቆጠር ተደንግጓል።

የውህደትን ጉልህ አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቆጣጠር በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ውህደት ለመፍጠር ያቀደ ነጋዴው ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ቅድሚያ በዝርዝር የማሳወቅ ግዴታ ተጥሎበታል። ባለስልጣኑም ውህደቱ የሚፈጥረው አሉታዊ ተፅዕኖ መኖር አለመኖሩን ያጣራል። እንደአስፈላጊነቱ የውህደቱ አካላት ተጨማሪ መረጃ ወይም ሠነድ እንዲያቀርቡ ያሳውቋል። ውህደቱን የሚቃወም ነጋዴም ሰፊ ስርጭት ባለው የጋዜጣ ማስታወቂያ ምክንያት እንዲያቀርብ ይጠራል።

ባለስልጣኑ አጣርቶ ውህደቱ የሚፈጥረው የጐላ ተፅዕኖ እንደሌለ ካረጋገጠ ይፈቅዳል። የሚፈጥረው የጐላ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳለ ካመነበት በአዋጁ አንቀጽ 11(1)(ለ) ውህደቱን የመከልከል ስልጣን ተሰጥቶታል። ሆኖም ውህደቱ የሚያስከትለው ጎጂ ተፅዕኖ የተወሰኑ ግዴታዎችን በመፈፀም ሊወገድ የሚችል ከሆነ ከግዴታዎቹ ጋር ውህደቱን መፍቀድ ይችላል። ከውህደቱ የጐላ አሉታዊ ተፅዕኖ ይልቅ ለንግድ ውድድር፣ ለሥራ ቅልጥፍና፣ ለቴክኖሎጂ የሚያበረክተው ጠቀሜታ ውህደቱ ከተከለከለ በሌላ መንገድ የማይገኝ ከሆነ ባለስልጣኑ ውህደቱን ሊፈቅድ ይችላል።

**5. ያልተገባ የንግድ ውድድር**

ቀደም ብለን ያነሳናቸው ያለውን የንግድ ውድድር የሚጐዱ የሚያጠፉ ወይም የሚያቀጭጩ የተከለከሉ የንግድ ተግባራት ሲሆኑ፤ ውድድሩን ተገቢ ያልሆነ አንዱ አለአግባብ እንዲያሸንፍ ሌላው ነጋዴ አለአግባብ እንዲወድቅ የሚያደርጉ ተግባራትም በአዋጁ አንቀጽ 8 ላይ ክልከላ ተደርጐባቸዋል።

የመጀመሪያው ማንኛውም ነጋዴ ሀቀኛ ያልሆነ፣ አሳሳች ወይም አታላይነት ያለበት እና የተወዳዳሪን የንግድ ጥቅም የሚጐዳ ወይም ሊጐዳ የሚችል ድርጊት በንግድ ሥራ ሂደት ውስጥ እንዳይፈፀም የሚከለክል ሲሆን፤ ያልተገቡ የንግድ ውድድር ተግባራት ደግሞ የሚከተሉት በአዋጁ አንቀጽ 8(2) ስር ተዘርዝረዋል።

-በነጋዴው በሥራው ከሚያቀርበው እቃ ወይም አገልግሎት ጋር በተገናኘ ማደናገርን ያስከተለ ወይም የሚያስከትል ድርጊት

-ባለቤት ከሆነው ነጋዴ ፈቃድ ውጭ ከሀቀኛ የንግድ አሰራር በተቃራኒው የሌላውን መረጃ ማውጣት፣ መያዝ መጠቀም

-የሌላውን ነጋዴ ስራውንም በተለይም የንግድ እቃ ወይም አገልግሎቱ ጋር በተገናኘ ታማኝቱን የሚያሳጣ ወይም ሊያሳጣ የሚችል የሀሰት ወይም ማረጋገጫ የሌለው መረጃ መስጠት

-በንግድ ማስታቂያ የንግድ እቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን በሀሰት ወይም በተዛባ ሁኔታ ማነፃፀር

-ከዋጋ፣ ከባህሪ ወይም ከመራራት፣ ከማምረቻ ቦታ፣ ከይዘት፣ ከአጠቃቀም ምቹነት ወይም ከጥራት ጋር በተገናኘ ምንጩ ያልታወቀውን ጨምሮ ለሸማቾች ወይም ለተጠቃሚዎች ሀሰተኛ ወይም የተዛባ መረጃ ማሰራጨት

-የሌላ ነጋዴ ሚስጥሮችን በቀድሞ ሰራተኞቹ ወይም በስራ ላይ ባሉ ሰራተኞች ማግኘት ለማግኘት መሞከር

-ሚስጥራዊ መረጃዎችን በማግኘት የነጋዴውን ደንበኞች ማስኮብለል ወይመ ሌላ ተወዳዳሪነቱን ለሚቀንስ ዓላማ ማዋል።

-አዋጁን ለማስፈፀም በሚመጣ ደንብ የሚዘረዘሩ ተመሳሳይ ያለተገቡ የንግድ ውድድር ተግባራትን መፈፀም ጤናማ ውድድርን ለማስፈን ሲባል ለማንኛውም ነጋዴ እንዳይፈጽሚቸው ተከልክለዋል።

ሌሎች በገጽና በጊዜ የተገደቡ ጉዳዮችን ሳምንት እመለስባቸዋለሁ።■

# የ 3 ትውልድ ድልድይ



በመስከረም አያሌው

ባሳለፍነው ሳምንት አርብ የበርካታ አረጋውያን እና አዕምሮ ህሙማን መጠለያ የሆነው የመቄዶኒያ የአረጋውያን እና አዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል በበርካታ ሰዎች ተጥለቅልቋል። የማዕከሉ ተረጂዎችም በቅጥር ግቢው ውስጥ በተዘጋጀላቸው መጠለያ ድንኳን ውስጥ ተቀምጠው ይጨዋወታሉ። ምርኩዞቻቸውን አገጫቸው ላይ ያስደገፉ አዛውንቶች ዝግ ባለ ድምጽ ከጐናቸው ካሉት ጋር ሲነጋገሩ፤ ሌሎች ደግሞ ካርታ ይጫወታሉ። ቀሪዎቹም ከፊት ለፊታቸው የተሰቀለው ቴሌቪዥን ላይ ዓይናቸውን ሰክተው ይመለከታሉ።

ይህንን ከላይ የተገለፀ ትዕይንት የተገነዘብነው በተጠቀሰው ዕለት ኤስ ኦ ኤስ የህፃናት መንደር ኢትዮጵያ የምስረታውን አርባኛ ዓመት እና የሰራተኞች የምስጋና በዓልን ከእነዚህ አረጋውያን እና የአዕምሮ ህሙማን ጋር በማዕከሉ ግቢ ውስጥ ለማክበር አቅዶ ወደዚያው ባመራበት ወቅት ነበር። የህፃናት መንደሮቹ ሠራተኞች እና ሌሎች ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ወደ ማዕከሉ መግባታቸውን ተከትሎ በአረጋውያን እና አዕምሮ ህሙማን ማዕከሉ ያሉ ሰዎችን የኋላ ታሪክ (ወድቀው የተገኙበትን፣ ወደ ማዕከሉ ሲመጡ የነበራቸውን ገፅታ፣ ወደ ማዕከሉ ለማምጣት የነበረውን ተግዳሮት ወዘተ) የሚያሳይ ዘጋቢ ፊልም እንዲከታተሉ ተደረገ። በርካቶች እንባና ድምጽ አውጥተው እስከማልቀስ በደረሰ ስሜት ውስጥ ሆነው ይሄንን ዘጋቢ ፊልም ከተመለከቱ በኋላ፣ እንግዶቹ በማዕከሉ የሚረዱ አረጋውያን እና አዕምሮ ህሙማንን እንዲጐበኙ ተደረገ። በዚህ ጊዜም ቀድሞ ካዩት በበለጠ በርካቶች እንባ አውጥተው ሲያለቅሱ ተስተውለዋል።

ኤስ ኦ ኤስ የህፃናት መንደር ሁለተኛውን የዓለም ጦርነት መጠናቀቅ ተከትሎ (እ.ኤ.አ በ1949) በአውስትራሊያዊው ሄርማን ጂሜነር እዚያው አውስትራሊያ ውስጥ ነበር የተቋቋመው። ሲቋቋምም ዓላማውን ያደረገው በጦርነቱ ምክንያት ከቤተሰቦቻቸው የተለያዩ ህፃናት ከቤተሰባቸው ጋር መቀላቀል እና የተበታተኑ ህፃናትን ደግሞ ሰብስቦ ከለላ መስጠትን ነበር። በዚህ መልኩ የተጀመረው ህፃናትን በመንደር የማሰባሰብ ተግባር በቀጣይ በተለያዩ አካባቢዎች በመስፋፋት በ133 ሀገራት ቅርንጫፍ መንደሮችን በመክፈት ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት መሆን የቻለ መንደር ነው። ይህ መንደር በቆይታውም 82ሺ 100 ወላጆቻቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ያጡ ችግረኛ ህፃናትን መርዳት ችሏል።

ኤስ ኦ ኤስ በአሁኑ ወቅት ለችግረኛ ህፃናት መንደር በማቋቋም ህፃናቱ በቤተሰብ ስር እንዲጠለሉ ያደርጋል። በአሁኑ ጊዜው እያንዳንዱ የህፃናት መንደር ከሀምሳ በላይ ቤተሰቦች ያሏቸው ሲሆን፤ ህፃናቱም በእነዚህ ቤተሰቦች ስር በመሰባሰብ አንድ ልጅ ከቤተሰብ ማግኘት የሚገባውን ፍቅር፣ እንክብካቤ እና ከለላ ሁሉ እንዲያገኙ ይደረጋል። በእያንዳንዱ ቤተሰብ ስር እስከ 10 የሚደርሱ ሴትና ወንድ ልጆች ይኖራሉ። እነዚህን ህፃናት የሚያሳድጉ እና ቤተሰቡን የሚያስተዳድሩ እናቶች ያሉ ሲሆን፤ እነዚህ እናቶችም የየሀገራቸውን ባህል ጠንቅቀው የሚያውቁ፣ ቤተሰቡን አስመልክቶ የተጣለባቸውን ኃላፊነት በቁርጠኝነት የሚወጡ እናቶች መሆን አለባቸው። በተጨማሪም እነዚህ እናቶች ከእነዚህ የህፃናት መንደር ውጪ ቤተሰብ የሌላቸው እና ሙሉ ጊዜያቸውን እና ትኩረታቸውን ለእነዚህ ልጆች የሚሰጡ መሆን አለባቸው።





## የህፃናት መንደሩ ይህን የሰራተኞች የምስጋና ቀን በዓል በዚህ የአረጋውያን እና አዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል ሲያከብር የዘንድሮው የመጀመሪያ ነው

በኢትዮጵያ የኤስ ኦ ኤስ የህፃናት መንደር አገልግሎት የተጀመረው በ1967 ዓ.ም ነበር። በወቅቱ በትግራይ አካባቢ ተከስቶ በነበረው የረሃብ አደጋ በርካታ ህፃናት ከወላጆቻቸው ተለይተው መቅረታቸውን እና ወላጆች በረሃቡ ምክንያት ሲሞቱ ህፃናት ያለ ወላጅ እና አሳዳጊ መቅረታቸውን ተከትሎ ነበር የመጀመሪያው የህፃናት መንደር በመቀሌ የተቋቋመው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም የኤስ ኦ ኤስ የህፃናት መንደሮች በተለያዩ ስድስት የሀገራችን ከተሞች የተቋቋሙ ሲሆን፤ በዚህ የአርባ ዓመት ቆይታም በርካታ ህፃናትን መታደግ ችለዋል።

ወደዚህ የህፃናት መንደር የሚገቡ ህፃናት እድሜያቸው ከስድስት ዓመት በታች የሆነ ሲሆኑ፤ እነዚህ ህፃናት ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደ ቴክኒክና ሙያ አሊያም ወደ ዩኒቨርሲቲ እስከሚገቡ ድረስ በመንደሩ ውስጥ እንዲቆዩ እና ማንኛውም የሚያስፈልጋቸው ነገር እንዲሟላላቸው ይደረጋል። በተለይ ሴት ተማሪዎች ደግሞ በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው ጭምር እገዛ ይደረግላቸዋል።

በህፃናት መንደሮቹ ውስጥ የቅድመ ትምህርት ቤት ህፃናት ማቆያ እና መዋዕለ ህፃናት የሚገኙ ሲሆን፤ ከእነዚህ ደረጃ በላይ ያሉ ተማሪዎች ደግሞ በየአካባቢው በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ይደረጋል። በህፃናት መንደሮቹ ውስጥ ለሚገኙ ህፃናት እና ለሌሎቹ አገልግሎት የሚሰጡ ነርሶችም በየመንደሩ ውስጥ ይገኛሉ።

የኤስ ኦ ኤስ የህፃናት መንደር ዋና ስራ አስኪያጅ የሆኑት አቶ ሳህለማርያም አበበ በማዕከሉ በዚያው የመንደሮቹ 40ኛ ዓመት እና የሰራተኞቹ የምስጋና ቀን በሚከበርበት ተገኝተው በዚህ የህፃናት መንደር የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን ገልፀውልናል። እንደ አቶ ሳህለማርያም ገለፃ ይህ የህፃናት መንደር በዋናነት ህፃናት በቤተሰብ መንፈስ እንዲኖሩ ማድረግ ነው። "እኛ የምናሳድጋቸው ህፃናት በተለያዩ ምክንያቶች የወላጅ ጥበቃና እንክብካቤ ያጡ ናቸው። ለእነዚህ ህፃናት እኛ እየሰጠናቸው ያለነው ቤተሰብ፣ የሚኖሩበት ምቹ የሆነ ቤት ነው። በተጨማሪም ያጡትን እናት ሰጥተናቸዋል። እንዲሁም እህትና ወንድም ሰጥተናቸዋል። ስለዚህ ህፃናቱ በቤተሰብ ውስጥ ሙሉ ጥበቃ ባለበት ነው የሚኖሩት" ይላሉ አቶ ሳህለማርያም።

የህፃናት መንደሩ ይህን የሰራተኞች የምስጋና ቀን በዓል በዚህ የአረጋውያን እና አዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል ሲያከብር የዘንድሮው የመጀመሪያ ነው። ከዚህ ቀደም በራሱ ጊቢ እና በተለያዩ ተቋማት ውስጥ ያከበረ ቢሆንም፤ ይህ ለ4ኛ ጊዜ የሚከበር በዓል ግን ከመንደሮቹ ጋር ተመሳሳይ ተግባራትን ከሚፈጽሙ ድርጅቶች ጋር ለማክበር በመወሰኑ እዚህ ማዕከል ውስጥ እንደተከበረ አቶ ሣህለማርያም ገልፀውልናል። በመሆኑም በመንደራቸው ውስጥ የሚገኙ ህፃናት መንደሩ ከሰጣቸው ቤተሰብ እና ወላጅ በተጨማሪ እነዚህ የመቄዶኒያ አረጋውያን ለህፃናቱ አያቶች ይሆናሉ የሚል ሃሳብ አለ።

"እነዚህ ህፃናት መንደራቸው በሚፈጥረው ግንኙነት አያት ያገኛሉ። ይህ ሲሆን ደግሞ፤ ህይወታቸው የበለጠ ይሳካል ማለት ነው። ይሄ ግንኙነት እየተጠናከረ ሲመጣ እኛም ልጆቻችንን እየያዝን እንመጣለን። ልጆቹ በፕሮግራም ወደ ማዕከሉ እየመጡ ጊዜ የሚያሳልፉበት እና ከአረጋውያኑ ልምድ እና ተሞክሮ የሚቀስሙበትን ሁኔታ እናመቻቻለን። አረጋውያኑም አልፎ አልፎ ወደ መንደሮቻችን እየመጡ ዘመድ ብለው የሚጐበኟቸው ቤተሰብ እንዲፈጠር እናደርጋለን" ይላሉ ሥራ አስኪያጁ።

በገፅ 20

# የብዝሃ ህይወት ጥበቃና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው

በአይቼው ደስአለኝ

ሀገራችን በብዝሃ ህይወት ተለያይነትና እጅግ መበርከት የተነሳ ዓለም አቀፍ ዕውቅና ካገኙት ሀገሮች መካከል አንደኛዋ መሆን ችላለች:: ብዝሃነት መኖር ስነ-ምህዳር ሳይዛባ እንዲቆይ በማድረግ በሰው ልጅ እንቅስቃሴ የሚፈጠረውን የሙቀት መጨመርና የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም ያስችላል:: ይህ ብቻ ሳይሆን ለምግብነት የሚውል ተክሎችን በማብዛት በምግብ ራስን ለመቻል እገዛ ያደርጋል::

የሀገራችን መልክዓ ምድር አቀማመጥ በጣም አስገራሚና የተለያዩ የአየር ፀባዮችን በውስጡ ለማቀፍ ያስቻለ ነው:: ከባህር ወለል በታች እስከ 5 ሜትር ከሆነው ዳሎል አካባቢ እስከ በረዷማውና ከባህር ወለል ከፍታው 4,591 ሜትር ድረስ ያለውን ያጠቃልላል:: ከቆላ ደጋ ወይናደጋና በርሃ ተብለው ከተለዩት የአየር ፀባያት በተጨማሪ እስከ 18 የሚደርሱ አግሮ ኢኮሎጂ ዞን እንደያዙ ሙያተኞች ይገልፁታል:: ይህም በርካታ ተለያይነት ያላቸው ለዘርፉ ብዙ ጠቀሜታ ሊሰጡ የሚችሉ የጄኔቲክ ሀብቶች እንዲገኙ ምክንያት ሆኗል:: በኢትዮጵያ ብዝሃ ህይወት ኢኒስቲትዩት የጄኔቲክ ሀብት አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ዳይሬክተር ዶክተር ዘለቀ ወልደሚካኤል እንደሚገልፁት፤ የብዝሃ ህይወት ዕፅዋት እንስሳትና የደቂቅ አካላት ዘረመሎች በስብጥርና በተደጋጋፊነት የሚኖሩበት ስርዓተ ምድር ሲሆን፤ የእነዚህ ሀብቶች ይዘትና መጠንም የበርካታ ዘመናት የተፈጥሮ ውጤት ሂደት ነው::

የብዝሃ ህይወት ሀብቶችን በመንከባከብ በማበልፀግና በዘላቂነት በመጠቀም ረገድ አርሶ አደሩ የላቀ ሚና ተጫውቷል:: በሀገራችን ለረጅም ጊዜ በምግብነት ጥቅም ላይ የዋሉት ስንዴ፣ ምስር፣ ማሽላ ከቅጠላ ቅጠል ምግቦች ደግሞ እንደ ጐመን፣ ካሮት እና እንሰት የመሳሰሉት ሳይጠፉ የቆዩት አርሶ አደሩ ከምግብነት በተጨማሪ ለዘርነት በማከማቸት ስላቆያቸው ነው:: በድርቅ ወቅት አካባቢውን በመልቀቅ በሚሰደዱበት ወቅት የአዝዕርት እህሎችን በማሰሮ በማድረግ ጉድጓድ ውስጥ በመቅበር ክፉ ቀን ካለፈ በኋላ ወደቀያቸው በመመለስ ዘሮችን በመዝራት ቀጣይነት እንዲኖራቸው አድርገዋል:: አዝዕርቶች ለተለያዩ ምግብነት ማለትም ለዳቦ፣ ለእንጀራ፣ ለቂጣ፣ ለቅንጬ፣ ለገንፎ፣ ለንፍሮ፣ ለቆሎ ወዘተ በሚቀላቸው የምግብ አሰራር እውቀቱ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ በመዝለቁ ለአዘዕርቶችም ቀጣይነት የራሱን አስተዋፅኦ አበርክቷል:: አዝዕርቶችና ተክሎች በሚበቅሉበት አካባቢ ተጠብቀው መቆየታቸው የአፈር ኬሚካሎች መስተጋብር እንዲካሄድ የአየር መዛባት እንዳይፈጠር በአካባቢው ያሉ አራዊቶችዋ እንዳይጠፉና እንዲኖሩ አድርጓል:: ብዝሃ ህይወት ከዚህ በተጨማሪ የዕፅዋት በሽታዎች ሲያጋጥሙ ከመካከላቸው በሽታውን መቋቋም የሚችሉትን ለይቶ በማውጣትና በማራባት በበሽታ የተጠቃው ተክል ከመጥፋት እንዲድን ማድረግ ያስችላል:: ከዚህ አኳያ የጄኔቲክ ሀብታችን ለሌሎች ሀገሮች እንደተረፈ ጭምር መረዳት አያዳግትም::

ለአብነትም ከ10 ዓመታት በፊት በዶ/ር ሰለሞን ይርጋ የአራት ኪሎ ሳይንስ ፋኩልቲ ተመራማሪ "ህልውና" ብለው በፃፉት መጽሐፋቸው ላይ የጠቀሱትን ማንሳት ይቻላል:: በደርግ አገዛዝ ዘመን በአሜሪካ ካሊፎርኒያ ግዛት የሚገኝ አንድ የቢራ ገብስ አምራች ኩባንያ ገብሱ በበሽታ ይመታበታል:: በዚህ ሳቢያም ለፋብሪካው የሚቀርብ የቢራ ገብስ እየተመናመነ መጥቶ ፋብሪካው ወደ መዘጋት ይቃረባል:: ይሁን እንጂ የኩባንያው ባለቤቶች ፋብሪካውን ከመዘጋት ለማዳን ትኩረታቸውን በብዝሃነት ወደምትታወቀው ኢትዮጵያ ያደርጋሉ:: ከዚያም ወደዚህ በመምጣት ከካሊፎርኒያ ጋር ተመሳሳይ የአየር ፀባይ ካለው ወደ ሰሜን ሸዋ በማምራት ምርምር አድርገው በሽታውን መቋቋም የሚችል የገብስ ዘር ማግኘት በመቻላቸው ዘሩን ከኢትዮጵያ ወስደው አሜሪካ በመትከልና በማራባት ስንዴውን ከመጥፋት ከማዳን በተጨማሪ የቢራ ፋብሪካውን ከመዘጋት አድነውታል::

ይሁን እንጂ ከዚህ የጄኔቲክ ሀብት ሀገራችንም ሆነች የአካባቢው አርሶ አደሮች አንዳችም ጥቅም አላገኙም:: የገብሱ ዘር በዝርያ ተወልዷል ማለት ይቻል:: በሌሎች በሰለጠኑት ሀገሮች ቢሆን ቀድሞውኑ ሲጀመር የሌሎች ሀገሮች ተመራማሪዎች የጄኔቲክ ሀብት ሲፈልጉ በአግባቡና በሕግ አስፈቅደውና አስፈላጊውን ክፍያ በመፈፀም ነው:: በዚያን ዘመን በሀገራችን ይህን በሚመለከት ጠንካራ ተቋማትና ሕጐች ስላልነበሩ ችግሩ ሊከሰት ችሏል:: ከዚህ አንፃር የሀገራችን የጄኔቲክ ሀብት እንዲጠበቅ በማድረግ በኩል የብዝሃ ህይወት ጽህፈት ቤት ከፍተኛ ኃላፊነት ይጠበቅበታል::

ከዚህ ጋር በሚመሳሰል መልኩ በጤፍ ሀብታችን ላይ የተፈፀመው ደባ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው:: ጤፍ በአሁኑ ወቅት በውስጡ የያዘው ንጥረ ነገር ከፍተኛ በመሆኑና ከኮሌስትሮል የነፃ በመሆኑ በአውሮፓ ገበያ ጭምር ፍላጐቱ እያደገ መጥቷል:: በዚህ የተነሳ አንድ የሆላንድ ኩባንያ የፓተንት መብትን በሕግ ከኢትዮጵያ በመግዛት ምርቱን ለማስተዋወቅ የገባውን ውል በማፍረስ በራሱ ባለቤትነት ስም በማስተዋወቁ ጉዳዩ በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት እየታየ መሆኑን ዶ/ር ክበበው ሰለሞን የተባሉ የደብረዘይት እርሻ ምርምር ተቋም ተመራማሪ በቅርቡ መግለፃቸው አይዘነጋም::

ከዚህ አኳያ የጄኔቲክ ሀብት ከየት ሀገር ተገኘ የሚለው በራሱ በሕግ ዕውቅና የተሰጠው ሲሆን፤ ወስዶ ለመጠቀምም ሕግና ስርዓት ተበጅቶለታል:: ይሁን እንጂ ለዘመናት የጄኔቲክ ሀብት በዘፈቀደ ሲዘረፍ እንደቆየ የሚታወቅ ነው:: አሁን እየተደረገ ያለው የጥበቃ ጥረትም ተጠናክሮ መቀጠል የሚገባው ነው::

በአሁኑ ወቅት በዓለም በጣዕሙ ጥሩነት የሚታወቀው ቡና ከኢትዮጵያ የተገኘውና በተለያዩ የዓለም አህጉራት የተሰራጨው ኮፊ አረቢካ የተባለው ሲሆን፤ ኢትዮጵያንም በማስጠራት ላይ ይገኛል:: አብዛኛው በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚገኘው የቡና ተክል በተፈጥሮ የበቀለና በጥቅጥቅ ደን ውስጥ የሚገኝ ነው:: ለቡናው እንክብካቤ መደረጉ ደኑ እንዲጠበቅ ማድረጉ የሚታወቅ ነው:: ይህን በተመለከተ ዶ/ራ ዘለቀ ሲገልፁ፤ ቡና ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው የጄኔቲክ ሀብት በመሆኑ በዘላቂነት ጥቅም ላይ እንዲውልና ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ የአካባቢውን ስነምህዳር እንዲጠበቅ ማድረግ ያስፈልጋል:: ምክንያቱም ቡና በተፈጥሮው ጥላ ስለሚፈልግ ደኑ ከተመነጠረ ቡናውም ወደ መመናመን ስለሚያመራ የአካባቢ ጥበቃ ስራ መስራቱን አጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባው ይታመናል:: ዶ/ር ዘለቀ አክለው እንደሚያስረዱት፤ የጫካ ቡናና ሌሎች የብዝሃ ህይወት ሀብቶችን በተገቢው መንገድ መጠበቅ በተለይ በአካባቢው ያለው ማኅበረሰብ ከፍተኛ ኃላፊነት አለበት:: ከዚሁ ጐን ለጐንም የብዝሃ ህይወት የሚያስገኘው ሀብት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተገቢ በመሆኑ በዚህ ረገድ የወጡትን ሕጐችንና ደንቦች እንዲያውቁ በብዝሃ ህይወት ኢንስቲትዩት አማካኝነት ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ እየተሰራ ይገኛል::

ይሁን እንጂ በቡና አብቃይነት የሚታወቀው የሸካ አካባቢ ደን አደጋ እየተጋረጠበት መሆኑን አንዳንድ በአካባቢ ጥበቃ ስራ በቦታው የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ይገልፃሉ:: ይህን በተመለከተ የመልካ ኢትዮጵያ ማኅበር ስራ አስኪያጅ ዶ/ር ሚሊዮን በላይ ሲገልፁ አካባቢው በጥቅጥቅ ደን የተሸፈነ ከመሆኑም በላይ 10 ለሚሆኑ ወንዞች በምንጭነት ያገለግላል:: በዓመት ለ10 ወራትም ዝናብ በማግኘት ይታወቃል:: ነገር ግን በህዝብ ብዛት መጠናቀቅ የተነሳ ባለው የስራ መጣበብ ሰዎች በመሀል ደን ውስጥ በመግባት አካባቢውን በመመንጠር ቡና በመትከልና በማልማት የራሳቸውን ገቢ እየፈጠሩ ይገኛሉ:: ይህም በደኑ ላይ አሉታዊ ጫና እያስከተለ ይገኛል:: እንደሚታወቀው ቡና Cash Crop ነው:: በቀላሉ ተመርቶ ብዙ ገንዘብ የሚያስገኝ ነው:: ስለሆነም የአካባቢው ሰዎች በቡና ስራ በመጠመድ በደን ምንጠራ ስራ መሰማራታቸው ለወደፊቱ በብዝሃ ህይወት ላይ አሉታዊ ጫና መፍጠሩ ስለማይቀር ሁኔታው ከወዲሁ ቁጥጥር ሊደረግበት ግድ ይላል::

በጅማ ዩኒቨርሲቲ የባዮሎጂ ተመራማሪው ዶክተር ቁጡሱ ሁንዲራ ከላይ በዶ/ር ሚሊዮን የተገለፀውን አባባል ያጠናክራሉ:: በሀገሪቱ ቡና በሚበቅልባቸው አካባቢዎች የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች ለተለያየ ጥቅም በደኑ ውስጥ ያሉ ትላልቅ ዛፎችን ይቆርጣሉ:: የዛፉ መቆረጥ ቡናውን ፀሐይ እንዲያገኝ በማድረግ ምርት መጨመር ቢቻልም በተቃራኒው የአካባቢው አየር ንብረት እንዲለወጥ በማድረግ ከፍተኛ ጉዳት በማድረስ ላይ ይገኛል:: የተፈጥሮ ቡና በዓለም ተወዳጅነት ያለው ነው:: ጣዕሙም ተመራጭ ነው:: በባህርይው ጥላ ይፈልጋል:: ጥላው የሚገኘው ከደኖች ነው:: ደኖች ከተቆረጡ የቡናው ህልውናውም ያከትማል:: ስለዚህ ጥንቃቄ ማድረጉ ተገቢ ነው::

በአሁኑ ወቅት ሀገራችን ወደ ውጭ የምትልከው ቡና መጠን በመጨመር ላይ ይገኛል:: ለዚህ ሲባልም አዳዲስ የቡና እርሻ መሬቶች በመስፋፋት ላይ ይገኛሉ:: የቡና ችግኞችም የሚራቡትና የሚሰራጩትም የአካባቢውን ስነምህዳርና የአየር ፀባይ ከግምት በማስገባት ነው:: የቡና ፍሬ እንደማናቸውም

**በአሁኑ ወቅት በዓለም በጣዕሙ ጥሩነት የሚታወቀው ቡና ከኢትዮጵያ የተገኘውና በተለያዩ የዓለም አህጉራት የተሰራጨው ኮፊ አረቢካ የተባለው ሲሆን፤ ኢትዮጵያንም በማስጠራት ላይ ይገኛል። አብዛኛው በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚገኘው የቡና ተክል በተፈጥሮ የበቀለና በጥቅጥቅ ደን ውስጥ የሚገኝ ነው**

አዝዕርት የተለያዩ የጄኔቲክ ክፍሎች አሉት:: ችግኞቹም በደጋና በወይና ደጋ አየር ፀባይ ላይ መብቀል እንደሚችሉ ተረጋግጦ ለገበሬዎች ይታደላል:: በዛም መሰረት የተሻሻሉ ዝርያ ያላቸው ውጤታማነታቸውን ከማስመስከራቸውም በተጨማሪ ራሳቸውን ውርጭ ከሚያስጥለው በሽታ ለመጠበቅ ችለዋል:: እነኚህ ችግኞችም በተለያዩ አካባቢዎች እየተሰራጩ እንደሚገኙ ሙያተኛው ገልፀዋል::

የብዝሃነት ጠቀሜታ አካባቢን ከመጠበቅ በተጨማሪ የተለያየ የጄኔቲክ ማንነት ያላቸው አዝዕርቶች በተለያዩ አካባቢና እጅግ በጣም ተቃራኒ የአየር ፀባይ ባለበት አካባቢ ለመብቀል ጭምር አስችሏቸዋል:: እንደ ደብረዘይት የእርሻ ምርምር ተቋም ተመራማሪው ዶ/ር ክበበው ገለፃ፤ ለምሳሌ ጤፍ ከበረሃማ ቦታዎች ጀምሮ እስከ ከባህር ወለል 2,000 ሜትር በላይ በሚገኙ ደጋማ ቦታዎች መብቀል የቻለው በውስጡ ብዙ ተለያይ የሆኑ አይነቴዎችን በመያዙ ነው:: ስለሆነም የጄኔቲክ ሀብት ከተጠበቀ ድርቅም ሆነ የተፈጥሮ አደጋ ቢከሰት የጐርፍ መጥለቅለቅ ጭምር ቢመጣ የዘር አይነቶቹ ተለይተው በሚስማማቸው የመሬት አቀማመጥና የአየር ፀባይ እንዲበቅሉ በማድረግ ቀጣይነታቸውን ማረጋገጥ ይቻላል:: ይህም በራሱ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል::

በስርዓት በተጠበቀ ስነ ምህዳር ውስጥ የሚገኙ ነባር ዝርያዎች ከበሽታና ከድርቅ የተነሳ የሚከሰቱ የአካባቢ ተፅዕኖዎችን በመቋቋም የተሻለ ምርት እንደሚሰጡ የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልፃሉ::

በተመሳሳይ በኢትዮጵያም ሆነ በሌላው ዓለም የሚገኝ በቆሎና ዳጉሳ ከደጋ ጀምሮ በርሃማና በርሃ ቀመስ በሆኑ ቦታዎች በመብቀል ምርትን መስጠት መቻሉ በውስጡ የተለያዩ ዘረ መሎችን በመያዙ ነው:: ይህ ዘረመል በተክሉ ውስጥ ያለውን ባህርይና ማንነት ይወስናል:: ዘሩ በቆሎ ወይም ስንዴ ቢሆን ሁሉም ተመሳሳይ ነው ማለት አይደለም:: ፍሬው በቆሎ ሆኖ የሚበቅልበት ቦታ ይወስነዋል:: በደጋማ ቦታ ላይ መተከል ያለበት በቆሎ ቆላማ ቦታ ላይ ቢተከል ፍሬ አይሰጥም:: ይህንን ሁሉ ጉዳይ ሙያተኞችም ሆነ አርሶ አደሮች በተገቢው በማወቃቸውና ስራ ላይ በማዋላቸው የሀገራችን ብዝሃ ሀብት እንደተጠበቀ ሊቆይ ችሏል::

በአሁኑ ወቅት በሀገራችን አርሶ አደሮች በኅብረት ስራ ማኅበሮቻቸው አማካኝነት የተለያዩ ጄኔቲክ መሰረት ያላቸውን የዘር እህሎችን ማለትም ድርቅን መቋቋም፣ ለበሽታ የማይበገሩትንና ምርታማነታቸው ከፍተኛ የሆኑትንም በመለየት በመጋዘኖች አከማችተው እንደየፍላጐታቸው እየተጠቀሙባቸው ይገኛል:: ይህም ለብዝሃነት መጠበቅ የራሱን እገዛ እያደረገ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ በሀገራችን በሚገኙ 13 የአዝዕርት የምርምር ጣቢያዎች ውስጥ የተለያየ ዘረመል መሠረት ያላቸው እህሎች በስርዓት ተቀምጠው ምርምር የሚደረግባቸው ሲሆን፤ በምርምር የተሻሻሉ ዘሮችም ተመርጠው ለአርሶ አደሩ እንደሚደርሱ ዶ/ር ዘለቀ ይገልፃሉ:: ከዚህ በተጨማሪም በኢትዮጵያ የጄኔቲክ ኢንስቲትዩት ውስጥ የዚህ መሰሉ ስራ እየተከናወነ ይገኛል::

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ከ6 ሺህ በላይ የዕፅዋት ዝርያዎች የሚገኙ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥም ከ10 እስከ 12 በመቶ የሚሆኑት በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ እንደሚገኙ የጄኔቲክ ባለሙያዎች ይገልፃሉ:: እኒህ ዝርያዎቹ እንዲበራከቱ ያደረገውም ሀገራቱ እጅግ በጣም የተበራከተ የመልክዓ ምድር ገጽታና የአየር ፀባይ በመያዝዋ ሲሆን፤ አብዛኛውም ዱር በቀል ነው:: አብዛኛዎቹም በደን፣ በሣራማ፣ በቁጥቋጦ እንዲሁም በርጥበታማ መሬቶች ላይ ይገኛሉ:: ስለሆነም ስነምህዳሩ ተጠብቆ እንዲቆይ ለብዝሃ ህይወት ክብካቤ ማድረጉ ጠቃሚ ነው::■

# ሀገራችንን ለማሸበር ሲዶልቱ የሚውሉ...


ተቃዋሚ ፓርቲዎችን እኛ በሶስት ከፍለን ነው የምናየው፡፡ በአግባቡ ጨዋታውን ለመጫወት የሚፈልጉና መጫወት የጀመሩ ፓርቲዎች አሉ፡፡ እነዚህ ለኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ትልቅ አስተዋፅኦ ስለሚያበረክቱ ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው፡፡ አንዳንዴ ደግሞ ወጣ ገባ የሚሉ ፓርቲዎች ወጣ ገባ ማለቱን ትተው በጨዋታው ሕግና ሥርዓት መሠረት መታቀፍ አለባቸው፡፡ በሀገራችን ዲሞክራሲ እንዲያብብ ከተፈለገ ኃላፊነቱ የመንግሥት ብቻ ሊሆን አይችልም፣ የሁሉም አካላት ኃላፊነት ነው ሊሆን የሚገባው፡፡ ከዚህ ተነስተን ስናይ አንዳንዶቹ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያቸው በውጪ ሀገር የሆነ፣ የአመጽና ብጥብጥ ውይይትና ስብሰባ ሲያካሂዱ የሚከርሙ ለሀገራችን ፖለቲካ ፋይዳ የሌለው ጉዞ የሚጓዙ እንዳሉ እናውቃለን፡፡ ከእነዚህም ጋር ያለን ግንኙነት የሚመሠረተው በተነጋገሩት ጉዳይ አይደለም፤ በሚያደርጉት ድርጊት ላይ ነው፡፡ ስለዚህ ይህንን የተነጋገሩትን ነገር በድርጊት ላይ ነው፡፡ ስለዚህ ይህንን የተነጋገሩትን ነገር በድርጊት ለማስደገፍ ሲሞክሩ መንግሥት ሕግና ሥርዓትን ለማስከበር ይገደዳል፡፡ ይሄ ግልጽ ሊሆን ይገባል፡፡ እኛ በተደጋጋሚ እየተናገርን ያለነው ለዲሞክራሲን፣ ለሕግ የበላይነት መኖር አለበት፡፡ ይሄ የሕግ የበላይነት ደግሞ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ብቻ ሣይሆን ለገዢው ፓርቲም፣ ለመንግሥት የሚሠራ ነው፡፡ ስለዚህ የተቃዋሚ ፓርቲ አካላት መሪያቸውን ታሠሩ ከማለታቸው በፊት ለምን ታሠሩ የሚል ጥያቄ አንስተው መወያየትና ሠላማዊ፣ ዲሞክራሲያዊና ሕጋዊ የሆነውን መንገድ መምረጥ አለባቸው፡፡ ከዚህ ውጪ ተኬዶ መንግሥትን ለመፈታተን ሙከራ የሚያደርግ አካል ካለ ተገቢ አይሆንም፡፡ መንግሥት ሕግና ሥርዓትን የማስከበር ግዴታ አለበት፡፡ ስለዚህ መንግሥትን መፈታተን ጠቃሚና ገንቢ ነው የሚል እምነት የለኝም፡፡ አንዳንዶቹ በጣም በስፋት የልማት ሥራ በሚሠራበት አካባቢ ከጠየኩኝ መንግሥት አይሰጥም፣ በሚል መንግሥትን አጣብቂኝ ውስጥ ለመክተት ሠላማዊ ሰልፍ በእነዚህ ቦታዎች ማካሄድ አለብኝ ብለው መንግሥትን ለመፈታተን ብለው የሚጠይቁ አሉ፡፡ ይሄ ሲሆን መንግሥት ግዴታ ስላበት መንግሥትን መፈታተን አይችልም፣ አይገባም፡፡ ስለዚህ ይሄ በሕጉ መሠረት መከናወን አለበት የሚል መልስ እንሰጣቸዋለን፡፡

አንዳንዶቹ ደግሞ በኢትዮጵያ ፓርላማ አሸባሪ ተብለው በተሰየሙ አካላት ጋር በቀጥታ እየተገናኙ የሀገራችንን ሠላም ለማወክ የሚሠሩ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች አሉ፡፡ እዚህ ላይ ግልፅ ማድረግ የምንፈልገው፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሕገወጥ ናቸው አላልንም፡፡ በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ግለሰብ አመራሮች ከአሸባሪ ቡድኖች ጋር ሀገራችንን ለማሸበር በየጊዜው እየዶለቱ የሚውሉ ኃይሎች በመረጃና ማስረጃ ስናረጋግጥ እነዚህ በሕግ እንዲጠየቁ እናደርጋለን፡፡ ሁሉንም ነገር ፍርድቤት ነው የሚወስነው፡፡ እኛ የምንመክረው እነኚህ ጠቃሚ ያልሆነ መንገድ የመረጡ አካላት መንግሥት መቼም ጊዜ ቢሆን ሕግ የማስከበር ሥራ ስለማያቆም ሕጋዊ በሆነ መንገድ ብቻ ቢሄዱ ለሀገራችም፣ ለዲሞክራሲም፣ ለፓርቲውም እድገት ይጠቅማል የሚል እምነት አለን፡፡ ከዚህ ውጪ ሄደው መንግሥት ዝም ይላል ብለው ካሰቡ ዝም እንደማይል በተደጋጋሚ ገልፀናል፡፡

በአፍሪካ ቀንድ ሀገራት እንደምናየው ሀገራችን እዚህም እዚያም ቦምብ የሚፈነዳባት ሀገር እንድትሆን መንግሥት አይፈቅድም፤ ይሄ ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡ እናም ሠላማዊ፣ ሕጋዊ፣ ዲሞክራሲያዊ፣ ለወከለውም ሕዝብ ክብር በሚሆን መንገድ ሁሉም አካል መንቀሳቀስ አለበት የሚል እምነት አለን፡፡ ስለዚህ ውንጀላው መንግሥት አሠረ ሳይሆን ለምን መንግሥት አሠረ የሚለው ነገር በሚገባ ሊያዝ ይገባል፡፡ ከዚያ ባሻገር ግን ሠላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብታቸው የተከበረ መሆን አለበት፡፡ ከዚህ ችግር ውጭ የሆኑ ፓርቲዎች ሠላማዊ ሰልፍ እያደረጉ ነው፡፡ መንግሥት ይህን ፓርቲ ስለሚወድ፣ ያንን ስለሚጠላ አይደለም፡፡ ልዩነቱ ሕጋዊና ሕገወጥ ነገር የመከተልና ያለመከተል ብቻ ነው፡፡

- በቅርቡ በባህርዳር ከተማ ከእምነት ቦታ ይገባኛል ጥያቄ ጋር በተያያዘ ሰልፍ የወጡ ሰዎች ላይ ጉዳት ስለመድረሱና ሠላማዊ ሰልፎችን በዘመናዊ ዘዴ መቆጣጠር ስለሚቻልበት ሁኔታ፣

ሠላማዊ ሰልፎችን በተመለከተ በሠላማዊ መንገድ ወይንም በሰለጠነ መንገድ እነዚህ ሰልፎች ተስተናግደው ወደ መቋጫቸው እንዲደርሱ ማድረግና በሰው ሕይወትም ሆነ ንብረት ላይ አደጋ እንዳይደርስ በማድረግ ዙሪያ ሁሉም አካላት የራሳቸውን ሚና መጫወት ይገባቸዋል፡፡ በመንግሥት የጥበቃ ኃይሎች ብቻ አይደለም፣ ሠላም የሚመጣው፡፡ እሱን የሚያካሂዱ አካላት ራሳቸው ሠላማዊ መንገድ መከተል አለባቸው፡፡ በዚህ ደግሞ የመንግሥት ጥበቃ ኃይሎች ሰልፉ በሠላማዊ መንገድ እንዲጠናቀቅ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ይህን የማድረግ ያለፉት ሰባት ዓመታት የፌዴራልም ሆነ የክልል ፖሊሶች ሠላማዊ ሰልፍን የሚያስተናግዱበት ሥልጠና ሆነ ቁሳቁስ ጭምር እንዲታጠቁ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡ እንግዲህ በዚህ መሠረት ሠላማዊ ሰልፎች ያለልዩ ትዕዛዝ የሚጠናቀቁበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡ በባህርዳር ከተማ በተካሄደ ሰልፍ ምክንያት የተወሰነ ጉዳት መድረሱ ይታወቃል፡፡ ይሄ ጉዳት ምክንያቱ ምንድነው የሚለው ተጣርቶ ነው የሚታወቀው፡፡ በፀጥታ ኃይሎች ነው የተከናወነው ወይስ የተለያዩ የራሱ መንገድ አለው የሚለው ተጣርቶ ነው ሊታወቅ የሚችለው፡፡ በመጣራት ላይ ያለ ጉዳይ ስለሆነ የመጨረሻ ሃሳብ መስጠት አይቻልም፡፡ ተጣርቶ በሚመጣበት ጊዜ ማንነው ተገቢውን ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡ የመንግሥት



**የበጀትና የአቅም ችግር አለብን። በአውሮፓና በተለያዩ ቦታዎች ምርጫ ስለምንታዘብ አሁን ባለው ሁኔታ ገንዘባችንን በከፍተኛ የምርጫ እንቅስቃሴ ለመመደብ የምንችልበት ሁኔታ ላይ አይደለንም። የዘንድሮው የምርጫ መታዘብ ይለፈን የሚል ጥያቄ አቅርበዋል**

አቋም ግን የሠላማዊ ሰልፍን ማስተናገጃ መንገዶችና የፀጥታ ኃይሎች ሊያካሂዱት የሚገባ ሥነሥርዓትና ጥበቃ በተመለከተ ሕግና ሥርዓት አለ፡፡ የፖሊስ መዋቅሩ የራሱ የሥነምግባር ደንብ አለው፡፡ ከዚህ የሥነምግባር ደንቡ ወጣ ያለ አካሄድ የተከተለ አካል ካለ በደንቡ በተቀመጠው መሠረት ተጠያቂ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይሄ በእኛ ሀገር ብቻ አይደለም፣ በተለያዩ የሰለጠኑ ሀገሮችም ጭምር ፖሊስ በወንጀል መከላከል ዙሪያ ሰልፍ በሚካሄድበት ጊዜ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ተጠያቂ የሚሆንባቸው መንገዶች አሉ፤ ነፃ የሚሆንባቸውም አሉ፡፡ አሁን ባልተጣራ ነገር ችግሩ ያለው ፖሊስ ጋር ነው ወይንስ ሰልፈኛው ላይ ነው የሚለው ነገር አሁኑኑ መናገር የሚቻል አይሆንም፡፡ በሒደት የምናየው ይሆናል፡፡ ይህም ሆኖ ግን በመንግሥት በኩሉ ሠላማዊ ሰልፎች በአግባቡ ለማስተናገድ የሚያስችል የቁሳቁስም ሆነ የሕግ፣ የሥነምግባር ደንቦችም ተዘጋጅተው ሁሉም አካል ሰልፉ ሠላማዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ለማድረግ ኃላፊነት መውሰድ አለበት፡፡ አንዳንድ ጊዜ በሰልፈኙውም ውስጥ ጋጠወጥነት የሚያጋጥምበት ጊዜ ይኖራል፡፡ ግማሹ ባዶ እጁን ይወጣል፣ ግማሹ ታጥቆ ይመጣል፡፡ ታጥቆ የሚወጣው ኃይል የፀጥታ ኃይሉን መሣሪያ ለመንጠቅ የሚሞክር ከሆነ የመከላከል እርምጃ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በዚህን ጊዜ ጉዳት ሊመጣ ይችላል፡፡ ሰልፈኛው ራሱ ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ሰልፉን ማካሄድ አለበት ማለት ነው፡፡ የፀጥታ ኃይሎች ሊያከናውኑት የሚችሉትን ሠላም የመጠበቅ ሁኔታ በማያውክ መንገድ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡ አንዳንዴ ከሰልፈኛው የሚመጡ ጥቃቶች አሉ፡፡ መንግሥትን ለማጠልሸት ሲሉ ሰልፈኛው ላይ የሚተኩሱበት ሁኔታ አለ፡፡ ይሄን በማድረግ መንግሥት ነው ጥቃት ያደረሰው ለማለት የሚሄዱ አሉ፡፡ ስለዚህ ሁኔታው በሁሉም አቅጣጫ መታየት ያለበት ነው ብሎ መውሰድ ተገቢ ይሆናል፡፡

- የአውሮፓ ኅብረት ምርጫ ታዛቢ ቡድን አለመሳተፍን በተመለከተ፣

የአውሮፓ ኅብረት ምርጫ መታዘብን በተመለከተ የአውሮፓ ኅብረት በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል በዘንድሮው ዓመት በሚካሄደው ምርጫ ለመታዘብ እንደማይችሉ አስታውቀዋል፡፡ ለዚህ የሰጡት ምክንያት የበጀትና የአቅም ችግር አለብን፡፡ በአውሮፓና በተለያዩ ቦታዎች ምርጫ ስለምንታዘብ አሁን ባለው ሁኔታ ገንዘባችንን በከፍተኛ የምርጫ እንቅስቃሴ ለመመደብ የምንችልበት ሁኔታ ላይ አይደለንም፡፡ የዘንድሮው የምርጫ መታዘብ ይለፈን የሚል ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ ድሮም ቢሆን የምርጫ ዋና ባለቤቶች የኢትዮጵያ ምርጫ ተፎካካሪዎች ወይንም የፖለቲካ ፓርቲዎችና የኢትዮጵያ ሕዝብ ናቸው፡፡ ስለዚህ ምርጫውን እነሱ ታዘቡትም፣ አልታዘቡትም ወሳኙ ጉዳይ እኛ እጅ ነው ያለው፡፡ ዴሞክራሲ በሀገራችን እንዲያብብ ለማድረግ ኃላፊነቱና ተነሳሽነቱ በእኛ እጅ ነው መሆን ያለበት፡፡ ስለዚህ ምርጫችንን ዴሞክራሲያዊ፣ ሠላማዊ፣ ተአማኒነት ያለውና ነጻ ለማድረግ ቢታዘቡም፣ ባይታዘቡም እኛ ሥራችንን መሥራት ይገባናል፡፡ ከዚህ በተረፈ የአፍሪካ ህብረት ምርጫ ታዛቢ ቡድን እንደሚልኩ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪ ሀገራዊ የሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሙያ ማህበራት፣ የሕዝብ አደረጃጀቶች፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ወኪል የሆኑ አካላት ምርጫውን ይታዘቡታል፡፡ ምርጫው ሠላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ተአማኒ፣ ነፃ እንዲሆን የበኩላችንን ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡



## ትዝብትን በጨዋታ

በአሸናፊ ደምሴ ......... demissieashenafi@gmail.com

# እረፍት በየፈርጁ. . .

ውዶቹ እንደምን ሰንብታችኋል? . . . ዛሬ እረፍት ተኮር ወሬ ላይ እንጨዋወታለን። መቼም ሁላችንም በዘፈቀደ እንደምናውቀው፤ ሳይንስ ደግሞ በምርምር እንዳረጋገጠው የሰው ልጅ እረፍት በእጅጉ ያስፈልገዋል። ምክንያቱም የአካልና የመንፈስ ድካም የሰው ልጆች የዝለት ምንጭ፤ ውጤትንም የሚያቀጨጭ ነውና። የሰው ልጅ በመንፈሱ ይደክማል። ይህም ማለት በመንፈሳዊ ህይወቱና በእዝነ- ልቦናዊ ማንነቱ ውስጥ የሚገለጥ ድክመት ነው። አንድ ሰው በመንፈሱ ሲደክም ተስፋ ይቆርጣል፤ ትዕግስት ያጣል፤ የመኖር ትርጉሙን ይጠይቃል፤ በሰዎችም በህይወትም ሆነ በራሱ ላይ ያለው መተማመን በእጅጉ የወረደ ይሆናል። ከዚህም ለመዳን አንድ ሰው ድንጋይም ቢሆን የሚተማመንበትና ሀሳቡን የሚያሳርፍበት አምላክ ይሉናል የስነ-ልቦና ተመራማሪዎች።

በሌላ በኩል ደግሞ ሰው በአካሉ ሊደክም ይችላል። በብዙ ከመስራት፤ እረፍት አልባ ከመሆንና በኑሮ ጫና ውስጥ ድንገት በመውደቅ ሰዎች በአካል ሊደክሙ፤ በፍጥነት ሊያረጁና አካላዊ ለውጣቸው የማይደበቅ ሊሆን ይችላል።

ብዙ ሰዎች ብዙ በደከሙ ቁጥር፤ ብዙ በለፉ ቁጥር፤ ብዙ እንቅልፍ አጥተው በሰሩ ቁጥር ወደስኬት የሚያመሩ ይመስላቸዋል። የሚሆነው ግን በተገላቢጦሽ ነው። ይህ የአካል መዛልና መድከም ደግሞ በገቢር የሚገለፅበት አጋጣሚ ብዙ ነው። አንዳንዶች ራሳቸውን እስከመሳትና መውደቅ፤ አንዳንዶች በጭንቀት ብዛት የአእምሮ መቃወስና የህክምና እርዳታ እስከመሻት የሚደርሱበት ሁኔታ አለ።

እዚህች'ጋ ለዛሬ የድካምና የእረፍት ትዝብት አዘል ጨዋታችን መቆዘሚያ ትሆነን ዘንድ አንዲት የዩኒቨርስቲ ጊዜ ትውስታዬን ላካፍላችሁ። ወቅቱ ክረምት መዳረሻ በመሆኑ የሦስተኛ ዓመት ትምህርታችን የማጠቃለያ ፈተና የምንወስድበት ሰሞን ነው። እንደሚታወቀው፤ ዩኒቨርስቲዎች በፈተና ሰሞን የተወረሩ ከተሞችን፤ የተማረኩ የጠላት ወረዳዎችንና ቀናቸው ሳይቀር የጨለማ ግርማ ሞገስን የሚላበሱ ናቸው። ተማሪው በየመፅሐፍት ቤቱ፤ በየመኝታ ክፍሉ፣ በየክላስና በየጥጋጥጉ ደብተሩ ላይ አድፍጦ እና መሸጎ የሚቆይበት ወቅት ቢኖር ይኸው የፈተና ሰሞን ነው።

ይህ በሚሆንበት አንድ ሰሞን ጓደኛችን በቁጥ - ቁጥ የለመደውን የእንቅልፍ ጊዜ እንደጨረሰ፤ ገና በ10 ሰዓት ወደ መመገቢያ አዳራሽ "በካፌ ሰቃይነት" ተገኘ (ምነው ቢባል በጊዜ በልቶ፣ በጊዜ ላይብረሪ ገብቶ "ሲቸክል" ለማፈር ትጥቅና ስንቅ ለማሟላት መሆኑ ነው።")

እንዳሰበውም ከካፌው የእፍታውን ምግብ አግኝቶ እንደወጣ በቀጥታ ያመራው ወደቤተ-መፃሕፍት ነበር፤ ወደ "ኬኔዲ ላይብረሪ"። አንድም ቀን አይቶት የማያውቀውን ማስታወሻ ደብተርን፤ "ሃንድ አውት" ብዙ ያላጠናቸው ቁምነገሮች የያዘውን ትምህርት ነገ ጠዋት ፈተና ሊቀመጥበት ጊዜ ተቆርጦለታል።

ወዳጃችን የንባብ ማራቶኑን ተያያዘው። ለእራት ጭር ብሎ የነበረው ቤተ-መፅሀፍቱ ተመልሶ መሙላትና ተማሪው ቦታ ፍለጋ መተራመስ ቢጀምርም ይህ የምላችሁ ወዳጄ የከመራቸውን ወረቀቶችና መፃሕፍቶች እያነሳ እየጣለ በንባብ ተወጥሮ ነበር።

እኩለ-ሌሊት ከተጋመሰም በኋላ ወዳጃችን ከንባቡ አልተነሳም። ስጋ ፈራሽ ብቻ ሳይሆን ደካማም በመሆኑ ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት አካባቢ ከሰሞኑ እንቅልፍ ማጣት ጋር ተጫጫነው ወንድማችን አንድ ጊዜ በእንቅልፍ ልቡ ከጠረጴዛ ጋር በመጋጨቱና ሁኔታውን ላዩት ተማሪዎችም የሳቅ ምንጭ በመሆኑ አፍሮና አንገቱን አቀርቅሮ ከቤተ-መፃህፍቱ ወጣ።

ወደመኝታ ክፍሉ (ዶርሙ) ሲገባ ደግሞ ከርሱ በተሻለ እረፍት ያገኙት ጓደኞቹ "ቸክለው" ሲያነቡ ደረሰ። የመኝታ ሞራሉ ጠፍቶ፣ እንደአዲስ ማንበብ ጀመረ። ከእንቅልፉ እየታገለም ቢሆን፤ እግሩን ውሃ ውስጥ ዘፍዝፎም ቢሆን፤ ገላውን እየታጠበም ቢሆን ሌሊቱን ሙሉ ሲያነብ ፀሐይ ወጣች።

ለሁለት ሰዓት ተከል ፈተና ወደአዳራሽ ከመግባቱ በፊት እንደነገሩ ቁርስ አደረገ። የሚያስቀውና የሚያሳቅቀው ነገር የተከሰተው በፈተና ክፍሉ ወንበር ላይ ከተቀመጠ በኋላ ነበር። ስንት የለፋበት፣ ስንት እንቅልፉን ያጣለት፣ ስንት የተሳቀበት ጥናቱ ሁሉ ውሃ በላው። ፈተና ወረቀት ፊቱ ሲቀርብለት ስሙን ፅፎ የተወሰኑ መልሶችን ሞክሮ ሲያበቃ ነበር፤ እንቅልፍ ያንገላጀጀው። ይህም ብቻ አይደለም በስተመጨረሻ ራሱን ስቶ ከመፈተኛ ክፍሉ በሰዎች እርዳታ ተደግፎ ነበር ወደህክምና ቦታ የተወሰደው። ይህ በተማሪነት ህይወቴ የማልረሳው ክፉ ትዝታዬ ነው። ይህ ታሪክ ብዙ የሚነግረን ነገር እንዳለ አስባለሁ። ዋናው ነገር ግን የሰው ልጅ በአካልም በመንፈስም የተረጋጋና እረፍትን የቀመሰ ሊሆን እንደሚገባ ይተርካል።

ሌላ ጨዋታ እናምጣ፡ ሰሞኑን ሞባይሌ ድንገት ቀጥ አለች። እንደባለሙያዎቹ አጠራር "ስታክ" እያደረገች፤ የሞባይል ጥገና ባለሙያ ዘንድ ሄድኩ። የሞባይሌን ችግር ዘርዝሬ ሳላበቃ "ምንጊዜም ሞባይልህ ድንገት ቀጥ ሲል የመጀመሪያ ተግባርህ መሆን ያለበት "ሪ-ስታርት" ማድረግ ነው፤ የሚል ምክር ለገሰኝ።

እውነትም ለካ ሞባይላችን ሳይለንት፤ ቫይብሬት፣ ስዊችድ ኦፍ እንዳለው ሁሉ ሪ-ስታርትም አለው። ይህ ማለት እንደ አዲስ መነሳትን የሚያመለክት ነው። ሞባይላችንና ከምፒዩተራችን መኪኖቻችንና ኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎቻችን ራሱ አርፈው መነሳትን "ሪ-ስታርትን" የሚፈልጉ ከሆነ እኛ ደግሞ በእጅጉ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን እረፍት ያስፈልገናል ማለት ነው።

አንድ ቀን ግን ሚስት
የትዕግስቷ ግድብ ፈረሰ፤ በቁጣ
ተናገረችው፤ አፍ አውጥታም
"አማረኝ" አለችው። በድካም
የዛለ አካሉን አልጋው ላይ
አሳርፎ እንቅልፉን ሳያስብ
የሚያገኘው ባል ግን
የሚከተለውን ምላሽ ሰጠ፤
"ተይ እንጂ ውዴ! እኔስ ብሆን
አላሳዝንሽም እንዴ?. . .
እንቅልፍ አጥቼ፣ ቆሎ በልቼ፣
ድንጋይ ፈልጬ፣ አንቺን
"አቅፌ" (በጨዋ አነጋገር መሆኑ
ነው) እችለዋለሁ እንዴ?"
ብሎላችሁ እርፍ።

ከመሰነባበታችን በፊት የእረፍት ነገር በህይወታችንና በትዳራችንም ቢሆን ምን ያህል አስፈላጊ ስለመሆኑ የምታሳይ ወግ እንካችሁ። ሰውዬው እንደሰው ትዳር መስርቶ ልጆችንም ወልዶ በቀን ሥራ ደፋ ቀና የሚል ባተሌ ነው። ታዲያላችሁ ሚስት የቱንም ያህል በቤቱ ሥራ ተጠምዳ ብተውል ምሽቱን ከብርድ ልብሱ ሙቀት በዘለለ ልፊያ ያምራት ኖሮ ባል ሳይረዳላት ብዙ ቀናት አለፉ። ሰውዬው ደግሞ ድንጋይ ሲሸከም፣ አሸዋ ሲዝቅ፣ ጭቃ ሲያቦካ፣ የሰውን ቤትና አጥር ሲገነባ ውሎ ደክሞት የሚገባ "ባተሌ" በመሆኑ ነገሩን ልብ አላለውም ኖሯል።


አንድ ቀን ግን ሚስት የትዕግስቷ ግድብ ፈረሰ፤ በቁጣ ተናገረችው፤ አፍ አውጥታም "አማረኝ" አለችው። በድካም የዛለ አካሉን አልጋው ላይ አሳርፎ እንቅልፉን ሳያስብ የሚያገኘው ባል ግን የሚከተለውን ምላሽ ሰጠ፤ "ተይ እንጂ ውዴ! እኔስ ብሆን አላሳዝንሽም እንዴ?. . . እንቅልፍ አጥቼ፣ ቆሎ በልቼ፣ ድንጋይ ፈልጬ፣ አንቺን "አቅፌ" (በጨዋ አነጋገር መሆኑ ነው) እችለዋለሁ እንዴ?" ብሎላችሁ እርፍ። እንግዲህ አካል ሲደክም "በዚያች" ነገር ላይ እንኳን ምን ያህል እንደሚያሰንፍ አያችሁልኝም አይደል?

እናላችሁ እረፍት በእጅጉ አስፈላጊ ነው። አንድ ሰው ሲሞት (ሲያርፍ) ምናልባት ለሚቀጥለው አለም እንደገና ታደሶ ሊነሳ "ሪ-ስታርት" ሊያደርግ መሆን አለመሆኑን ማን ያውቃል? በመሆኑም እረፍት በየፈርጁ ይታረፋል ብለን ምን ይለናል? ምንም። ቸር እንሰንብት።

## ኪነጥበብ-ዜና

በአሸናፊ ደምሴ

### "የመሀን ምጥ" ፊልም እየታየ ነው




በሞመንተም ሚዲያ ፕሮዳክሽን ተዘጋጅቶ የቀረበው "የመሀን ምጥ" ፊልም በመታየት ላይ ነው። በማህበረሰባዊ ስነ-ልቦና ጉዳይ ላይ አተኩሮ የተሰራው ይህ ልብ አንጠልጣይ ፊልም የ1:40 ደቂቃ ጊዜን ይፈጃል።

"የመሐን ምጥ" ፊልም ዳይሬክተር ዳንኤል በየነ እና ሞመንተም ሚዲያ ፕሮዳክሽን ሲሆኑ፤ በትወናው ደሳለኝ ሃይሉ፣ ፀጋነሽ ሃይሉ፣ ወለላ አሰፋ፣ ሽመልስ ለጋስ፣ መፍትሄ ንጉስ ብርሃኑ ሽብሩ፣ ስዩም ተፈራ እና ሌሎም ተዋንያን ተሳትፈውበታል።

ተሰርቶ ለመተናቀቅ የሁለት አመታትን ጊዜ የወሰደው ይህ ፊልም፤ ኤዲት የተደረገው በዳንኤል በላይ፤ ካሜራውን የሰራው ብስራት ጌታቸው፤ ፕሮዳክሽን ማኔጀሩ ታምራት ገዛኸኝ ሲሆን፤ ኤክስኪውቲቭ ፕሮዲሰሩ የሺወርቅ ወልደሄር መሆናቸው ታውቋል።

### "የበረዶ ስር ፍሞች" መፅሐፍ ለንባብ በቃ

ከዚህ ቀደም "የጨለማ ግሳቶች" በሚል ስራዎቹ የሚታወቀው እሙሻ አስራ አንድ ታሪኮችን የያዘ "የበረዶ ስር ፍሞች" የተሰኘ የአጫጭር ልቦለድ ስብስቦችን ለንባብ አበቃ።

"የበረዶ ስር ፍሞች" መፅሐፍ 171 ገጾች ያሉት ሲሆን ዋጋው ደግሞ 40 ብር መሆኑ ተገልጿል። ፀሐፊው በስደት ሆኖ በስራዎቹ ውስጥ የምወዳት ሰፈሬ ካሳንቺስ ስትወረገረግ አንብቧት ይለናል።

"የበረዶ ስር ፍሞች" በመፅሐፍ ስብስቡ ሳይቤሪያና ዳሎል፣ የሺህ ዘመን ቀጠሮ፣ ግንድና ቅርንጫፍ፣ እማማ ስንዴ፣ ሞዛዛ ፍቅር፣ ፕሬዝዳቱ፣ አልተለያይቶም፣ ፈረጃ፣ እንቁጤ፣ ችንቻው እና ቴጌዮጵያ የተሰኙ ታሪኮችን ይዟል።



በዚህ ዓምድ ስር የሚወጡ ጽሁፎች የፀሐፊውን እንጂ የኤዲቶሪያሉን አቋም አያንፀባርቁም

# አንድነትና መኢአድ ትክክለኛ አመራሮቻቸውን አላሳወቁም

## • የመኢአድ የአመራር ምርጫ ሕግና ሥርዓትን የጣሰ ነው

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርዱ የጊዜ ሰሌዳ በማዉጣት የምርጫ እንቅስቃሴዉም በዚያዉ አግባብ እየተከናወነ ይገኛል። በመጪዉ እሁድ በመላ አገርቱ በየምርጫ ጣቢያዉ መራጩ ህዝብና የፓርቲ ወኪሎችም በተገኙበት የህዝብ ታዛቢዎች ምርጫ ይካሄዳል። (ከአዘጋጁ:- እሁድ ታህሳስ 12 ቀን 2007 ዓ.ም መከናወኑ ይታወሳል) በገለልተኝነት የምርጫዉን ሂደት የህዝብ ዓይንና ጆሮ በመሆን የሚታዘቡ፣ የምርጫዉን ፍትሃዊነትና ዴሞክራሲያዊነት የሚያረጋግጡ ናቸዉ። የፖለቲካ ፓርቲዎች የመወዳደሪያ ምልክቶቻቸዉን እስከ ኅዳር 30 ድረስ ባለዉ ጊዜ ዉስጥ መርጠዋል። ቦርዱም ሰሞኑን በካሄደዉ 004/2007 መደበኛ ስብሰባ ፓርቲዎቹ የመረጡዋቸዉን ምልክቶች ከተሻሻለዉ የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ አኳያ መርምሮ ዕዉቅና ሰጥቷል። ይሁን እንጂ በሂደቱ ቦርዱን ያጋጠሙት ቀላልና ጥቂት ችግሮች ነበሩ። በመጀመሪያ የተመረጡት ምልክቶች አልፎ አልፎ መመሳሰል፣ ለህትመት ስራ አመቺ ያለመሆንና ግልጽነት የሚጎድላቸዉ ሲሆን ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተገቢዉን ማስተካከያ እንዲያደርጉ ቦርዱ አስፈላጊዉን አመራር ሰጥቷል።

በሁለተኛ ደረጃ ጠንከር ያለዉ ችግር በሁለት የፖለቲካ ፓርቲዎች ጉዳይ ነበር። እነኚህ ፓርቲዎች የመወዳደሪያ ምልክቶቻቸዉን ለጊዜዉ በሆደ ሰፊነት እንዲያስገቡ የተደረገ ቢሆንም በየፓርቲዎቹ የዉስጥ ጉዳይ ምክንያት በአመራሮች መካከል መከፋፈል በመፈጠሩ የፓርቲዎቹ ህጋዊና ትክክለኛ አመራሮች ያለመታወቅ ችግር ነበር። በመኢአድ ዉስጥ በተፈጠረ የዉስጥ ዲሞክራሲ እጦት ምክንያት ከ2003ዓ.ም ጀምሮ የምርጫ አዋጁንና የፓርቲዉን መተዳደሪያ ደንብ ባከበረ መልኩ ጠቅላላ ጉባኤ አካሂዶ ለቦርዱ ሪፖርት በማድረግ ማጸደቅ ያለመቻል፤ በየጊዜዉ "ደንብ አሻሽለናል፣አመራር ቀይረናል፣አዲስ ተመርጠናል" የሚሉ አካላት መፈጠሩ ትልቅ ችግር ነበር። በዚህ መሰረት ሐምሌ 14 ቀን 2005ዓ.ም ቦርዱ በማያዉቀዉና ቀርቦለት ዕዉቅና ባልተሰጠዉ መተዳደሪያ ደንብ አዲስ አመራሮች ተመርጠዋል፤ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስከ መስከረም ወር 2007ዓ.ም ድረስ እነዚህ አመራሮች በቦርዱ ዕዉቅና ባያገኙም የተጓደሉትን ጉዳዮች እናሟላለን በሚል ሲንቀሳቀሱ ቆይተዋል። የፓርቲዉን ዉስጠ ደንብና የምርጫ አዋጁን በጣሰ መልኩ ቀደም ሲል ከኃላፊነት ተነስተዋል የተባሉት ግለሰብ ቦርዱ በማያዉቀዉ ምክንያት ህጋዊ ያልሆነ ጠቅላላ ጉባኤ በመጥራት የፓርቲዉን እንቅስቃሴ በድጋሚ ተረክበናል ብለዉ ቀርበዋል። ይሄዉ ኃይል የጠቅላላ ጉባኤዉ ዉጤት ለቦርዱ እስከአሁን ባልቀረበበት ሁኔታ የፓርቲዉን አመራር /ፕሬዚደንት/ ነን በማለት እንቅስቃሴ ጀምሯል። ምርጫዉም የተካሄደዉ በደብዳቤ ለቦርዱ ከተገለጸለት ሰዓት ዉጭና ቦርዱ ተወካዮች ባልተገኙበት ነበር። ስለዚህ የመኢአድ ፕሬዝዴንት ማነዉ?/ አቶ አበባዉ መሐሪ ወይስ ኢ/ር ኃይሉ ሻወል ወይስ አቶ ማሙሸት አማረ? የሚለዉ እንቆቅልሽ ሆኖብናል። የትኛዉም ወገን ቢሆን የፓርቲዉን ዉስጠ ደንብና የምርጫ ህጉን በተከተለ መልኩ አመራር ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልቻለም። አንድነት ፓርቲን በተመለከተ ቦርዱ በማያዉቀዉና እዉቅና ባልሰጠዉ የመተዳደሪያ ደንብ፣ አሻሻልኩ የሚለዉን ደንብም ለሰባት ወራት ለቦርዱ ሪፖርት ሳያደርግ ሚስጥር አድርጎ አስቀምጠዋል። እንደገና ይሄንኑ ደንብ በመጠቀም ኢ/ር ግዛቸዉ ሽፈራዉን/የፓርቲዉን ፕሬዝደንት/ ከስልጣን አሰናብተዋል። በመቀጠልም ሌላ ፕሬዝደንት በምትካቸዉ በፓርቲዉ መተዳደሪያ ደንብም ሆነ በምርጫ አዋጁ በጠቅላላ ጉባኤ መመረጥ ያለበትን ወደ ጎን በመተዉ በብሔራዊ ምክር ቤት እንዲመረጥ አድርገዋል።

ጠቅላላ ጉባኤዉም የተካሄደዉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ በጣሰ መልኩ ምልዓተ ጉባኤ ባልተሟላበት፣ለጠቅላላ ጉባኤዉ በህጉ የተሰጡትን ስልጣኖች በብሔራዊ ምክር ቤቱ እንደወሰን በማድረግ ነበር። ይሄንን ተከትሎ የቀድሞዉ አመራር አላስፈላጊ ጫና ተፈጥሮባቸዉ ከስልጣን እንዲነሱ የተደረገዉ ከህግ ዉጭ በመሆኑ አሁን ተመረጥን ለሚሉት ቦርዱ ዕዉቅና እንዳይሰጥ የሚሉ በርካታ የፓርቲዉ አመራሮችና አባላት ቅሬታ አቅርበዋል። በሌላ በኩል የምርጫ ሂደቱ ያለብትን ግድፈት እናስተካክላለን በሚል አዲስ ተመርጠናል በሚሉት አካላት እንቅስቃሴ ቢደረግም ተስተካክሎ ለቦርዱ የቀረበ ነገር ባለመኖሩ ህጋዊ አመራሩን የመለየት ስራ ቦርዱ ማከናወን አልቻለም።

ማጠቃለያ

መኢአድ

1. በፓርቲዉ መተዳደሪያ ደንብ በስራ ላይ ያለዉ 2001 በቦርዱ ዕዉቅና የተሰጠዉ ሲሆን አንቀጽ 20/1/ መሰረት ፕሬዝደንትና ምክትል ፕሩዝደንት የሚመረጠዉ በጠቅላላ ጉባኤዉ ከማዕከላዊ ምክር ቤት አባላት መካከል ነዉ ይላል።አሁን የተመረጡት ግን ከአባልነት ተሰርዘዉ ከ4 ዓመታት በላይ የቆዩ ወደ ጉባዔዉም የገቡት በአባልነት እንዲሳተፉ እንጂ እንዲመረጡ ደንባቸዉ አይደግፍም።

2. መተዳደሪያ ደንቦችን ማሻሻል የፈለገ የፖለቲካ ፓርቲ አስቀድሞ ለቦርዱ ማሳወቅ እንዳለበት በፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ 573/2000 አንቀጽ 12/2/ ፓርቲዉ ይሄንን ሳይፈጽም ደንቦች ያሻሽላል በቦርዱ ባልጸደቀ ደንብም እርምጃዎችን ይወስዳል።ይህም ከአሰራር ዉጪ ነዉ።

3. በፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ አንቀጽ 19/1(ለ) መሰረት የቦርድ ተወካይ ባልተገኘበት የጠቅላላ ጉባኤ መካሄዱና የአመራሮች ምርጫ ተደርጓል። ይህ ህጋዊ አሰራርም አይደለም።

4. በፓርቲዉ መተደዳሪያ ደንብ አንቀጽ 10(2)(17) መሰረት በድጋሚ ካልተመረጠ በስተቀር የአመራር አባላትም ሆነ ሌሎች የማዕከላዊ ምክር ቤት አባላት የስራ ዘመን አምስት ዓመት እንደሆነ ይደነግጋል። ይሄንን በተጻረረ መልኩ በ2005 የተመረጠዉ አመራር አሉ የተባሉትን ጉድለቶች ለማስተካከል እንቅስቀሴ ላይ እያለ ሌላ አመራር በላዩ ላይ እንዲመረጥ ተደርጓል።

5. የፖለቲካ ፓርቲዎች በተሟላ ሰነድና ማህተም በተደገፈ ሪፖርት ለቦርዱ ማቅረብ እንደሚገባ በምዝገባ አዋጁ አንቀጽ 19 ስር የተደነገገ ቢሆንም ተካሄደ የተባለዉን ጠቅላላ ጉባኤ በተሟላ ሰነድ በማስደገፍ ማቅረብ አልቻለም።

አንድነት

በስራ ላይ ያለዉ የ2004ዓ.ም የመተዳደሪያ ደንብ

1.አንድነት ፓርቲ በተመለከተ ወቅታዊ የፓርቲዉ ጠቅላላ ሪፖርት በወቀቱ ያለማቅረብ ሰባት ወራት በማዘግየት አቅርቧል፤ ይሄ ደግሞ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁ.573/2000 አንቀጽ 19 እስከ 27 እንደዚሁም አንቀጽ 39 ን የጣሰ ከመሆኑም በላይ የፓርቲዉን የዉስጠ ደንብ ጥሰዋል።

2. የፓርቲዉ አመራሮች ፕሬዝደንቱን ጨምሮ በጠቅላላ ጉባዔ እንደሚመረጥ በፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁ.573/2000 አንቀጽ 8/2(ረ)/ስር ተመልክቷል። የፓርቲዉ ዉስጠ ድንብ አንቀጽ 13/1/ ስር «በጠቅላላ ጉባኤዉ ይመረጣል» የሚለዉን የጣሰና ፕሬዝደንቱ በጠቅላላ ጉባኤ መምረጥ ሲገባቸዉ በብሔራዊ ምክር ቤት ተመርጠዋል።

3.የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ብዛት በተመለከተ በምዝገባ አዋጁ አንቀጽ 15 ንኡስ አንቀጽ 1/ሠ/ የፓርቲዉን ስብሰባ እና ዉሳኔ አሰጣጥ ስነ ስርዓት ሊኖረዉ እንደሚገባ ይደነግጋል። የፓርቲዉ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 10/2/ (ቀ) የጠቅላላ ጉባኤ የድምጽና ዉሳኔ አሰጣጥ በአብላጫ ድምጸ/50 +1/ ይሆናል እያለ ይሄንን ባላከበረ መልኩ ፓርቲዉ ጠቅላላ ጉባዔዉን አካሂዷል።

4. ፓርቲዉ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 11/1(ሠ)/ መሰረት የፓርቲዉ መሪ እንዲሁም ስራ አስፈጻሚ ከህግ ወይም ከፓርቲዉ ፕሮግራም ዉጭ እየተንቀሳቀሰ ነዉ ብሎ ሲያምን በ2/3ኛ ድምጽ መሪዉን ጨምሮ ስራ አስፈጻሚዉን በማገድ የጠቅላላ ጉባኤ እንዲጠራና በ6 ወራት ጊዜ ዉስጥ አዲስ ምርጫ እንዲደረግ ብሔራዊ ምክር ቤቱ ስልጣን የተሰጠዉ እንጂ ፕሬዝደንት እንዲመርጥ ስልጣን ሳይኖረዉ ፈጽሟል።

በመሆኑም እነዚህ ሁለት ፓርቲዎች ስለመረጡት ምልክት ቦርዱ የመጨረሻ ዉሳኔ ለመስጠት በመቸገሩ ጉዳያቸዉን አስተካክለዉ እንዲያቀርቡ ቦርዱ ታህሳስ 4 ቀን 2007 ባካሄደው መደበኛ ስብሰባዉ የአንድ ሳምንት ጊዜ ሰጥቷቸዋል። ይህም የተደረገዉ ቦርዱ ከዚህ በፊትም በሆደ ሰፊነት ያለባቸዉን ችግሮቻቸዉን እንዲፈቱ ዕድል ሲሰጣቸዉ እንደነበር ሁሉ አሁንም በተሰጣቸዉ ጊዜ ዉስጥ የዉስጥ ጉዳያቸዉን በህጉ መሰረት በመፍታት እንዲያቀርቡ ለማስቻል ነዉ። ይሄ ካልተፈጸመ ቦርዱ ለሁለቱም ፓርቲዎቹ የሰጡትን ምልክት እዉቅና ለመስጠትና ተግባራዊ ለማድረግ እንደሚቸገር አጥብቆ ያሳስባል።

ታህሳስ 10/2007 ዓ.ም■

# በምርጫ ቦርድ ደባ አንድነት አይደናገጥም!

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) የተሰጠ መግለጫ

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) የ2007 ዓ.ም አገራዊ ምርጫ እንደሚሳተፍና ለዚህም መተማመኛው ሕዝቡ መሆኑን ገልፀ "ተደራጅ 2007 ለለውጥ" በሚል መፈክር አንግቦ አገራዊና ሕዝባዊ ኃላፊነቱን ለመወጣትና ኢህአዴግን በቃህ ለማለት ሌት፣ ከቀን በንቃትና በትጋት እየሠራ ይገኛል።

በአሁኑ ወቅት ነፃ ሚዲያ በታፈነበትና በተዘጋበት አንድነት የራሱን የማተሚያ ማሽን ገዝቶ በየጊዜው ሆን ተብሎ በሚመስል መልኩ በሚጠፋው የኤሌክትሪክ ችግርን ለማሸነፍ የራሱን ከፍተኛ ኃይል ያለው ጀነሬተር በመግዛት በሣምንት የራሱን ጋዜጦችን እያተመ እያንዲያሰራጭ ተገዷል። ምሁራን፣ ወጣቶች፣ ጋዜጠኞችና ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ለወሳኑ የ2007 ምርጫ ትግል እየተቀላቀሉት ይገኛሉ። አንድነት በአሁኑ ሰዓት ከመቼውም ጊዜ በላይ ትግሉን በአግባቡ ለመምራትና ለውጥ ለማምጣት በተሻለ ቆመና ላይ ነው ያለው።

በምርጫ ቦርድ በአንድት ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ ሆነ በገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የሌለውን የጠቅላላ ጉባኤ አባላትና የምላተ-ጉባኤ ቁጥር በተሻሻለው ደንባችን ውስጥ እንድናካትት የተወሰነብንን ፈርድ ገምድል ድርጊት ሕገ-ወጥ መሆኑን ብናውቀውም ጠቅላላ ጉባኤ መጠራትን እንደ ጉዳት ሳይሆን እንደ ልዩ እድል በመቁጠር፣ 320 የጠቅላላ ጉባኤ አባላት በመጥራት የምርጫ ቦርድ ተወካይ በተገኘበት የተሳካና አንፀባራቂ ጠቅላላ ጉባኤ አካሄደናል። የጠቅላላ ጉባኤውንም ሰነድ ታህሣሥ 10 ቀን 2007 ዓ.ም ለምርጫ ቦርድ ገቢ ተደርጓል።

ሁ ሉ እንደሚገነዘበው በአሁኑ ሰዓት ሕዝቡ በኑሮ ውድነትና በሥራ እጦት ከመሰቃየቱም በላይ ሙስና ሰፍኗል፤ መልካም አስተዳደር የሕግ የበላይነት ከቶውንም ጠፍቷል። የሕዝብ የነፃነትና የዴሞክራሲ ጥያቄ ገዝፎና አፍጥጦ እየመጣ ነው። በመሆኑም ኢህአዴግ በፍርሃትና በጭንቀት እየራደ ነው። ምረጡኝ ብሎ ሕዝብ ፊት ለመቅረብ የሚያስችለው የፖለቲካና የሞራል ኃይል ስለሌለው ውሸት፣ ማስፈራራት ማሰር መግደል ማሸነፊያ መሣሪያዎች እንዳልሆኑትም በግልጽና በትክክል ተደራጅቷል። አሁን የቀረው ማሸነፊያው መንገድ አንድነት ፓርቲን በመዝጋት ነው የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረሱ ጥንቱንም የአንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታዎች የሆነውን ወኪሉን በመጠቀም በአንድነት ላይ ዘመቻ ከፍቷል።

**በተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ አካቶ ያላቀረበ በመሆኑ ይህንኑ አሟልታችሁ እንድታቀርቡ በአክብሮት እናሳውቃለን" የሚል ነው። እኛም ጠቅላላ ጉባኤ ጠርተን ይህንኑ ጥያቄ እንዲሟላ ከማድረጋችንም ባሻገር በሕገ-ደንባችን መሠረት በብሔራዊ ም/ቤት ተመርጠው የነበሩት የፓርቲውን ፕሬዚደንት ሹመት በጠቅላላው ጉባኤ አፀድቀናል**

ታህሣሥ 10 ቀን 2007 ዓ.ም በምርጫ ቦርድ ከፍተኛ አመራር የተሰጠው በቅጥፈትና በውሸት የተሞላው መግለጫም የሚያሳየውና የሚመሰክረው ይህንኑ ነው። ነገር ግን እውነቱን በአጭሩ እንደሚከተለው እናስቀምጣለን። አንድነት ፓርቲ ታህሣሥ 19 እና 20 ቀን 2006 ዓ.ም ያካሄደውን የጠቅላላ ጉባኤ ሰነድ ለምርጫ ቦርድ ካስገባ በኋላ ምርጫ ቦርድ ሐምሌ 20 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በዘጠኝ ነጥቦች ላይ ማብራሪያ እንድንሰጥ ጠይቄን መልስ ሰጠን፤ በመቀጠልም ጥቅምት 20 ቀን 2007 ዓም በተፃፈ ደብዳቤ ጥያቄ ከዘጠኝ ወደ ሦስት አውርዶ ላከልን ለዚህም አንድነት መልስ ሰጠ። ቀጥሎም ቦርዱ ህዳር 10 ቀን 2007 በተፃፈ ደብዳቤ ጥያቄውን ወደ አንድ አወረደው እንዲያውም በመጨረሻ ህዳር 19 ቀን 2007 ዓም በተፃፈ ደብዳቤ። "ፓርቲው በሰጠው ምላሽ የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ብዛት 320 እንደሆነ አሳውቋል። ይሁን እንጂ በተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ አካቶ ያላቀረበ በመሆኑ ይህንኑ አሟልታችሁ እንድታቀርቡ በአክብሮት እናሳውቃለን" የሚል ነው። እኛም ጠቅላላ ጉባኤ ጠርተን ይህንኑ ጥያቄ እንዲሟላ ከማድረጋችንም ባሻገር በሕገ-ደንባችን መሠረት በብሔራዊ ም/ቤት ተመርጠው የነበሩት የፓርቲውን ፕሬዚደንት ሹመት በጠቅላላው ጉባኤ አፀድቀናል። እንጂ አይነቱን በሕገ-ደንቡና በሥነ-ሥርዓት ለተከናወኑ ጉዳዮች ያልተገባና የተሳሳተ መግለጫ መስጠት በጣም አሳኝ ነው። በተለይም የሕዝብ ታዛቢዎች ታህሣሥ 12 ቀን 2007 ዓ.ም እንደሚመረጡ እየታወቀ ይህን ዓይነት መግለጫ መስጠት ሕዝቡ በጥንቃቄና በተደራጀ ምልኩ ትክክለኛነትና ሀቀኞች የሆኑ ታዛቢዎችን እንዳይመርጥ ለማሰናከል የታቀደ ይመስላል። በመሆኑም ዛሬም ሆነ ነገ አንድነት ፓርቲ ከሕዝብ ጋር ሆኖ ትግሉን አጠንክሮ ይቀጥላል አባላትም ሆነ ሕዝቡ ከፓርቲያችን ጎን ተሰልፎ ትግሉን እንዲያጧጡፈው ከአክብሮት ጋር እንጠይቃለን።

ድል የህዝብ ነው!

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)

ታህሣሥ 11 ቀን 2007 ዓም

በዚህ ዓምድ ስር የሚወጡ ጽሁፎች የፀሐፊውን እንጂ የኤዲቶሪያሉን አቋም አያንፀባርቁም

# ባለፉት ምርጫዎች የታዩ ድክመቶች በምርጫ 2007 ሊደገሙ አይገባም

## (ኢህአዴግን ለተደጋጋሚ ትዝብት ያጋለጠው የታዛቢዎች ምርጫ)

ጥላሁን እንደሻው
የመድረክ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ

ኢህአዴግ በሀገራችን የፖለቲካ ሥልጣን ከተቆጣጠረበት 1983 ጀምሮ በርካታ ምርጫዎች በየደረጃው የተካሄዱ ሲሆን በሀገር አቀፍ ደረጃ እንኳን አራት ዙር ምርጫዎች ተካሂደው አምስተኛውም ከፊታችን ቀርቦ ይገኛል። ያለፉት የምርጫ ሂደቶች በርካታ ድክመቶች ስለነበሩባቸው በአሁኑ ወቅት ከነዚያ ድክመቶች ብዙ ተምረንባቸው ትክክለኛውን ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ለማካሄድ የነበሩብንን ጉድለቶች ለይተን በማወቅ የእርምት እርምጃ መውሰድ ነበረብን። የጉዳዩ ባለቤቶች የሆንን በተለይም የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ መሠረታዊ ችግሮቻችንን በሰላማዊ ውይይትና ድርድር በጋር ገምግመን ተጨባጭ የማስተካከያ እርምጃዎችን ከወሰድን በኃላ ወደ ቀጣዩ ምርጫ መግባት ቀናነት፣ አርቆ አስተዋይነትና በሳልነት የተሞላበት ሰላማዊ የችግሮች መፍቻ መንገድ ስለሆነ ይህንኑ የመፍትሄ አቅጣጫ እንድንከተል የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ በጽናት ጥረት እያደረገ ይገኛል።

ይህ ቀናና ሰላማዊ የሆነው ወሳኝ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የትግል አቅጣጫ በ1997 ዓ.ም ሀገር አቀፍ ምርጫ ወቅትም በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት አባል ድርጅቶች አማካይነት ከገዥው ፓርቲ ጋር በተደረገው እልህ አስጨራሽ ድርድር በሰላማዊ መንገድ ጠንካራ ትግል የተካሄደበትና በመጠኑም ቢሆን በዚያ ዓመት ለተካሄደው ምርጫ አንጻራዊ መሻሻል አስተዋፆ ያደረገ መሆኑ ሊካድ የማይቻል ሐቅ ነው። በ1997 ምርጫ ወቅት መስተካከል ይገባቸው ከነበሩት መሠረትዊ ችግሮች ውስጥ የምርጫ ክርክር ቀጥታ ስርጭት በድርድሩ ወቅት ከስምምነት በመደረሱ እልባት ያገኘና ጥሩ ውጤትም ያስገኘ ቢሆንም ሌሎች እልባት ሳያገኙ ወደ ምርጫው የተገባባቸው ጉዳዮች ወደ ኃላ ምርጫው ለሀገራችን የዴሞክራሲ ግንባታ ችግሮች ማስገኘት ይችል የነበረውን ውጤት ሳያስገኝ እንዲቀር አድርገውታል። ከነዚህም በወቅቱ እልባት ሳያገኙ ከቀሩት መሠረታዊ ችግሮች ዋነኞዎቹ የገለልተኛ የምርጫ አስተዳደርና ገለልተኛ የምርጫ ታዛቢ ጉዳዮች ነበሩ።

የኢትየጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት ለነዚህ መሠረታዊ ችግሮች መፍትሔ ሳይገኝ የሚገባበት ምርጫ ሊያስከትል የሚችለውን ችግር በመገንዘብ ጠንካራ ድርድር በማድረግ በገዥው ፓርቲ ላይ ሐቀኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በመተባበርና ሕዝቡንም ሆነ ዓለም አቀፍ ማሕበረሰቡን በማስተባባር ለዴሞክራሲ ግንባታችን የሚያግዝ አዎንታዊ ተጽዕኖ ለማሳደር እንዲቻል የበኩሉን ከፍተኛ ጥረት ቢያደርግም ከሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች በተለይም በወቅቱ ጥሩ አቋም ላይ ከነበረው (ድርጅታዊ አቅም ከነበረው) (ቅንጅት) የአሁኑ አንድነት ለፍትሕና ለዴሞክራሲ ተገቢውን ድጋፍ ሊያገኝ አልቻለም። ይልቁንም ሕብረት እልህ አስጨራሽ ድርድር ሲያደርግ በነበረበት ወቅት ቅንጅት ካለምንም ቅድመ ሁኔታና ድርድር ነበር ወደ ምርጫው ለመግባት ወስኖ የተንቀሳቀሰው። ይህ የችግሮችን የመፍትሄ አቅጣጫ በአግባቡ ባለማጤን የተደረገው የቅንጅት እንቅስቃሴ በወቅቱ ለኢህአዴግ ትልቅ ድጋፍና እፎይታ ነበር ያስገኘለት። በዚህም ምክንያት ኢህአዴግ ከህብረት ጋር ጀምሮት የነበረውን ድርድር አቋርጦ ከቅንጅት ጋር የምርጫ ውድድሩን ለመቀጠል በመንቀሳቀሱ ሕብረትም ጉዳዮቹ እልባት ሳያገኙ ወደ ምርጫው ውድድር ለመግባት ተገደደ። በዚህም ምክንያት ኢህአዴግ ለምርጫው ዴሞክራሲያዊነት ወሳኝ የነበሩ ጉዳዮች በወቅቱ እልባት ሳያገኙ በእንጥልጥል እንዲቀሩና እስከ አሁንም እነዚሁ ችግሮች ቀጣይ የሀገራችን መሠረታዊ የምርጫ ችግሮች ሆነው እንዲቆዩ አድርጎ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክም በይፋ ከተመሠረተበት መስከረም 2002 ጀምሮ ኢዴኃሕ አንስቶአቸው የነበሩትንና እልባት ሳያገኙ የቀሩትን መሠረታዊ

**ሰሞኑን ታህሳስ 5 ቀን 2007 ዓ ም በአዲስ አበባ ከተማ የጠራውና በ10 ሺዎች የሚቆጠር የአዲስ አበባ ሕዝብ በጠንካራ ድጋፍና የትግል ወኔ የተሳተፈበት ሰላማዊ ሰልፍም የዚሁ መድረክ ለሀገራችን መሠረታዊ ችግሮች ሰላማዊ መፍትሔ ለማስገኘት እያካሄደ ያለው ትግል አካል ነው።**

የሀገራችን የምርጫ ችግሮች ጥያቄዎች በማንሳት በሰላማዊ ውይይትና ድርድር እልባት ለማስገኘት ጥረት ማድረጉን እስከ አሁንም ቀጥሎበታል። ሰሞኑን ታህሳስ 5 ቀን 2007 ዓ ም በአዲስ አበባ ከተማ የጠራውና በ10 ሺዎች የሚቆጠር የአዲስ አበባ ሕዝብ በጠንካራ ድጋፍና የትግል ወኔ የተሳተፈበት ሰላማዊ ሰልፍም የዚሁ መድረክ ለሀገራችን መሠረታዊ ችግሮች ሰላማዊ መፍትሔ ለማስገኘት እያካሄደ ያለው ትግል አካል ነው።

መድረክ በ1997 ዓ ም በሀገራችን የምርጫ ሂደት የነበሩ ጉድለቶችንና በተለይም በ2002 የሀገራችን የምርጫ ሂደት የወረደበትን አዘቅት በሚገባ በጥልቀት ገምግሞ እነዚህን ቀደም ባሉት ምርጫዎች የነበሩ ጉድለቶችን በማረምና በማስተካከል ለ2007 ምርጫ ነፃ፣ ፍትሓዊና ዴሞክራሲያዊ መሆን የሚኖረውን ወሳኝ ሚና በግልጽ አስቀምጧል። ይህንን እውነታ በአግባቡ መገንዘብ ያልቻሉና ከ1997 እና ከ2002 ምርጫዎች ደካማ ጎኖች ተገቢውን ትምህርት ለመቅሰም ያልቻሉ አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በመሠረታዊ የምርጫ ችግሮች ላይ የመደራደሩን ጉዳይ ወደጎን ትተው በምርጫው ለመሳተፍ ወስነናል የሚለውን መግለጫ አስቀድመው በመስጠት ልክ ቅንጅት በ1997 ተቻኩሎ ለኢህአዴግ የለገሰውን አይነት ድጋፍና እፎይታ እየቸሩለት ይገኛሉ። ይህንኑ የአንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ልብ ያገኘው ኢህአዴግም መድረክ ያቀረበውን የድርድር ጥያቄ ወደ ጎን ትቶ በ1997 ሳይፈቱ የቀሩ ችግሮችን ብቻ ሳይሆን በ2002 የጨመራቸውን እንደ 1ለ5 የጠርናፊና ተጠርናፊ፣ የምርጫ ሠራዊት መዋቅሩን አጠናክሮና የሕዝብ የምርጫ ታዛቢ ጉዳይንም በአስቂኝ ድራማው እያጠናቀቀ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ ታህሳስ 12 ቀን 2007 ዓ.ም በመላ በሀገራችን ተካሄደ ስለተባለው የሕዝብ ታዛቢዎች ምርጫ ሂደትና ውጤት ዝርዝር መረጃዎችን አጠናቅሮ ይፋዊ መግለጫ ወደፊት ያወጣል። እስከ አሁን ከተለያዩ ክልሎችና ከተማዎች እየደረሰን ባለው መረጃ ለማወቅ የተቻለው ግን ኢህአዴግ አሁንም የከርሞ ጥጃ ሥራውን እንደቀጠለበት መሆኑን ነው። በዚሁም መሠረት ለሕዝቡ ገለልተኛ የምርጫ ታዛቢዎች የሚመርጡበትን ቦታና ሰዓት ገልጾ በየቀበሌዎቹ ጥሪ ሳያስተላልፍ በድርጅታዊ መዋቅሩ አማካይነት በስውር በጠራቸው ጥቅት አባሎቹ አማካይነት ቀደም ብሎ የተዘጋጁ ምልምሎቹን (በብዙ ቦታዎችም የታወቁ አባሎቹን) እያጸደቀ የሕዝብ ታዛቢዎችን አሰመረጥኩ እያለ ለትዝብት ያጋለጠውን ሥራ በማከናወን ላይ መሆኑን ለመረዳት ችለናል።

ስለዚህም መድረክ ኢህአዴግ በሕዝብ መብት ላይ መቀለዱን ትቶ ሕገ መንግሥቱንና ሕግን አክብሮ ምርጫን ማካሄድ ስለሚቻልበት ሁኔታ ጊዜ ሳያባክንና ሳይረፍድ ከመድረክና ሌሎችም ለዚህ ዓላማ ዝግጁ ከሆኑ ፓርቲዎች ጋር በመወያየትና በመደራደር የሀገራችን የምርጫ መሠረታዊ ችግሮች የሚፈቱበትን ሁኔታ እንዲያመቻች ይጠይቃል።

# የሚያረካ ምላሽ ያላገኘው "አብዮታዊ ዴሞክራሲ"

በጌታቸው በቀለ
ጦር ኃይሎች አካባቢ

ከፖለቲካ፣ ከሃይማኖት፣ ከሳይንስ፣ ከፍልስፍናና ከሌሎችም ዘርፎች የሚያረካ ምላሽ ያላገኙ ጥያቄዎች ይነሳሉ። የሚያረካ ምላሽ እስከሚያገኙ ድረስ እየተደጋገሙ ይጠየቃሉ። ለዚህ ነው ታዋቂው ገጣሚ ሰለሞን ዴሬሳ "አንዳንድ ጥያቄ አለ፤ አስሬ ተጠይቆ፤ አስሬ መልስ አግኝቶ ዳግመኛ አስሬ የሚጠየቅ" ያለው።

ከላይ እንደገለጽኩት የሚያረካ ምላሽ ያላገኙ ጥያቄዎች ከተለያዩ ዘርፎች ይነሳሉ። እኔ ግን ከፖለቲካ፣ የሚያረካ ምላሽ ያላገኘውን ጥያቄ አነሳለሁ። እሱም፤ "አብዮታዊ ዴሞክራሲ ምንድነው?" የሚል ነው። "አብዮታዊ ዴሞክራሲ ምንድን ነው?" የሚለው ጥያቄ ለእኔ የሚያረካ ምላሽ ያላገኘ ነው። እንኳን እኔ በኢህአዴግ "ውስጥ" የነበሩ ሰዎችም በቅጡ አልተረዱትም። የሚያውቁት መለስ ዜናዊና የእሱ "የልብ" ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

ከወያኔ ድብቅነት የተነሳ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ምንነት በቅጡ አልተብራራም። የአብዮታዊ ዴሞክራሲን ምንነት ለማወቅ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በዳንኤል ተፈራ አማካኝነት "ዳንዲ፡- የነጋሶ መንገድ" በሚል ርዕስ የፃፉትን መጽሐፍ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ አነበብኩት። ስለ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ምንነት የሚያረካ ምላሽ ባላገኝበትም፤ እግረ መንገዴን ግን ዶ/ር ነጋሶ ከወያኔ ጋር ስለነበራቸው የሎሌና ጌታ ግንኙነት ለማወቅ ችያለሁ። ከርዕሴ ጋር ስለማይሄድ ግን አልፌዋለሁ።

ዶ/ር ነጋሶ በመጽሐፋቸው እንደተናገሩት የአብዮታዊ ዴሞክራሲን ምንነት እንዲያስረዳቸው መለስ ዜናዊን ጠይቀው የሚያረካ ምላሽ አልሰጣቸውም። እንዲህ የሚል ምላሽ እንደሰጣቸው ዶ/ር ነጋሶ ይናገራሉ። "አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚባለው በ1904 እ.ኤ.አ የከሸፈው የራሺያ ሪቮሉሽን ነው፤ ሌኒን ያዳበረው ሃሳብ ነው። ከፊውዳሊዝም ወደ ሶሻሊዝም ከመሄዱ በፊት አጠር ላለ ጊዜ የካፒታሊስት ሥርዓት ሊኖር እንደሚችል፤ በዚህ ጊዜ ሠርቶ አደሩና ላብአደሩ የመንግሥት ሥልጣን ይዘው፣ ከአብዮታዊ ምሁራን ጋር ለተወሰነ ጊዜ (ካፒታሊስቶች የመንግሥት ሥልጣን ሳይዙ)፣ የተለያዩ ርዕዮተ ዓለም የያዙ ሰዎች እንዲደራጁ የሚፈቀድበትን ወቅት ካካሄድን በኋላ ወደ ሶሻሊዝም እንሄዳለን።" (ዳንዲ፡- የነጋሶ መንገድ ከገጽ ፪፻፷፩ - ፪፻፷፪)

ዶ/ር ነጋሶ በመለስ ዜናዊ መልስ አለመርካታቸውን ካነጋገራቸው ማወቅ ይቻላል። እንዲህ ነበር ያሉት፡- "ለበለጠ ማብራሪያ የሚጠቅሙ መፃሕፍትን ግን አልጠቆመኝም።.... ሆኖም መለስ የጠለቀ ዕውቀት እንዳለው ተገንዝቤያለሁ" (ዝኒ ከማሁ)

እኔም እንደ ዶ/ር ነጋሶ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ምንነት አልገባኝም። ያሬድ ጥበቡ የተባለ ሰው ግን መለስ ዜናዊ የጠቆማቸውን መጽሐፍ እንዲህ ሲሉ ይናገራሉ "መለስ የስታሊንን 'ፋውንዴሽን ኮፍሌኒኒዝም' እና 'ኢንዘ ኦፖዚሽን'ን በደንብ ማጥናት አስፈላጊ እንደሆነ የነገረኝ ትዝ ይለኛል" (ዕንቁ መጽሔት ቁጥር ፸፬ ገጽ ፴፪)

**ወያኔ እንደ መንግሥት ሥልጣን ላይ ሆኖ እነዚህን መፃሕፍት አስተርጉሞ ለንባብ አላቀረባቸውም። ምናልባት መፃሕፍቱ በውስጣቸው ሤራ ሊኖርባቸው ይችላል**

ያሬድ ጥበቡ "Foundation of Leninism, "On the opposition" የተባሉ መፃሕፍትን መለስ ዜናዊ ያነብ እንደነበር ጥቆማ ሰጥተዋል። ዶ/ር ነጋሶ እነዚህን መፃሕፍት አንብበዋቸው ይሁኑ አይሁኑ አላውቅም። ያሬድ ጥበቡ ግን እነዚህን መፃሕፍት ማንበብ መለስ ዜናዊንና አስተሳሰቡን ማወቅ እንደሆነ እንዲህ ሲሉ ይናገራሉ፡- "በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ወዲ ዜናዊ ያደርግ የነበረው ማተራመስ ሰዎች ግራ ሲያጋባቸውና ሲጠይቁኝ 'መለስን መረዳት ከፈለጋችሁ እነዚህን ሁለት መፃሕፍት በቅጡ አንብቡ' እላቸው ነበር። ጊዜውን ወስዶ ያነበበ ግን ያለ አይመስለኝም" (ዝኒ ከማሁ፣ ሠረዝ የኔ ነው)

እንግሊዝኛ አንብቦ የመረዳት ችግር ሳይኖርብኝ፣ ያሬድ ጥበቡ የጠቀሷቸውን መፃሕፍት ማግኘት ባለመቻሌ አዝናለሁ። ወያኔ እንደ መንግሥት ሥልጣን ላይ ሆኖ እነዚህን መፃሕፍት አስተርጉሞ ለንባብ አላቀረባቸውም። ምናልባት መፃሕፍቱ በውስጣቸው ሤራ ሊኖርባቸው ይችላል። የወያኔ ድብቅነትም የሚመነጨው ውስጡ ካለው ሤራ ነው የሚል እምነት አለኝ። ፈረንጆች "The devil is in detail" የሚሉት ለዚህ ሳይሆን አይቀርም።

ያም ሆነ ይህ፣ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚያረካ ምላሽ ያላገኘ "የዴሞክራሲ" ዓይነት ነው። ■

# “የክፉ ቀን ደራሿ . . .

ማስታወቂያ ተወደዋል። እስቲ እሱ ማስታወቂያ እንዴት እንደተሰራ ንገሪኝ እንቺስ እንዴት ተሳተፍሽ?

ፍሬህይወት፡- የሚገርም ነገር ነው፤ እኔ ከማርቆስ ኤሊያስ ጋር “ቆራሌው” የሚለውን ዘፈኑን ክሊፕ ለመስራት ነበር የሄድኩት። ያንን ስሰራ “ካሜራማኑ” ያን ዕለት አየኝና “አንድ የምንሠራው ስራ አለ ትረጂኛለሽ” አለኝ። እሺ ብዬ በተዘጋጀ ስራ መሀል ልክክ አልኩልህ እልሃለሁ። አሁን ካሉ ማስታወቂያዎች እንግዲህ በትንሹ በትልቁ ሰው ሁሉ ተወዳጅ ስራ ይመስለኛል። ባይገርም እኛም ደስ ብሎን የሰራነው ማስታወቂያ ነው። በተለይ እኔ መጨረሻ ላይ በስሜት ሆኜ “8100” እልኩ ብቻዬን የደነስኩበትን ጊዜ አስታውሰዋለሁ (ሳቅ) የተሳካ ማስታወቂያ በመሆኑ አንድነት ለአሪፍ ስራ ወሳኝ መሆኑን አሳይቶኛል።

ሰንደቅ፡- እስካሁን በስራሽ የፈተነሽ ገፀ-ባህሪይ አጋጥሞሽ ያውቃል?

ፍሬህይወት፡- እስካሁን ምንም አልገጠመንም። እኔ ፊልምም ድራማም ሆነ ቴአትር ሲሰጠኝ እምሽክ አድርጌ ነው የማጠናው። አሁን ለምሳሌ ፊልም ስንሰራ ዛሬ አንዱን ትዕይንት ነገ ደግሞ ሌላውን እየተባለ ነው የሚጠናው፤ እኔ ግን ሁሉንም አንዴ ነው አጠናቅቄ የምመጣው። ከዚያ በኋላ ፅሁፉ ከኔ ጋር አይገናኝም። ባይገርም 100 ምናምን ገፅ በ15 ቀን ውስጥ በቃሌ እይዛለሁ።

ሰንደቅ፡- ሰዎችን በስራዎችሽ እንደምታዝናኚ ሁሉ አንቺንስ ምን ያዝናናሻል?

ፍሬህይወት፡- ሰው ሲደሰት በጣም ያዝናናኛል። ለሰዎች በማድረግና ባደረኩላቸውም ነገር ሲደሰቱ ማየት በጣም ነው የሚያዝናናኝ። አሁን ለምሳሌ አዳማ ላይ ወጣት የፊልም ሰሪዎች አግኝተውኝ እንደሚያደንቁኝ ነግረውኝ፤ ፊልም ለመስራት እንደሚፈልጉ ሲያማክሩኝ እኔ በሂሳብ አልተደራደርኩም አብሬያቸው በመስራት እንደማግዛቸው ስነግራቸው በጣም ነበር የተደሰቱት ያ ነገር እኔንም ያስደስተኛል።

ሰንደቅ፡- ብዙ ሰዎች ለገንዘብ ድርድር ትኩረት እንደማትሰጪ ይናገራሉ። ታሪክ መረጣ ላይስ እንዴት ነሽ?

ፍሬህይወት፡- ከታሪክ ይልቅ ለኔ የሚመቸኝን “ካራክተር” (ገፀ-ባህሪይ) ነው የምምርጠው። አሁን ለምሳሌ ረጋ ብላ፣ ድክም ብላ የምትሳል ገፀባህሪይ አትሆነኝም። ነገር ግን ግዴታዬ ከሆነ እየታሸውም ቢሆን እሰራለሁ። ምረጪ ከተባልኩ ግን ቀልቃላና ፈጣን ሴት ባገኝ ደስ ይለኛል። (ሳቅ)

ሰንደቅ፡- እስቲ ስለቤተሰብ ሁኔታ አጫወቺኝ?

ፍሬህይወት፡- ሁለት ልጆች አሉኝ። ባለቤቴ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ ሰባት ዓመት ሆኖታል። ነፍሱን ይማረውና ሀገር ፍቅር እኩል ነበር የተቀጠርነው። በአሁኑ ወቅት የልጅ- ልጅ አይቼ አያት ሆኛለሁ። እህቶቼን ወንድሞቼን ሰብስቤ አንድ ግቢ ውስጥ በሰላምና በፍቅር ነው የምንኖረው።

ሰንደቅ፡- ይሄ የማሰባሰብ ነገር በሀገር ፍቅር ቴአትር ጊቢ ውስጥም እንዳለ ሰምቻለሁ፤ ማህበር መስርተሽ አንጋፎችን እያሰባሰብሽ ነው የሚባለው ነገር እውነት ነው?

ፍሬህይወት፡- እውነት ነው። ብዙዎቻችን በሀገር ፍቅር ያለነው አንጋፋ ሰራተኞች ጡረታ የመውጫችን ጊዜ እየተቃረበ ነው። ይሄ ነገር ከሆነ እስከመጨረሻው ተለያይተን ልንቀር ነው የሚል ስጋት ነበረብኝ። ይሄን ያህል ዓመት አብረን ሰርተን ከመበታተናችን በፊት ምንድነው ማድረግ ያለብን? ተባባልንና አሁን በቅርቡ የአንጋፎቹን ስም መዝግበን ማህበር መስርተናል። እና ለኔ ሰዎች ሲከፉም ሆነ ሲበታተኑ አልወድም። እኔ ያለሁበት ቦታ ላይ ማላዘን እንዲኖር አልፈልግም፤ መሳቅ መጫወት ደስ ይለኛል።

ሰንደቅ፡- አሁን የተንዠሸበትን መንገድ ዞር ብለሽ ስታስቢው ባደርገው ኖሮ ብለሽ የሚቆጭሽ ነገር አለ?



እኔ ሁልጊዜ ቢያዘጋጀኝ ብዬ የምመርጠው ተሻለ ወርቁ ነው። በርግጥ እኔ የተቃኘሁት በእነመላኩ አሻግሬና በእነሰሃሉ ነው። በዚህ ዘመን ግን ተሻለ ቢያዘጋጀኝ እመርጣለሁ

ፍሬህይወት፡- ብዙም አይደለም። ግን ይህን ያህል ዓመት ሰርቼ ቤተሰቦቼን የምሰበስብበት ቤት አለመስራቴ ይቆጨኛል። ነገ ለልጆቼ ምንድነው የምተውላቸው የሚለውን ነገር ሳስብ እቆጫለሁ። ያም ሆኖ ግን ይመስገነው በጣም ደስተኛ ነኝ።

ሰንደቅ፡- ሲያዩሽ በጣም ጠንካራ ሴት ነሽ፤ ስፖርት ትሰሪያለሽ እንዴ?

ፍሬህይወት፡- አዎ! ከልጅነቴ ጀምሮ ስፖርተኛ ነኝ፤ አክሮባት እሰራ ነበር። አሁንም ቢሆን ፈጣን እንቅስቃሴ እወዳለሁ። (ሳቅ)

ለዛም እኮ ነው ቀልቃላ ገፀ-ባህሪይ ባገኝ እወዳለሁ ያልኩህ።

ሰንደቅ፡- ሳንቺ የሚመችሽ አዘጋጅ ማነው?

ፍሬህይወት፡- እኔ ሁልጊዜ ቢያዘጋጀኝ ብዬ የምመርጠው ተሻለ ወርቁ ነው። በርግጥ እኔ የተቃኘሁት በእነመላኩ አሻግሬና በእነሰሃሉ ነው። በዚህ ዘመን ግን ተሻለ ቢያዘጋጀኝ እመርጣለሁ። ምክንያቱም እኔን ያቀኛል። ድርሰት ሲሰራ እንኳን ለኔ ቀዶ ነው የሚፋልኝ፤ እርሱ ያዘጋጀው ስራ አይሰፋኝም፣ አይጠበኝም።

ሰንደቅ፡- በቅርቡ በምን እንጠብቅሽ?

ፍሬህይወት፡- በቅርቡ እንግዲህ ያልወጡ ወደአራት ፊልሞች አሉ። ከእነሱ በተጨማሪ የሚመጣ ቴአትር አለ በመድረክም እንገናኛለን ማለት ነው።

ሰንደቅ፡- ስነበረን ቆይታ አመሰግናለሁ።

ፍሬህይወት፡- እኔም እናንተን በጣም አመሰግናለሁ።

# የ3ትውልድ...

አረጋውያንን መርዳት ማለት ከመመገብ እና ከማልበስም ያለፈ ከእድሜ መግፋት ጋር ተያይዘው የሚመጡ በርካታ ተግዳሮቶችን ማለፍ እንደሚያስፈልግ የገለፁት አቶ ሣህለማርያም፤ በማዕከሉ እየተከናወኑ ያሉት አረጋውያንን የመንከባከብ ተግባራትም እነዚህን ተግዳሮቶች በፅናት በማለፉ ሊደነቅ እንደሚገባው ገልፀዋል።

ኤስ ኦ ኤስ የህፃናት መንደር ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ከዚህ ማዕከል ጋር በሚያከናውናቸው ተግባራት ትውልዶችን የማገናኘት ስራ እየሰራ እንደሆነም ተገልጿል። እነዚህ አረጋውያን ያለፈው ታሪክ ባለቤት እና ሙሉ መረጃው በእጃቸው ላይ ያለ ሲሆን፤ በመንደሩ ውስጥ የሚያድጉት ህፃናት ደግሞ ቀጣይ ትውልድ በመሆናቸው የአሁኑ ትውልድ እነዚህን ትውልዶች የማገናኘት ሥራ የመስራት ዓላማ እንዳለው ነው አቶ ሣህለማርያም የገለፁልን። በመሆኑም ያለፉት እሴቶች በቀጣዩ ትውልድ ውስጥ እንዲቀጥሉ የማድረግ ስራ ይሰራል። አቶ ሣህለማርያም እንዲህ ይገልፁታል። “የማእከሉ መረጃ እንደሚያመለክተው ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አረጋውያን ናቸው። እነዚህ ሰዎች ሰፊ የታሪክ እውቀት ያላቸው ናቸው። በእኛ እድሜ ያለው ትውልድ የአሁን ትውልድ ሲሆን፤ የምናሳድጋቸው ህፃናት ደግሞ ቀጣይ ትውልድ ናቸው። ስለዚህ እኛ መካከል ላይ ሆነን እነዚህን ሦስት ትውልዶች ለማገናኘት እንሰራለን። ስለዚህ ያለፈው ታሪካችን አይጠፋም። ህፃናቱም እና ወጣቶቹ የአባቶቻቸው ታሪክና እሴት ይዘው ያድጋሉ ማለት ነው” ይላሉ።

ኤስ ኦ ኤስ የህፃናት መንደሮች በኢትዮጵያ ባዘጋጀው በዚህ በዓል ላይ የመንደሩ ሰራተኞች የላቀ አስተዋፅኦ ላበረከቱት የመንደሩ ሰራተኞች ሽልማትን በማበርከት እንዲሁም ቀሪዎቹ ሰራተኞች ላበረከቱት አስተዋፅኦ በማመስገን የተከበረ ሲሆን፤ ለመቄዶኒያ የአረጋውያን እና አዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከልም፤ የ30 ሺህ ብር የገንዘብ ድጋፍ፣ የተለያዩ አልባሳት እንዲሁም በህፃናት መንደሩ ቴክኒክ ኮሌጅ የተሰሩ ቁሳቁሶች እና የገንዘብ መሰብሰቢያ ሳጥኖችን በስጦታ አበርክቷል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በርካቶች የሚያዘጋጇቸውን ዝግጅቶች ወደ ማዕከሉ ይዘው በመምጣት ከአረጋውያን እና አዕምሮ ህሙማን ጋር ማክበራቸው እየተለመደ መምጣቱ እንደ ጥሩ ጐን ሊወሰድ ይገባል የሚል ሀሳብ ያላቸው የማዕከሉ አማካሪ ዶክተር ጌታቸው ተድላ፣ ጥቅሙንም አስረድተውናል። እዚህ የሚኖሩ አረጋውያን እና አዕምሮ ህሙማን መታየታቸው በሌሎች ሰዎች ውስጥ “ለካ እንዲህም ሊረዳ ይችላል” የሚል መነሳሳትን እንደሚፈጥርም አማካሪው ገልፀውልናል። “እዚህ ማዕከለ ውስጥ ያሉ ሰዎች ለሀገራችን ትልቅ ነገር የሰሩ መጨረሻ ላይ ግን በየቦዩ ወድቀው የተገኙ ናቸው። ሁሉንም ብናናግራቸው እያንዳንዳቸው አንድ መጽሐፍ ሊወጣቸው የሚችሉ ናቸው። ስለዚህ በህይወት ዘመናቸው ብዙ ያሳለፉ በመሆናቸው በሰው ሲጐበኙ እና ከሰው ጋር ሲነጋገሩ ደስተኞች ናቸው” ይላሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ በማዕከሉ የሚረዱ አረጋውያን እና የአእምሮ ህሙማን በየጊዜው በበርካታ ሰዎች መጐብኘታቸው በሰዎቹ ላይ ሊያመጣ የሚችለው ነፃነትን የመነፈግ ስሜት ሊኖር እንደሚችል ዶክተር ጌታቸው ይገልፃሉ። እንደ እርሳቸው ገለፃ የግለሰቦች ነፃነት አጠያያቂ ቢሆንም ነገር ግን አስገዳጅ ሁኔታም ይኖራል። “ነፃነት ቢኖር ያለ ምንም ጥርጥር ይመረጣል። ነገር ግን እነዚህ በማዕከሉ የሚኖሩ ሰዎች የሚበሉትም የሚጠጡትም ከሚጐበኟቸው ሰዎች በሚገኘው እርዳታ ነው። ስለዚህ እነርሱ ወደዱም ጠሉም ሰዎች ሊጐበኟቸው ይገባል። ነገር ግን ብዙዎቹ ሰው ሲጠይቃቸው እና ሲጐበኛቸው ደስ ሲላቸው ነው የማየው”■

# ራትን ቁርስ ላይ

በዳንኤል ክብረት

አፍሪካውያን ቀደምት አያቶቻችን እንዲህ የሚል ትንቢት አዘል አባባል ነበራቸው:: “የዚህ ትውልድ ትልቁ አደጋ ራታቸውን በቁርስ ሰዓት ለመብላት መፈለጋቸው ነው”:: ሰው እንደ መላእክት አይደለምና በሂደት እየበሰለ፣ በሂደት እየተገነባ፣ በሂደትም የበለጠ እየተማረ የሚሄድ ፍጡር ነው:: ይኼ ደግሞ የመንፈስ፣ የአካል፣ የስሜትና የአእምሮ ዕድገትና ለውጥን ይጠይቃል:: ሰው ሲወለድ ለማደግና ለመለወጥ ከሚያስችል ዐቅም ጋር ነው:: ይህንን ዐቅም ተጠቅሞ ለማደግና ለመለወጥ ግን ልምድ፣ ትምህርትና የሰውነት ግንባታ ያስፈልጉታል:: ልምድ የሚባለው ከተወለደ ጊዜ ጀምሮ በሕይወት ውጣ ውረድ የሚደርስበት ተሞክሮ ነው:: ይህም የሕይወት ተጋድሎ ይባላል:: ትምህርት ከሰዎች፣ ከትምህርት ቤት፣ ከመጻሕፍት፣ ከአካባቢውና ከሌሎችም የዕውቀት ምንጮች የሚያገኘው ጥበብ ነው:: የሰውነት ግንባታ የሚባለው ደግሞ በምግብና በእንቅስቃሴ የሚያበለጽገውን አካል ነው::

እነዚህ ነገሮች የሚመጡትና የሚከናወኑት በሂደት ውስጥ በመሆኑ ሰዎች ለተለያዩ የኑሮ ደረጃዎች የሚበቁበት ጊዜ ይለያያል:: በልጅነት፣ በወጣትነት፣ በዐዋቂነትና በአረጋዊነት ጊዜ የሚከናወኑት ተግባራት በዚያው በየዘመናቸው እንዲከናወኑ የሚያስገድዱት ሰዎች እነዚህን ነገሮች ለማከናወን የብስለታቸው ደረጃ እንደ ዕድሜያቸውና በዚያ ዕድሜ የተነሣ እንደሚያገኙት ልምድና ዕውቀት ብሎም አካላዊ ዝግጁነት ስለሚለያይ ነው:: የልጆች ጋብቻንና የልጅነት ጊዜ ወሊድን የምንቃወመው፣ ጋብቻም ሆነ ወላጅነት የሚፈልጓቸው የመንፈስ፣ የአካል፣ የስሜትና የአእምሮ የዕድገት ደረጃዎች ስላሉ ነው::

የመንፈስ ዕድገት የምንለው በመንፈሳዊው ዓለም ሰው የሚኖረው ዕድገትና ለውጥ ነው:: በእምነት፣ በአመለካከት፣ በመርሕና በአተያይ የሚኖረው የብስለት ደረጃ:: የስሜት ዕድገት ለነገሮች የሚኖረንን ፍቅርና ጥላቻ፣ ቀረቤታና ርቀት፣ ሙቀትና ቅዝቃዜ፣ ስበትና ግፊት የምንለካበት የዐቅም መጠን ማደግ ነው:: እነዚህን ነገሮች ለመቆጣጠር፣ ሕጋዊ፣ ሰላማዊ፣ ትክክልና ተገቢ በሆነው መንገድ ለመምራት ያለን ዐቅም ማለት ነው:: የአእምሮ ዕድገት ስንል ደግሞ በዕውቀት ማደግን ነው::

በትምህርት፣በልምድና በሰውነት ግንባታ እያደገና እየተለወጠ የሚሄደው ሰው፣ ሕይወቱ ተከታትለው በሚመጡ ሦስ ነገሮች የሚዘወር ነው:: ዐሉላ ጥላሁን ‹‹የሕይወት ሙሻዙር›› ይለዋል:: እነዚህ ሦስቱ ጉጉት፣ ተጋድሎና ስኬት ይባላሉ:: በሰው ሕይወት ውስጥ የሚያጓጓ፣ ይደረስበታል ተብሎ የሚታሰብ፣ የሚናፈቅና ተስፋ የሚደረግ ነገር ከሌለ ተጋድሎ የሚባለው የሕይወት ዋነኛ አጣፋጭ፣ ሰውንም ወደ ሙሉ ሰውነት የሚያደርሰው ታላቁ ድልድይ ተሰብሯል ማለት ነው:: እርሱ ከተሰበረ ደግሞ ስኬት የሚባለው ነገር አይታሰብም:: በዓለማችን ላይ ከፍተኛ ሥልጣኔ የተመዘገበባቸው ሀገሮችና ዘመናትን ታሪክ ብናጠና እነዚህ ሦስቱ ነገሮች ገንዘባቸው የነበሩ መሪዎችን፣ ሊቃውንትንና ሕዝቦችን እናገኛለን:: በሌላ በኩል ደግሞ በኋላ ቀርነት ይሰቃዩ የነበሩና አሁንም የሚሰቃዩትን ሕዝቦች ስናይም እነዚህ ነገሮች ሲያጥሯቸው እናስተውላለን::

ሰው ይህንን የሕይወት ሙሻዙር ዘውሮ ሕይወቱን ወደ ልዕልና እንዳያደርሳት የጉጉት፣ ተጋድሎና ስኬትን መሥመር የሚሰብሩ አራት ነገሮች አሉ:: የመጀመሪያው ዋናን የሚያጠፋ ርዳታ ነው:: ርዳታ ወይም እገዛ መልካም የሚሆነው ዓሣ ሊያሰግር የወጣውን ሰው በቀላሉ ብዙ ዓሣዎች እንዲያሰግር የሚያስችለውና እርሱም የተሻለ ማስገሪያ እንዲሠራ የሚያበቃው ዓይነት ርዳታ ከሆነ ነው:: ሰውዬው ቁጭ ብሎ ዓሣ እንዲያገኝና ምንም እንዳያስብ የሚያደርገው ርዳታ ግን ርዳታ ሳይሆን ግድያ ነው:: መጀመሪያ ብዙ ዓሣ ለማስገር የነበረውን ጉጉት ይገድልበታል:: ቀጥሎ ያንን ጉጉት ለማሟላት እንዳይጋደል ያሰንፈዋል:: በመጨረሻም ስኬት አይኖረውም:: ስኬት ማለት የጥረት ውጤት ነውና:: ያለ ጥረት በዱብ ዕዳ የተገኘ ነገር ሁሉ ስኬት አይደለም:: ዕድል፣ ዕጣ ወይም ስጦታ ይሆናል እንጂ:: ሰውን ወደ ዕድል፣ ዕጣና ስጦታ ደረጃ ማውረድ ደግሞ ከሰውነት አሳንሶ ‘መትኅተ ሰብእ መልዕልተ እንስሳት’ ማድረግ ነው:: ራቱን ቁርሱ ላይ እንዲበላው ማድረግ:: ነገ ልታገኘው የምታስበውና የምትለፋለት አዲስ ነገር ከሌለህ ‘ነገ’ ለምን ይምጣ? ‘ነገ’ ስ ከአንድ ተጨማሪ ቀን ውጭ ሌላ ምንድን ነው?

ሁለተኛው ሰባሪ አደጋ ደግሞ በወንጀል የተገመደ አቋራጭ መንገድ ነው:: በስርቆት፣ በጉቦ፣ በማስመሰል፣ በሥልጣን በመባለግ፣ የሰዎችን ዕድል በማበላሸት፣ ትውልድን በመግደል፣ ሀገርን በማጥፋት፣ ወዘተ በኩል የሚገኝ አቋራጭ መንገድ:: በቀላሉ ሥልጣን፣ ገንዘብ፣ ክብር፣ ስምና ዝና የሚገኝበት:: ይህ መንድ ምናልባት ገንዘብ፣ ስምና ክብር፣ ሥልጣንና ዝና ያስገኝ ይሆናል:: ውስጣዊ ደስታ ግን አያስገኝም:: ደስታ ከስኬት የሚገኝ ነውና:: ሌሎቹን ነገሮች ማስመሰል ቢቻልም ውስጥን ማስመሰል ግን አይቻለም:: ደስታ ውስጣዊ ስለሆነ ነው አስመስሎ መሥራት የማይቻለው::

> ሰው በሂደት የሚሟላ ፍጡር ነው። የሚያሟሉትም ትምህርት፣ ልምድና የሰውነት ግንባታ ናቸው። እነዚህ ደግሞ የሚፈጸሙት በጊዜ ውስጥ ነው። ለሁሉም ጊዜ አለው የተባለውም ለዚህ ነው

እንዲህ ባደረገ ሰው ውስጥ የሚፈጠረው ጦርነት የትም ቦታ የማይፈጠር ነው:: የሕግ መውጣት፣ የሥርዓት መለወጥ፣ የዳኝነት ሥርዓት መጠንከር፣ የሚዲያ ምርመራ መጀመር፣ የሰዎች ዕውቀት መጨመር፣ እርሱ የፈጸማቸውን ነገሮች የሚቃወሙ አሠራሮች መምጣት፣ የዓለም አስተሳሰብ እየተቀየረ መሄድ ያሳስበዋል:: ያስጨንቀዋል:: ለዚህም ነው እውነተኛውን ደስታ የማያገኘው:: ድሮ “ከዕለታት አንድ ቀን” የሚለው መግቢያ ለተረት የሚያገለግል ነበረ:: ዛሬ ዛሬ ግን ለሰዎችም ያገለግል ጀምሯል:: “ከዕለታት አንድ ቀን እገሌ ድንገት ኢንቨስተር ሆነ፣ ድንገት ባለ ሀብት ሆነ፣ ድንገት ባለ ዘጠኝ ፎቅ ሆነ፣ ድንገት ባለ ሥልጣን ሆነ፣ ድንገት ባለ ኩባንያ ሆነ፣›› ከየት ተነሥቶ፣ በየት በኩል ሄዶ፣ ምንም አድርጎ? መልስ የለም:: “እንዴው ከዕለታት በአንድ ቀን›› ነው መልሱ:: በዚህ መንድ የሚመጡ ሰዎች ስኬታማ አይደሉምና ደስተኛም አይደሉም:: ደስተኛ ግን ይመስላሉ:: ራታቸውን ቁርሳቸው ላይ ስለበሉት ምንጊዜም የራት ነገር ሲያሳስባቸው ይኖራል:: ራት ያልበላ ሰው የሚተኛውን የረሃብ ዕንቅልፍ ስለሚተኙ፣ አልጋ እንጂ ዕንቅልፍ አይኖራቸውም:: ቅዠት እንጂ ሕልም አይታያቸውም::

ሦስተኛው ሰባሪ አደጋ ዕድል፣ አጋጣሚና የተመቻቸ ሁኔታ የሚፈጥሩት ግሽበት ነው:: የማስተማሪያ ዐቅምና ዕድል ስላገኘን ብቻ ልጃችንን ያለ ዕድሜው ወደ ትምህርት ቤት ብንልከው ልጁ እየተማረረ እንጂ እየተማረ አይመጣም:: በኋላም ከፍ ሲል ትምህርት ጠል ከሚሆንባቸው ምክንያቶች አንዱ ያለ ዕድሜ ወደ ትምህርት ቤት መግባትና መደበኛ ትምህርት መጀመር ናቸው:: ዕድልና አጋጣሚ አገጣጥሞላቸው ያለ ከዕድሜና ከዕውቀት በፊት ገንዘብ ማግኘት ያቻሉ አንዳንድ ሰዎች ገንዘቡ መጥፊያቸው ሲሆን አይተናል:: አካባቢያቸውን ለማስተዳደር መጀመር ባለባቸው ጊዜ አገር ማስተዳደር የሚጀምሩ፣ ቤተሰባቸውን መምራት ከመጀመራቸው በፊት የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት መምራት የጀመሩ ሰዎች ዕድሉን ለስኬት ከመጠቀም ይልቅ ሀገር ለማጥፋት የሚጠቀሙበት በዚህ ስኬት ሰባሪ አደጋ የተነሣ ነው:: ራታቸውን ቁርስ ላይ በልተውት::


ዛሬ ዛሬ በጋብቻ ውስጥ ብቻ ሊደረጉ የሚገባቸው ነገሮች ከጋብቻ በፊት፣ በበሳል ዕድሜ ሊፈጸሙ የሚገባቸው ጾታዊ ግንኙነቶች በሚዲያ፣ በፊልም፣ በማኅበራዊ ድረ ገጾችና በአንዳንድ አቀንቃኞች ምክንያት በሚፈጠሩ የስሜት መመቻቸቶች የተነሣ በልጅነት ዕድሜ እየተፈጸሙ በመምጣታቸው ሰዎች ራታቸውን ቁርስ ላይ በልተው የሚጓጉለት ነገር እንዳይኖር አድርጓቸዋል:: ልጆች ተምረው ሊያገኙት የሚገባውን ነገር የድመት ፍቅር በያዛቸው ወላጆች ምክንያት ሳይማሩ ስለሚያገኙት ለትምህርት ሊያውሉት የሚያስፈልግ ጉጉትና ጥረት ተሚጥጠባቸዋል:: በምዕራቡ ዓለም ታላላቅ ሰዎች ልጆቻቸውን በኩባንያቸውና በፖለቲካ መሥመራቸው መተካት የቻሉት፣ ልጆቹ መሥመሩን ተከትለው በመጋደል መሥመሩ የሚያስገኝላቸውን እያገኙ እንዲያድጉ በማድረጋቸው ነው:: የአባታቸው ሀብት ስለሆነ ብቻ አያገኙትም፤ ተምረው፣ ሠርተው፣ ከሌሎቹ ጋር ተወዳድረው፣ ከታች እስከ ላይ ያለውን የዕድገት መሰላል በመንፈስ፣ በትምህርት፣ በልምድና በአካላዊ ዕድገት እየዳበሩ አልፈው፣ በተወዳዳሪነትና በአሸናፊነት ተጋድሎ ተፈትነው ሲደርሱ፤ ያን ጊዜ ወላጆቻቸው ‘ተቀመጥ በወንበሬ፣ ተናገር በከንፈሬ’ ብለው ያስረክቧቸዋል:: ሳንቲሞች እንዴት እንደመጡ ሳያውቁ ብሮችን አያስነኳቸውም:: ነገ ሊደርሱበት የሚገባውን ራት ዛሬ በቁርስ ሰዓት አያበሏቸውም:: ልጅ ምንም ያህል ቢፈለግ በሦስት ወር ይወለድ አይባልምና::

አራተኛው ሰባሪ አደጋ የሚመጣው በጋሸበ አድናቆትና ግፊት ነው:: አንዳንድ ጊዜ ከሰዎች የሚሰጠንን አስተያየት፣ ድጋፍ፣ ተቃውሞ፣ ክብር፣ ዝና፣ ስምና ታላቅነት ከውስጣችን ዐቅም ጋር መዝነን ካላስተናገድነው አደጋ ያስከትላል:: ሰዎች ትችላላችሁ፣ ያለ እናንተ ሰው የለንም፣ ጀግና ናችሁ፣ ስላሉን ያሉንን ሁሉ አንሆንም:: ጭብጨባውን፣ ሙገሳውን፣ አድናቆቱን ለችሎታ መመዘኛነት ከወሰድነው ከራሳችን ጋር እንጣላለን:: ቀስ በቀስ በዕድገትና በልምድ፣ በትምህርትና በተጋድሎ ልንደርስበት የሚገባንን ገፋፍተው ሲያወጡን ከተቀበልንና ‘ሕዝብ ከመረጠኝ፣ ሕዝብ ካለ፣ ሕዝቡ ከደገፈኝ’ ካልን ራታችንን ቁርስ ላይ ያስበሉናል:: እላይ ከወጣን በኋላም የምናደርገው ይጠፋናል:: በውጫዊ ግፊትና አድናቆት ‘ነህ’ የሚሉንን ከመቀበል በውስጣዊ ዕውቀት ‘አይደለህም’ የሚለንን መቀበሉ ያዋጣናል:: ዛሬ ዓለምን ለበሽታ የዳረጓት ዕንቁላል ሳይሆኑ ዶሮ የሆኑት ናቸው::

ሰው በሂደት የሚሟላ ፍጡር ነው:: የሚያሟሉትም ትምህርት፣ ልምድና የሰውነት ግንባታ ናቸው:: እነዚህ ደግሞ የሚፈጸሙት በጊዜ ውስጥ ነው:: ለሁሉም ጊዜ አለው የተባለውም ለዚህ ነው:: አንድን ነገር ዕድል ስላገኘን፣ ነገሮች ስለተመቻቹ፣ አቋራጭ መንገድ ስላለው፤ በአድናቆትም ሆነ በተቃውሞ ስለተገፋፋን፣ ጊዜ የሰጠው ቅል ስለሆንን ወይም ደግሞ በምናያቸው ፊልሞች፣ በምናነባቸው ስሜት ቀስቃሽ ጽሑፎች፣ ከጓደኞቻችን በሚፈጠሩብን ግፊቶች ተስበንና ተገፍተን ራታችንን ቁርስ ላይ መብላት የለብንም:: ጉጉት የሌለው ነገ፣ የማይጋደሉበትም ሕይወት ስኬትን አያመጣምና:: ስኬትን የማያጣጥም ሰውነት ደግሞ ምንጊዜም ውስጡ ክፍተት ይኖረዋል:: ያ ክፍተት ነው ተስፋ መቁረጥን፣ ትካዜን፣ ራስን መጥላትን፣ የበታችነትን፣ ወራዳነትንና ራስን መጥፋትን የሚፈጥረው::

# ተጨማሪ ኢንቨስትመንቶችን...

ዝዋይ ከተማና አካባቢዋ በስምጥ ሸለቆ ስር የሚገኙ ናቸው:: አካባቢው ከባህር ጠለል በላይ ባለው ከፍታና በአየሩ አመቺነት ለወይን አትክልት ተስማሚ መሆኑን ባለሙያዎቹ ይገልፃሉ:: ይሁንና ስምጥ ሸለቆ አካባቢ በበርካታ የወፍ ዝርያዎች የታወቀ ከመሆኑ አንፃር የወይን ልማትን ለማካሄድ የቦታ መረጣው ምን ያህል አግባብነት አለው የሚል ጥያቄ ከጋዜጠኞች ተነስቶ ነበር:: ለዚሁ ምላሽ የሰጡት የእርሻው ኃላፊዎች በአካባቢው በርካታ የወፍ ዝርያ የሚገኝ መሆኑን ገልፀው ይሁንና አእዋፋቱ በወይን ዝርያ ላይ ጉዳትን እንዳያደርሱ የወይን ዘለላዎቹን በመረብ (Bird net) በመሸፈን፣ የንስር ቅርፅ ያላቸው ምልክቶችን በማሳው መሀል በማሰቀመጥና አእዋፋትን ሊያባርሩ የሚችሉ የተለያዩ ድምፆችን (Syrens) በመጠቀም አእዋፋቱን መከላከል የሚቻል መሆኑን አስታውቀዋል:: ለባለሙያው ከዚህም በተጨማሪ የወይን አትክልት ከሌሎች የእፅዋት ዝርያዎች በተለየ ሁኔታ ለምን ለጠጅ ምርት ተመራጭ ሆነ የሚል ጥያቄም ተነስቶላቸው ነበር:: የወይን አትክልት በተፈጥሮው ስሩ ወደ መሬት በጥልቀት ስለሚገባና በመሬትም ወስጥ ያሉትንም ልዩ ልዩ ማዕድናት በመሳብ ፍሬው ውስጥ የማስገባት አቅም ስላለው በማዕዛውም



ካስትል የወይን ጠጅ ምርቶቹን ለአገር ውስጥ ገበያ ከማቅረብ ባለፈ ኤክስፖርት በመድረግም ምርቶቹን ወደ ቻይና አሜሪካ፣ ጀርመን፣ ስዊድንና አውስትራሊያ መላክ ጀምሯል

ሆነ በተለያዩ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎቹ የወይን ፍሬ ለጠጅነት ተመራጭ መሆኑን ኃላፊዎቹ ጨምረው አብራርታዋል::

ካስትል የወይን ጠጅ ምርቶቹን ለአገር ውስጥ ገበያ ከማቅረብ ባለፈ ኤክስፖርት በመድረግም ምርቶቹን ወደ ቻይና አሜሪካ፣ ጀርመን፣ ስዊድንና አውስትራሊያ መላክ ጀምሯል:: በዓለም አቀፍ ደረጃ በወይን አምራችነቱ የታወቀው ካስትል ኩባንያ በኢትዮጵያ በዘርፉ መሰማራቱ ሌሎች ታላላቅ መሰል ኩባንያዎችም በኢትዮጵያ መዋዕለ ነዋያቸውን ለማፍሰስ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው እያደረገ ነው ተብሏል:: ቀደም ሲል በወይን ምርት የታወቁ የአውሮፓ አገራት አሁን ካለው የዓለም ሙቀት መጨመር (Global Warming) ጋር በተያያዘ ለወይን አመቺነት የነበረው የአየር እየተቀየረ በመሄዱ ባለሀብቶቹ ወደ አፍሪካና ላቲን አሜሪካ እያማተሩ ሲሆን፤ ተመራጭ ከሆኑት አገራት መካከልም ኢትዮጵያ አንዷ መሆኗ ታውቋል:: ግዙፉ ካስትል የወይን ጠጅ አምራች ኩባንያም በኢትዮጵያ መዋለ ነዋዩን ማፍሰሱ በርካታ በዘርፉ የተሰማሩ ኩባንያዎችም ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለከቱ እያደረጋቸው መሆኑ ታውቋል::

# ዮርዳኖስ አባይ

## ከ11 ዓመት በኋላ ፕሪሚየር ሊጉ ቆሞ ጠብቆታል

በቆንጂት ተሾመ

በኢትዮጵያ እግር ኳስ ታሪክ በ1990ዎቹ አመታት ደምቀው ከነበሩ ተጫዋቾች መካከል አንዱ ዮርዳኖስ አባይ ነው። ከድሬደዋ አሸዋ ሜዳ የጀመረው ህይወቱ በሀገር ውስጥ ክለብ ደረጃ ድሬደዋ ጨርቃጨርቅና ምድር ባቡር፣ መብራት ሀይል ከዚያም ኢትዮጵያ ቡና ዘልቆ የላቀ ስምና ዝናን አትርፏል። በ1993 ዓ.ም. ለመብራት ሀይል በተሰለፈባቸው 26 የፕሪሚየር ሊግ ጨዋታዎች 24 ግቦችን በማስቆጠር ኮከብ ግብአግቢነት ክብርን ተቀዳጅቷል። እስከአሁን ድረስም ይህንን የግብ ብዛት ያለፈ ወይም የደረሰበት ተጫዋች በፕሪሚየር ሊጉ አልተገኘምና ክብረወሰኑ በስሙ እንደተመዘገበ ነው።

መብራት ሀይል እንዳለፉት ጥቂት አመታት ላለመውረድ ሳይሆን ለዋንጫ የሚጫወት ቡድን እንዲሆን ካስቻሉት ተጫዋቾች መካከልም ዮርዳኖስ አባይ ዋነኛው ነበር። በግሉ ተጽዕኖ መፍጠር የቻለ ተጫዋች መሆኑ ብዙዎችን ያስማማል። ለዚህም እርሱ 24 ግቦች ባስቆጠረበት 1993 ዓ.ም መብራት ሀይል የፕሪሚየር ሊጉን ዋንጫ ማንሳት መቻሉን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል። በዚያው ዓመትም ክለቡ የጥሎ ማለፍና የሱፐር ካፕ አሸናፊ በመሆን የሶስት ዋንጫ ባለቤት ለመሆኑ ዮርዳኖስ ቁልፍ ሚና ነበረው።

የድሬው አጥቂ በመብራት ሀይልና ኢትዮጵያ ቡና ክለቦች ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ውስጥ ቆይታውም ስኬታማ ጊዜያትን አሳልፏል። መብራት ሀይል ውስጥ ድንቅ እንቅስቃሴ ማሳየቱን ተከትሎ ከ20 አመት በታች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ውስጥ ተመርጦ በወጣቶች የአፍሪካ ዋንጫ ላይ ተጫውቷል። በውድድሩም የወጣት ቡድኑን ለአለም ዋንጫ በማሳለፍ በግሉ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል።

በአርጀንቲናው የወጣቶች አለም ዋንጫ በግል ምርጥ ብቃት ካሳዩ ተጫዋቾች መካከል አንዱ የነበረው ዮርዳኖስ አባይ፣ ኢትዮጵያ በምድብ ማጣሪያ በኮስታሪካ 3ለ1 ስትሸነፍ ብቸኛዋን ግብ ማስቆጠሩ ይታወሳል። በኔዘርላንድ 3ለ2 በተሸነፈችበት ጨዋታም ድንቅ እንቅስቃሴ ማድረጉ አይዘነጋም። ከዓለም ዋንጫው በኋላ በቤልጂየምና ሆላንድ ክለቦች ለመጫወት ያደረገው ሙከራ ባመሳካቱ ወደ ሀገር ቤት በመመለስ ኢትዮጵያ ቡናን ነበር የተቀላቀለው።

በኢትዮጵያ ቡና በነበረው የሁለት አመት ቆይታው (1994 እና 1995 ዓ.ም.) የጭሎ ማለፍ ዋንጫ ያነሳ ሲሆን፣ በደጋፊዎች ዘንድ የተወደደለትን ክህሎት ማሳየት ችሏል። ሊጉ ጠንካራ ፉክክር እንዲታይበት ካስቻሉ ተጫዋቾች መካከልም አንዱ ነበር። በወቅቱም ሜዳ ውስጥ በተመልካቾች ዘንድ አድናቆትና ትችትን ከሚቀበሉ አነጋጋሪ ተጫዋቾች አንዱ ነበር።

በሴካፋ ዋንጫ እነ አሸናፊ ግርማ፣ አንዷለም ንጉሴ አቤጋና ዘውዱ በቀለን የመሳሰሉ ተጫዋቾች ባሉበት ቡድን ውስጥ እ.ኤ.አ. በ2001 የሴካፋ ዋንጫን አንስቷል። በሀገር ውስጥ ውድድሮች የግልም ሆነ የቡድን ስኬቶችን መጎናጸፉ ለሌላ የውጭ ሀገር ሊግ እንዲፈለግ አድርጎታል። እናም በ1995 ዓ.ም. መጨረሻ ላይ ጥሩ ክፍያ ወደሚያገኝበት የመን ሊግ አመራ።

በየመን ሊግ አልሳክር ለተባለው ክለብ በመፈረም ከአስር አመት በላይ የተጫወተ ሲሆን፣ ለሶስት ጊዜ የሊጉን ዋንጫ አንስቷል። ሊጉን በተቀላቀለ የመጀመሪያ አመት እ.ኤ.አ. በ2003 እና በ2005 ኮከብ ግብ አግቢ ሆኖ ጨርሷል። የክለቡ የምንጊዜም ግብ አግቢ ሆኖ ታሪክ ላይ አጽፏል። በየመን ሊግ የምንግዜም ኮከብ ግብ አግቢ ከሆኑ ተጫዋቾች መካከልም በአምስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። በሀገሪቱ ሊግ የተሳካ የእግር ኳስ ጊዜ ካሳለፉ የውጭ ሀገር ተጫዋቾች መካከልም በቀዳሚነት የሚጠቀስ ነው።

ዮርዳኖስ አባይ ወደ የመን ከተጓዘ በኋላ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ በፊት መስመር ተጫዋችነት የእሱን ያህል የእግር ኳስ ክህሎትና ብቃት ያለው ተጫዋች አልታየበትም ማለት ይቻላል። በተለይም ደግሞ ወጥ የሆነ አቋም ይዘው ለአመታት የዘለቁ ተጫዋቾችን መጥቀስ አስቸጋሪ ነው። ታፈሰ ተስፋዬ ኢትዮጵያ ቡና በነበረበት ጊዜ ግቦችን በማስቆጠር ቡድኑን ውጤታማ አድርጓል። የዮርዳኖስን ክብረወሰኑን ለመስበር ያደረገው ጥረት ሳይሳካለት ቀርቷል። ሌላው የግብ አዳኝ አሁን በደቡብ አፍሪካ ቢድቪትስ ዊትስ ክለብ የሚገኘው ጌታነህ ከበደ ከሁለት አመት በፊት ደደቢት ሳለ የዮርዳኖስን ክብረወሰን ለመስበር ተቃርቦ ነበር። እርሱም 22 ግቦች ላይ ደርሶ ቆሟል። ሳላዲን ሰኢድና አዳነ ግርማ በጊዮርጊስ፣ ሳሉ በፊት መስመር ተጫዋችነት ምርጥ ብቃት ቢያሳዩም የዮርዳኖስን የግብ ክብረወሰንና ብቃት ሊያስረሱ አልቻሉም።

ዮርዳኖስ አባይ ግን በየመን ሊግ ለአል ሳክር በርካታ ግቦችን እያስቆጠረ ክብረወሰኖችን አስመዝግቧል። በቅርቡ ደግሞ በሀገሪቱ እግር ኳስን በቃኝ ብሎ ሲሰናበታቸው ደማቅ የሽኝት ጨዋታ ተደርጎለታል። የክለቡን የወጣት ቡድን በማሰልጠን ቆይታውን እንዲያራዝም ቢጠየቅም እርሱ ግን ወደ ሀገሩ መመለስን መርጧል። በሀገሪ ከፍተኛ ሊግ ኳስ መጫወቱን እንደሚቀጥል ግን ብዙዎች አልጠረጠሩም። የውጭ ሀገር ተጫዋቾችንና ስመ ጥር ተጫዋቾችን በማስፈረም የተጠመዱት ክለቦቻችን ለቀድሞው የሊጉ ኮከብ ትኩረት ይሰጣሉ የሚል ግምት አልነበረም። በቅርቡ ከዋና አሰልጣኙ ከቡልጋሪያዊው ስቶይኮብ ጋር የተለያየው መብራት ሀይል ግን ለቀድሞው የክለቡ ጀግና ቦታ አላጣም። አሁንም ተጫዋቹን አምኖታል። ከ14አመት በፊት አስፈርሞት የነበረውን የድሬውን አጥቂ ለሁለተኛ ጊዜ አስፈርሞታል።



የዮርዳኖስ አባይ ዳግም ወደ መብራት ሀይል ተመልሶ መጫወት በእግር ኳሳችን ላይ ብዙ ነገሮችን የሚያሳይ ነው

ከሳምንት በፊት መብራት ሀይል ከዳሽን ባንክ በተጫወቱበት የፕሪሚየር ሊጉ ጨዋታ ላይም ዮርዳኖስ የቀድሞ ክለቡን መለያ ለብሶ ወደ ሜዳ ገብቷል። ክለቡ አቻ የተለያየባትን ብቸኛ ግብም ከመረብ አሳርፏል። ተጫዋቹ አሁንም ድንቅ የአጨራረስ ብቃቱ ከእሱ ጋር እንዳለ አሳይቷል። በእለቱ ቡድኑን ከሽንፈት የታደገችዋን ግብ ያስቆጠረው ዮርዳኖስ የተጋጣሚ ቡድን ተከላካዮችን ማስጨነቅ ችሏል። ጥሩ ኳሶችን ቢያገኝ ወደ ግብነት መቀየር እንደሚችል ደጋፊዎቹን አሳምኗል።

የዮርዳኖስ የግብ አዳኝነት ችሎታ አሁንም እንዳልነጠፈ ሌላኛው ማሳያ ደግሞ እሁድ እለት መብራት ከአርባ ምንጭ ከነማ 1ለ1 በተለያየበት ጨዋታ ነው። በጨዋታው መብራት ሀይል ነጥብ ተጋርቶ እንዲወጣ ያደረገችዋን ብቸኛ ግብ አስቆጥሯል። የተገኙ የግብ እድሎችን በቀላሉ መጠቀም የሚችል ተጫዋች መሆኑንም አስመስክሯል። በመጀመሪያ ተከታታይ ጨዋታዎቹ ግቦችን በማስቆጠር የታዳጊነት ክለቡን መታደግ የቻለው ዮርዳኖስ አባይ በቀጣይም በሊጉ የደበበዘውን መብራት እንደሚያደምቀው ከወዲሁ መገመት ይቻላል። ከእንግዲህም መብራት ላለመውረድ የሚጫወት ክለብ እንደማይሆን የዮርዳኖስ እንቅስቃሴ ተስፋ ሰጥቷል።

ዘንድሮ ዮርዳኖስ ወደ ኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ሲመለስ ከ11 አመት በኋላ ነው። እድሜው 30 መሆኑን የፓስፖርቱ መረጃ ያመለክታል። ሆኖም ኢትዮጵያ ውስጥ የተጫዋቾችን ትክክለኛ እድሜ የማይታወቅ በመሆኑ የዮርዳኖስን እድሜ 30 ብቻ ነው ብሎ ማመን ያስቸግራል። ከ14 አመት በፊት ኮከብ ግብ አግቢ የነበረ ተጫዋች፣ ለታዳጊ ቦታ የማይሰጡ በኢትዮጵያ ክለቦች ታሪክ ከ14 አመት በፊት በመብራት ሀይል በዋና ቡድን ውስጥ የተካተተና ከ20 አመት በታች የአለም ዋንጫ ላይ የተሰለፈ ተጫዋች፣ አሁን ላይ 30 አመቱ ነው ማለት ይከብዳል። ከ30 አመት በላይ እንደሚሆነው መገመት ግን ይቻላል።

አሁን ዮርዳኖስ ኮከብ የነበረበት ዘመን የተለየ ነው። እግር ኳሱ የገባቸው ወጣትና ጠንካራ ተጫዋቾች ይኖራሉ ተብሎ ይታመናል። በኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግም ለተጫዋቾች የሚሰጠው ዋጋ ከፍ ብሏል። ኳሱ በጣም ፈጣንና ጠንካራ እንዲሁም የጋለ ፍላጎት ያላቸው ተጫዋቾችን የሚፈልግ ነው። ክለቦች በከፍተኛ ገንዘብ ከማዛወር በተጨማሪ ከውጭ ሀገር ጭምር ተጫዋቾችን በማስመጣት ውጤታማ ለመሆን የሚፎካከሩበት ዘመን ነው። ይህ ሁሉ ግን ለዮርዳኖስ አባይ ፈታኝ አልሆነም።

የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ከ11 አመት በኋላም ቆሞ ጠብቆታል። ሊጉ አንድ እርምጃ ወደፊት ተራምዶ እርሱን የሚያስንቅ ተጫዋች አላፈራም። ክለቦች ለቋሚ ተሰላፊነት የሚመርጧቸው ተጫዋቾችን እስኪቸገሩ ድረስ ብቃት

ያላቸው ተጫዋቾችን በብዛት ይዘው አላገኛቸውም። ተቀራራቢ ፉክክር የሚያደርጉ ክለቦች ቁጥር ከፍ ብሎ አልታየም። አሁንም የሁለትና ሶስት ክለቦች የዋንጫ ግልቢያ እንዳየለ ነው። ዋንጫ ያነሳበት ክለቡ መብራት ሀይልም በየጊዜው ሳለመውረድ የሚታገል ሆኖ ነው የጠበቀው። የውጭ ሀገር አሰልጣኝና ተጫዋች በከፍተኛ ገንዘብ ቢቀጥርም እንኳ የዋንጫ ተፎካካሪ ሊሆን አልቻለም። ዮርዳኖስ ግብ እያስቆጠረ መጫወት ችሏል። ወጣቶቹም ሆኑ ልምድ ያላቸው የሊጉ ተጫዋቾች የእርሱን እንቅስቃሴ መግታት አልቻሉም።

የዮርዳኖስ አባይ ዳግም ወደ መብራት ሀይል ተመልሶ መጫወት በእግር ኳሳችን ላይ ብዙ ነገሮችን የሚያሳይ ነው። የፕሪሚየር ሊጉን ደረጃ፣ የተጫዋቾችን ብቃትና ክህሎት፣ የክለቦችን የተፎካካሪነት ልክ እና ሌሎችንም ጉዳዮች እንድንፈትሽ የሚያደርገን ነው። ዮርዳኖስ ከአውሮፓ ሊግ አይደለም የመጣው። ለአስር አመት የተጫወተበት አል ሳክር በአህጉሩ እንኳ ጠንካራ የሚባል ክለብም አይደለም። የየመን ሊግ በጣም ደካማ ከሚባሉና ከኢትዮጵያም ባነሰ ደረጃ ከሚጠቀሱ ሊጎች መካከል አንዱ ነው። የተጫዋቹ እድሜ ገፍቷል። ግን አሁንም በኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ መጫወት ችሏል። በዚህም የተጫዋቹን የግል ብቃት ከማድነቅ ባሻገር ስለ እግር ኳሳችን የሚነግረንን እውነት መመልከት ይኖርብናል።

ወደ ቀድሞ ክለባቸው በመመለስ ለመጫወት የቻሉ በርካታ የአለማችን ተጫዋቾች አሉ። እንደ ዮርዳኖስ አባይ ግን ከ11 አመት በኋላ ወደ ክለቡ በመመለስ የተጫወተ ይኖር ይሆን?■

# ፍቅሩ የዋንጫ ባለቤትና የሴት ልጅ አባት ሆኗል




በህንድ ሱፐር ሊግ ለአትሌቲኮ ደ ኮልካታ የሚጫወተው ኢትዮጵያዊው አጥቂ ፍቅሩ ተፈራ ከክለቡ ጋር የዋንጫ ባለቤት ሲሆን፣ ከባለቤቱ ጋር ደግሞ ሴት ልጅ አባት ሆኗል። ለህክምናም ወደ ደቡብ አፍሪካ መመለሱ ታውቋል።

ዘንድሮ ለመጀመሪያ ጊዜ በተካሄደውና ስምንት ክለቦች ተሳታፊ የሆኑበት የህንድ ሱፐር ሊግ እሁድ እለት ፍጻሜውን አግኝቷል። በፍጻሜ ጨዋታው የፍቅሩ ክለብ አትሌቲኮ ደ ኮልካታ 1ለ0 በማሸነፍ የዋንጫ ባለቤት መሆኑን አረጋግጧል። በፍጻሜ ጨዋታው ፍቅሩ በጉዳት ባይሰለፍም ቡድኑን ለዋንጫ በማብቃት ከፍተኛ ሚና ከተጫወቱ ተጫዋቾች መካከል ዋነኛው ነው። ኢትዮጵያዊው አጥቂ ለክለቡ ወሳኝ የሚባሉ ግቦችን በማስቆጠር ኣበረከተው ሚና ከአሰልጣኙና ለክለቡ ባለቤቶች ምስጋናና አድናቆት ተችሮታል።

የቀድሞው የቅዱስ ጊዮርጊስ፣ የሱፐር ስፖርት ዩናይትድና ኦርላንዶ ፓይሬትስ አጥቂ፣ በህንድ ሱፐር ሊግ ከፍተኛ ተጽዕኖ መፍጠር ከቻሉ የውጭ ሀገር ዜጎች መካከል በዋነኛነት የሚጠቀስ ሆኗል። በሊጉም ሆነ በክለቡ ታሪክ የመጀመሪያ ሆና የተመዘገበችዋን ግብ በማስቆጠርም በህንድ እግር ኳስ ውስጥ ስሙን በደማቅ ቀለም ማጻፍ ችሏል። አምስት ግቦችን በማስቆጠርም ሁለተኛው ኮከብ ግብ አግቢ ሆኖ ጨርሷል።

ፍቅሩ በሳምንቱ መጨረሻ የህንድ ሱፐር ሊግ ዋንጫን በማንሳቱ በተጨማሪ የሴት ልጅ አባት በመሆንም አመቱ የደስታና የስኬት ሆኖለታል። የሴት ልጅ አባት መሆኑን ተከትሎ እንኳን ደስ ያለህ መልዕክታቸውን ያስተላለፉለት የክለቡ ባለቤትነት ላይ ድርሻ ያላቸው ሎስታቭ፣ ደቡብ አፍሪካ በሚሄድ ከቤተሰቡ ጋር የደስታ ጊዜውን እንዲያሳልፍና ህክምና እንዲያገኝ የተፈቀደለት መሆኑን ገልጸዋል።■

# ቅዱስ ጊዮርጊስ ከአልጄሪያ፣ ደደቢት ከሲሺየልስ ክለብ ተገናኝተዋል

ቅዱስ ጊዮርጊስና ደደቢት እ.ኤ.አ. በ2015 የውድድር አመት ሲጀመር በካፍ የክለቦች ውድድር መድረክ ኢትዮጵያን ወክለው የሚሳተፉ ክለቦች ናቸው። በቻምፒየንስ ሊጉ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከአልጄሪያው ኤል ኢውማ ከተባለ ክለብ የተገናኘ ሲሆን፣ ደደቢት ደግሞ በኮንፌዴሬሽን ዋንጫ ከሲሺየልሱ ኮት ደ ኦር ጋር ተመድቧል። ሁለቱም ክለቦች በቅድመ ማጣሪያው የመጀመሪያ ጨዋታቸውን ከሜዳቸው ውጪ 2015 የመጀመሪያ ወር አጋማሽ ላይ ያደርጋሉ።

ካፍ የ2015 የቻምፒየንስ ሊግና ኮንፌዴሬሽን ዋንጫ የማጣሪያ ጨዋታ ተጋጣሚዎችን ድልድል እሁድ እለት ይፋ አድርጓል። የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ አሸናፊው ቅዱስ ጊዮርጊስ ከአልጄሪያው ኤል ኢውማ ጋር ተመድቧል። ሁለቱ ቡድኖች በደርሶ መልስ በሚያደርጉት ጨዋታ ውጤት መሰረት ወደ አንደኛው ዙር የማጣሪያ ጨዋታ ማለፋቸውን ያረጋግጣሉ።

ጊዮርጊስ የመጀመሪያ ጨዋታውን ከሜዳው ውጪ የሚያደርግ ሲሆን፣ ከሁለት ሳምንት በኋላ ደግሞ የመልስ ጨዋታውን በሜዳውና በደጋፊዎቹ ፊት የሚያከናውን ይሆናል። ክለቡ በ2014 የቻምፒየንስ ሊግ ተሳትፎው ሩብ ፍጻሜ ድረስ በመጓዝ በክለቡ ታሪክ ጥሩ የሚባል ውጤት ማስመዝገቡ ይታወቃል።

በኮንፌዴሬሽን ዋንጫ ኢትዮጵያን ወክሎ የሚሳተፈው ደደቢት ደግሞ ከሲሺየልሱ ኮት ደ ኦር ክለብ ጋር የቅድመ ማጣሪያ ጨዋታ ያደርጋል። ደደቢት የመጀመሪያ ጨዋታውን እንደጊዮርጊስ ሁሉ ከሜዳው ውጪ ነው የሚያደርገው። የመልስ ጨዋታውን በሜዳው በማድረግም ወደ መጀመሪያው ዙር ማጣሪያ የማለፍ እድሉን ያሰፋል ተብሎ ይገመታል።■

## የዝውውር ወሬዎች

የማንቸስተር ዩናይትድ አሰልጣኝ ሉዊስ ቫን ኻል በስፔን ከሪያል ማድሪድ ጋር ስኬታማ ጊዜ እያሳለፈ የሚገኘው ጋርዝ ቤልን ለማስፈረም ድርድር እንዲጀምሩ ተፈቅዶላቸዋል። ከዚህ በተጨማሪም አሰልጣኙ የፈለጓቸውን የቤኔፊካ አማካዮች ኢንዞ ፔሬዝ እና ኒኮላስ ጌይታን እንዲሁም የሮማውን ኬቨን ስትሩትማንን ለማዛወር እንዲችሉ 80 ሚሊዮን ፓውንድ ተመድቦላቸዋል።

ሉዊስ ሱዋሬዝን ለባርሴሎና ከሸጠ በኋላ አጥቂ መስመሩ የሳሳበት ሊቨርፑል የቀድሞ ኮከቡን ፈርናንዶ ቶሬስን በድጋሚ ለማስፈረም አስቧል። ከቼልሲ ኤሲ ሚላን በሁለት አመት በውሰት የተቀላቀለው የ30 አመቱ ስፔናዊ አጥቂ አንፊልድን ለቆ ከሄደ ከአራት አመት በኋላ የመመለሱ ዜና እውን ከሆነ እርሱንም ሆነ ብዙ የሊቨርፑል ደጋፊዎችን ደስተኛ የሚያደርግ ነው።

የጣሊያኑ ኢንተር ሚላን የቶተንሃም ሆትስፐር የክንፍ መስመር ተጫዋች አሮን ሌነን ለማስፈረም ድርድር ጀምሯል። ከ27 አመቱ ሌነን በተጨማሪ የ21 አመቱን የዌስትብሮም አጥቂ ሰኢዶ ቤራሂኖን በመጪው ጥር ወር ለማዛወር እንቅስቃሴ መጀመሩን ዘ ሰን ጋዜጣ ዘግቧል።

አርሴናል በሳውዝ ሀምፕተን አስደናቂ ብቃት በማሳየት ላይ የሚገኘውን ሞርጋን ሽንደርሊንን ለማስፈረም ዳጎስ ያለ ፓውንድ መመደቡ ተሰምቷል። ክለቡ የ25 አመቱን አማካይ ተጫዋች በጥር ወር የዝውውር መስኮት ለማስፈረም መዘጋጀቱን ሜትሮ ጽፏል። አሰልጣኝ አርሰን ቬንገር በባየር ሊቨርኩሰን የሚገኘውን የ23 አመቱን አማካይ ክርስቶፍ ክራመርን ለማስፈረም አምና የጀመሩትን ጥረት ማጠናከራቸውንም ጋዜጣው ጨምሮ ገልጿል።

በእንግሊዞቹ አርሴናል፣ ቼልሲ፣ ሊቨርፑልና ማንቸስተር ዩናይትድ ሲፈለግ የነበረው የቦርሲያ ዶርትሙንዱ አማካይ ማርኮ ሬስ ምርጫው ወደ ስፔን አድልቷል። ተጫዋቹ ከሪያል ማድሪድ የቀረበለትን ጥሪ እምቢ ማለት እንዳልፈለገና የውድድር አመቱ ማብቂያ በኋላ በ20 ሚሊዮን ፓውንድ ሂሳብ ወደ ቤርናባው እንደሚያቀና ሰንዴይ ኤክስፕረስ ዘግቧል።

በአርሴናል ቋሚ ተሰላፊነት በእድል የተነፈገው ያያ ሳኖጎን በውሰት ለማስፈረም የሚፈልጉ የእንግሊዝ ክለቦች ጥያቄያቸውን በይፋ ማቅረብ ጀምረዋል። የ21 አመቱን አጥቂ በውሰት ለመውሰድ ከሚፈልጉ ክለቦች መካከል አስቶንቪላ፣ ስንደርላንድና ክሪስታል ፓላስ እንደሚገኙበት ዴይሊ ሜይል ዘግቧል።■

ደርባ ሲሚንቶ
DERBA CEMENT



# ከቡራትና ከቡራን ደንበኞቻችን!

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ላለፉት ጥቂት ወራት በጥገናና እድሳት ላይ ቆይቶ ሥራውን በማጠናቀቅ ወደ ሙሉ ምርታማነቱ ተመልሷል፡፡

የሲሚንቶን ዋጋ በማረጋጋት የሚታወቀው ፋብሪካችሁ እንደተለመደው ከፍ ያለ ጥራት ያላቸውን OPC እና PPC ሲሚንቶ በተለየ አደረጃጀት እደጃፋችሁ ድረስ ማድረሱን ከህዳር 29 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ የተለመደውን አገልግሎት መስጠት ጀምሯል፡፡

በዚህ አጋጣሚ በእድሳትና ጥገና ወቅት አብራችሁን ለቆያችሁት ደንበኞቻችን ወደር ለሌለው ትዕግሥታችሁ የደርባ ማኔጅመንትና ሠራተኞቹ ከፍ ያለና የከበረ ምስጋናቸውን ለእናንተ ለደንበኞቻቸው ያቀርባሉ!!

## "ለሁሉም ሥራ በሁሉም ሥፍራ ነገን ዛሬ እንስራ"
## "ደርባ ሲሚንቶ"